ዳሩል አርቀም

መስከረም 2008 1436 ዙል ሂጃ ቅፅ 002

መደራጀት



የኢትዮጵያ ሙስሊም የወቅቱ አጀንዳ?



ሂጅር - የፅናት ተምሳሌት

https://www.facebook.com/darularqem1
DARULARQEMETHIO GMAIL.COM

ዳሩል አርቀም

ማውጫ

አጀንዳ

መዳራጀት - የኢትዮጵያ ሙስሊም የወቅቱ አጀንዳ?



ገፅ 19 ተቅዋ የህይወት ሰንቅ

ገፅ 07 የውዴታ ማሰያ

ገፅ 21 ከሰኪታማ ወንድ ጎን ጠንካራ ሴት አለች

ገፅ 09 በመንፈሳዊነትና በአለማዊነት መካከል

ገፅ 15 ሚዛናዊ - አውቀት - ፍሀጋ - ለወጣቶች

ገፅ 23 ሀጅ ፣አለም አቀፍ ኮባዔ

ገፅ 16 የዘመን - መክዉጫ - ወይስ - ቅዱስ - ዮሐንስ - አደስ - ዓመት - ከኢትዮጵያዊ - የዘመን - መቁጠሪያነት - ባሻገር

ገፅ 13 ሀጅር የፅናት ተምሳሌት



ርዕስ አንቀጽ

በቅን ልቦና ከሆነ ጅምሩ ይቀጥል !

በየትኛውም የዘመን አቆጣጠር ይሰላ ጊዜ ተቀያይሮ ብዙ ለውጥን ያመጣል። በሰውኛ ዕሳቤ በጎም ክፉም ተብለው ሊወሰዱ የሚችሉ ወሳኝ ክንውኖች አላህ በፈቀደው መልኩ በጊዜ ውስጥ ይከወናሉ። ጊዜ ሁሉንም ነገር ያሳያል። "መኖር ደጉ" ብዙ ነገር አሳየን ይላሉ ብዙ ያዩት አበው። በግለሰብ ፣ በማህበረሰብ ፣ በመንግስት ፣ በሐገር እና በዓለማቀፍ ደረጃ ብዙ ነገሮች በቅርቡ ተቀይረዋል። የሰው ልጅ ስቃይ ጥግ ነክቶ ህጻናት ያለወንጀላቸው ሲሰደዱ ወንዝ ዳር ባፍጢማቸው ተደፍተዋል። ይህም የዓለምን ህዝብ ፣ የብዙኃኑን ልብ ያንቀሳቀሰ አጋጣሚ ሆኗል። የምዕራባውያንን ዓቋም የፈተነ ፣ የሚጠበቀውን ያህልም ቢሆን በህዝብ እና ሚዲያ ግፊት ማዘን የጀመሩ ይመስላል። ስደተኞችን ሊያስጠልሉ እየሞከሩ ነው ፤ ምንም ጥፋት ለሌለባቸው ንጹህ የዘመኑ ምንዱባን ምህረት አድርገው በሐገራቸው ድንበር ውስጥ እንዲኖሩ ሊያደርጉ ዓቅደዋል። ከፊሎቹ ደሴት ገዝተው እኒህን ተንገላች ምስኪኖች ሐገር ሊለግሷቸው ነይተዋል። ለነዚያ ሐገራቸውን የተነጠቁ ሐገር-ዓልባ የምድር ላይ እግረኛ እና የጀልባ ተጓጉች። ባንጻሩ ለዕድገት እና ለፈጠራ የተዘጋጀን ያንድ ፍሬ ልጅ እጅ በካቴና ቀፍድደዋል። ላገሩ እና ለወገኑ ቅን ያሰበ ታዳጊ በሽብር ተወንጅሎ ዘብጥያ ወርዷል። ይህ ሙስሊምን በድፍኑ የመጥላት እና የመጠራጠር በሽታ ዳግም የዓለም መገናኛ ብዙኃን መነጋገሪያ ሁኖ ውሎ አድሯል።

በሐገራችንም ዓውድ ስንመለከት በርካታ ክስተቶች ዓይን የሚስቡ መሆን ጀምረዋል። እንዳለማቀፍ ማህበረሰብ ሁሉ ከሰሞኑ ያገራችን መንግስት ጥቂት ንጹሃን ሙስሊሞችን በሰላም ባገራቸው እንዲኖሩ ነጻነታቸውን መልሶ አጎናጽፏል። ቀድሞውንም ላገር ሰላም እና የዲሞክራሲ ዕድገት የተጉ ንጹሃንን ነበር በኃይል ያጎረው። በማረሚያ ቤት የሚገራ ስብዕና ድሮም አልነበራቸውም። መታረም የሚያስፈልገው ባህሪ እና መጸጸት የሚያሻው አንዳች የጥፋት ድርጊት አልተስተዋለባቸውም። እንደ አሜሪካዊው ታዳጊ አህመድ ሙሐመድ ጥላቻ እና አጉል ስጋት በፈጠረው ፍርኃት ታፍሰው ታሰሩንጅ። ለማንኛውም ከዚህ ቀደም ከፊሉ የኮሚቴው አባላት ነጻ ተብለው እንደተሰናበቱት ሁሉ የነኝህም ከእስር መፈታት እሰየው የሚያስብል ጅምር ነው።

ነገር ግን ከጅምሩ ሳይታሰሩ የቀሩ የህዝብ ወኪሎች ፣ ተከላከሉ ሳይባሉ በነጻ የተሰናበቱት ፣ አሁን በምህረት ተለቀቁ የተባሉት እና በማረሚያ ቤት የቀሩት የኮሚቴው አባላት መካከል ምንም ልዩነት አልነበረም። ሁሉም ህጋዊ ጥያቄ ያነሳውን ህዝብ ወክለው ከመንግስት ዓካላት ጋር የተደራደሩ እንደራሴዎች ናቸው። ለሽማግሌ ደግሞ ይገዙለታል እንጅ አያስሩትም ፣ አይወሱትም። ሲዘመግል አልታረቅም ያሉትን ገላጋይ ይቅርታ ይጠይቁታል እንጅ አይወነጅሉትም። ባገራችን ተለምዶ ሽማግሌ ከሁለቱም ወገን ያለውን ጉዳይ ዓይቶ "አንተም ተው ፤ አንተም ተው፤" ብሎ ላንደኛው "ሌላኛው ጥፋቱን አምኗል ፣ ይቅር በለው " ሲል እንጅ ተሸምጋይ ዞሮ ሽማግሌውን ሲወነጅል እና ተጸጽቶ ምህረት ተደርጎለታል አይልም/አያስብልም። ነገር ግን ይህ ሆኗል እና ይሁን ብለን ብንቀበልም ፤ ካሁን በኋላ ላለው ጊዜ የምንመክረው በይግባኝም ሰሚ ችሎትም ሆነ ሌላ ያደኛኝ ስርዓት ቀሪዎቹን የኮሚቴ አባላት እና ወንድሞቻችንን በክብር ማሰናበቱ ይቀጥል የሚል ነው።

እዚህ ጋር ሳይጠቀስ የማይታለፈው ሌላው ነጥብ መንግስት ፈታኋቸው ያለን ሰዎች መለቀቅ የትግሉን ዓቅጣጫ አያስተውም ፤ መንግስት ከህዝበ ሙስሊሙ ጋር ያየገባበትን ግብግባዊ ውጥረት አያረግበውም ፤ ለመነሻ ጥያቄዎችም ምላሽ አያደርገውም። ከዚህ ቀደም ከማጎሪያዎች ተለቀው ወደ ህዝብ የተቀላቀሉ ወገኖቻችን መኖር ህዝቡን ወደ ቤቱ አላስገባውም ፤ ላራት ዓመታት ያነሳውን የፍትህ ጥም አልመለሰውም። እናም ይህ ጅምር ለዓራተኛው ጥያቄ አጥጋቢ ያልሆነ ከፊል ምላሽ ነው። የዚህ ጥያቄ መልስ የተሟላ እስካልሆነ ድረስ መንግስት ከጥያቄው ሙሉ ነጥብ አላገኘም። የሁሉንም ታሳሪዎችን ስም ዘርዝሮ መፍታት ፤ በመኃል አገር እና በክልል ያሉ የትግሉ አቀንቃኞችን ሁሉ ማሰናበት ግድ ይለዋል። መንግስት የወሰደው ውሳኔ ስያሜው ምህረትም ሆነ ሌላ በቅን እሳቤ የተወሰደ ካልሆነ ነገሮችን ከማወሳሰብ ያለፈ ትርፍ ለማንም አያስገኝም። ህዝባዊው ትግል ብዙ እርከኖችን አልፎ የማይቀለበስበት እዚህ ደረጃ ላይ ተደርሷል። ከጅምሩ ባንዳንድ የመንግስት ዓመራሮች ዕብሪተኛ እምቢተኝነት የተፈጸሙ ያቅጣጫ ስህተቶችን ካሁኑ መርምሮ ማረም ያስፈልጋል። መሰረታዊ ያስተሳሰብ እና የዓቅጣጫ ለውጥ ካልተደረገ ፤ በቅንጥብጣቢ የመፍትሄ ኃሳቦች ብቻ ጉዳያችን ፍጻሜ አያገኝም። ይህን መንግስትም የተረዳ ይመስለናል። ጥያቄው ስር የሰደዱ መሰረታዊ የተቋም ችግሮችን መንቀል ነበር ፤ ነገር ግን መንግስት በሙስሊሙ ብቸኛ ተቋም በሆነው መጅሊስ ውስጥ ያለውን መርዘኛ እሾህ ከመቅጠፍ ይልቅ ፤ በቀበሌ መንጅሊስ ምርጫ በዘራው ዓረም ሊሸፍነው ሞከረ። ያልተሳካ ሙከራ ነበርና ትግሉን ወደ ሁለንተናዊ ሙበት ማስከበር አሸጋገረው።

አሁንም ቢሆን መንግስት የበየነው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ያስተላለፈው ቅጣት ህዝበ ሙስሊሙን ለቁጭት ዳርጎታል። ባልተለመደ እና በተደራጀ መልኩ ተጽዕኖ በሚፈጥሩ ሰላማዊ ተቃውሞች መንግስት ላይ ጣቱን እየሰነዘረ ነው። እያንዳንዷ የመንግስት ግፊት ትግሉን ወደ ቀጣዩ እርከን የማሸጋጋር ሚና ብቻ ሲኖረው ታይቷል። ስለዚህም ፖለቲካዊ ጨዋታው ቀርቶ ለሐገር ጥቅም እና ለህዝብ ደህንነት እንዲሁም ለዜጎች ክብር የሚመጥኑ ውሳኔዎች በቀጣይነት ይጠበቃሉ። በቅርቡ በሁሉም ቦታዎች የታገቱ ቀሪ ንጹኃንን ማሰናበት ህዝበ ሙስሊሙ ከመንግስት የሚጠብቀው አስቸኳይ የቤት ስራው ነው።

መደራጀት - የኢትዮጵያ መሰረም የወቅቱ አጀንዳ?

በ''የሱፍ ኻሊድ''

ተቋማዊነታችን ከታሪካዊ እና ወቅታዊ ነባራዊ ሁኔታዎች አንፃር ሲቃኝ

ከ1400 ዓመታት በላይ ያስቆጠረውን ረጅሙን የእስልምና እና ኢትዮጵያ የግንኙነት ታሪክ ትተን የባለፈውን 100 ዓመት ታሪክ ብቻ እንኳን ብንመለከት የኢትዮጵያ ሙስሊም ከማህበረ-ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ መስተጋብሮች እና ሁነቶች እንዴት ስልታዊ በሆነ ሁኔታ ሲገፋ እንደኖረ፣ ዛሬም እንዴት እየተገፋ እንደሆነ መገንዘብ እንችላለን። በየዘመናቱ የተተካኩት አገዛዞች የተማረ ፤ ማንነቱንና ታሪኩን ጠንቅቆ የሚያውቅና እና በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የበኩሉን አስተዋፅዖ ማድረግ የሚችል አሰላሳይ ሙስሊም ግለሰብም ሆነ ማህበረሰብ እንዳይፈጠር ሌት ተቀን ተግተው በመስራታቸው እነሆ ዳፋው ለዚህኛው ትውልድም ተርፎታል። በባለፉት 100 ዓመታት በሀገሪቱ ላይ በትረ-ስልጣኑን የጨበጡ ገዥዎች በአጠቃላይ - የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እና የኢህአዴግ አገዛዞች በተለይ - ሙስሊሙ ማህበረሰብ የራሱ አጀንዳ የሌለው ፤ እሴትም እና የታሪክ አሻራ የሌለው ማህበረሰብ እንዲሆን ተግተው ሰርተዋል ፤ ዛሬም በመስራት ላይ ይገኛሉ። በተለይ የንጉሱ አገዛዝ ሙሉ በሙሉ ራሱን ሐይማኖታዊ መንግስት አድርጎ የሰየመ በመሆኑ የተነሳ ከተቻለ ሙሉ በሙሉ እስልምናንና ሙስሊሙን ከሀገሪቱ ማጥፋት ፤ ካልተቻለም ''ስንኩል ሙስሊም''ን የመፍጠር ምኞትን አዝለው

በባለፉት 100 ዓመታት በሀገሪቱ ላይ በትረ-ስልጣኑን የጨበጡ ገዥዎች በአጠቃላይ - የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እና የኢህአዴግ አገዛዞች በተለይ - ሙስሊሙ ማህበረሰብ የራሱ አጀንዳ የሌለው ፤ እሴትም እና የታሪክ አሻራ የሌለው ማህበረሰብ እንዲሆን ተግተው ሰርተዋል

ተንቀሳቅሰዋል። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እ.ኤ.አ በ1949 ዓ.ል አሜሪካን በመጎብኘት ላይ እንዳሉ በአሜሪካ ኮንግረስ ምክር ቤት ባደረጉት ንግግር ላይ "በሀገሬ ኢትዮጵያ በየአውራጃው እና ወረዳው ጥቂት እስላሞች ተበታትነው ይገኛሉ። ከወዳጅ ሀገሮች በቂ እርዳታ ካገኘሁ ፤ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ለማጥፋት እችላለሁ፤" ሲሉ ንግግር አድርገው ነበር። ይሄ የንጉሱ ንግግር ከሌሎች ታሪካዊ ሁነቶች ጋር- በተለይ ዘመናትን ተሻግሮ እዚህ የደረሰውን የአፋር-ዒሳ የጎሳ ግጭት- ደምረን ብንመለከተው የሚሰጠን ምስል የንጉሱ እስልምናን የማጥፋት ፍላጎት ምን ያህል ጣራ እንደነካ የሚያስገነዘበን ነው። ንጉሰ ነገስቱ ''ሀይማኖት የግል ነው ፣ ሀገር የጋራ ነው'' የሚል መፈክርን በአደባባይ ቢያስተጋቡም እስልምናንም ሆነ እስልምና የግል እምነቱ ብሎ በጋራ አገሩ ላይ ሊኖር ያሰበ ሙስሊም ኢትዮጵያዊ ከጠላት ጋር አብረው ሊያጠፉት መቋመጣቸውን ባለም መድረክ ዘርግፈዋል ፤ ባገር ውስጥ ያለው ዙፋን ያባውን ያሜሪካ ምክር ቤት ያስወጣዋል እንዲሉ። ከሰሜን ቀይ ባህር ፣ ከምዕራብ በሱዳን ድንበር አድርጎ ፣ በመንዝ ተራራ ስር አልፎ እስከ ኬንያ በሚደርሰው ረባዳና ቆላማ ምድር ላይ ሰፍሮ የሚኖረው በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ በሙሉ እስላም ነው። ይህ ህዝብ መገደሉ እና በተሸረበለት እርስ በርስ የማፋጀት ሴራ

መጋደሉ ቀርቶ ሰላም ቢሆን ፤ "ዘላን" መሆኑ ቢቀር እና ባንድ ቦታ አረፍ ብሎ እንደሌላው እኩል ቢማርና ቀለም ቢቀምስ እርስ በርሱ አንድነት እየፈጠረ በዙሪያው ካሉት እስላም አገሮች ጋር ግንኙነት ያደርጋል ፤ ክርስቲያን ለሆኑት ነገስታትና "የክርስቲያን ደሴት" ነች ብለው ለሚያስቧት ኢትዮጵያም እጅግ አደገኛ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል። ይህ ክፉ ጥርጣሬ አሁንም ድረስ በርካቶች ጋር ይኖራል። የገዥው መንግስትም ወቅታዊ ጸረ ሙስሊም ፖሊሲዎች የተቃኙት በመሰል አሉባልታዊ ድምዳሜዎች ነው። ለዚህም የንጉሱ እና የዘመናቸው ዓይነት ዕሳቤን ያነገቡ አንዳንድ "ጸሃፊዎች" ድርሻ እንዳላቸው በገሃድ ይናገራሉ። ይህ መጋኛ ዕሳቤ ተጠናውቷቸውም ነበር ንጉሱ "እንዲሁ እየተጋደሉ ፤ ሳይማሩና ተከፋፍለው በዘላንነት ብቻ ግብር እየከፈሉ እንዲኖሩ..."2 የሚል ስውር አዋጅ እስከ መደንገግ የደረሰ ሸፍጥን ሲፈፅሙ የኖሩት! ንጉሠ ነገሥቱ በተለይ በኢትዮጵያ ሙስሊም ላይ ከፈፀሙት ግፍ ሁሉ የከፋው የትምህርት ዕድልን በመንፈግ ለዘመናት ኋላ ቀር እና የስልጣኔ ጭራ እንዲሆን ማድረግን ነው። በዋናነትም ዓለማዊ ትምህርትን ከቤተ-ክህነት ትምህርት ጋር በመቀላቀል ፤ ትምህርት የሚዘጋባቸው ቀናትን የክርስትና በዓል ቀናት ብቻ በማድረግ ወዘተ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ወይ ከትምህርት ወይ ከሀማይኖቱ እንዲሆን በማድረግ አጣብቂኝ ፈተና ውስጥ ጥለውታል ፤ ከዚህም ባለፈ ኢስላማዊ ት/ቤቶችን (መድረሳዎችን) እና የመማማሪያ ስብስቦች (ሀለቃዎችን) ሳይቀር በትምህርት ሚ/ር የቁጥጥር ስርዓት ስር እንዲወድቁ በማድረግ ሳንሱር እያደረጉ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ያልነቃ እና ኋላ ቀር እንዲሆን ስልታዊ ተግባራት አከናውነዋል። ከዚህም በከፋ ሁኔታ በሀገር ውስጥ የመማር ዕድል የተነፈጉ ሙስሊሞች በውጭ ሀገራት የሚገኙ የትምህርት ዕድሎችን እንዳይጠቀሙ ፓስፖርትእና የይለፍ ወረቀት ከመከልከል አንስቶ "የእስላም ልጅ በውጭ ሀገር ሄዶ መማር ቀርቶ በሀገር ውስጥ እንኳን እንዳይማር"3 ተብሎ ለመኳንንቱ እና መሳፍንቱ መመሪያ እስከማውረድ ሲደርሱ ይሄንን መመሪያ ተቋቁመው ያለ ምንም ዜግነትን የሚገልፅ ማስረጃ በውጭ ሀገራት እንግልትና መከራ እንዲጋፈጡ በማድረግ ታሪክ በማይሽረው መልኩ ደባ ተፈፅሟል።

ኃይለሥላሲያዊ ውርስ ወይስ ዮሐንሳዊ?

ይሄው ደባ ዛሬም ቀጥሏል! የአፄ ዮሃንስ የልጅ ልጆች ፤ የኃይለ ስላሴ መንግስት የመንፈስ ወራሾች ሆነው ለሙስሊሙ ማህበረሰብ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ላይም "ወይ ከትምህርቱ ፣ ወይ ከሀይማኖቱ" የሚል መመሪያን አውርደው በርካታ ዜጎችን ችግር ላይ ጥለዋል። በየትምህርት ተቋማት ዛሬም ሂጃብ ተገፈፈ ፤ ተማሪዎች እንዳይሰግዱ ተከለከሉ ፤ ሙስሊም ተማሪዎች ሀላል ያልሆነ ስጋ እንዲበሉ ተደረገ ፤ ወዘተ የሚሉ አሳዛኝ ዜናዎች ለጆሯችን መድረስ ቀጥለዋል። አገዛዙ ምንም እንኳን በህገ-መንግስት መሰረት ላይ የቆመ ፣ ሀይማኖት እና መንግስትም የተለያዩ ናቸው4 ብሎ ቢያውጅም ዛሬም በሀይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ብያኔ ሰጪ ሆኖ እንደ መዘያየር እና ዚክር ማድረግን የሚከለክል ደንብ በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ተግባራዊ በማድረግ ሙስሊም ተማሪዎች እንደ አፄው ዘመን ሁሉ ዛሬም በመማር እና ሀይማኖታዊ ማንነትን በመጠበቅ መካከል አጣብቂኝ ውስጥ ወድቀዋል። ይሄው የትምህርት ሚኒስቴር ደንብ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ተፈፃሚ ሲደረግ በርካታ ተማሪዎች ትምህርታቸውን አቋርጠው ወደ ትውልድ ቀያቸው እንዲመለሱ ማድረጉ የትላንት ትውስታችን ነው። በንጉሱ ዘመን ፊታውራሪነት የተጀመረው የአፋር-ዒሳ ግጭት እነሆ ዛሬም በ21ኛው ክፈለ ዘመን ተባብሶ ቀጥላል ፤ ስርዓቱም ሁሉቱን ጎሳዎች አስታርቆ እና የደም መፋሰሱን አስቁሞ ወደ ልማት ከመመለስ ይልቅ ዱላ አቀባይ ሆኖ ዛሬም ቆሞ ይመለከታል። የኢትዮጵያ ሙስሊም ታሪክ ከትላንት እስከ ዛሬ እንዲህ በመከራ ፤ በተንኮል እና በትንቅንቅ እንደታጀበ ይሄው እስከ አሁን ቀጥሏል! ይሄ ሁሉ እየተፈፀመብን ያለው ምን ተፈልጎ ነው? ሙስሊሙ ማህበረሰብስ ምን ስለጎደለው ነው? ብሎ መጠየቅ የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ይመስለኛል። መልሱ ለሁለቱም አንድ ነው።

የሙስሊሙ የተቋም ጥም

በየዘመኑ የነገሱ አገዛዞች የበደል በትራቸውን የሚሳርፉት በመጀሪያ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ድርጅት አልባ ስለሆነ ነው። ጥላ ከላለ የሚሆን ፤ ታሪክን ሰንዶ የሚያስቀመጥ ፤ ለወቅታዊ ነባራዊ ሁኔታዎች ትንተና ሰርቶ ስትራቴጂዎችን የሚነድፍ እና የሙስሊሙን ማህበረሰብ ጥቅም የሚያስከብሩ ድርጅቶችን መመስረት ባለመቻሉ ነው ፤ ለዘመናት የአምባገነኖች የበደል በትር ሰለባ እየሆነ ያለው። በየዘመናቱ የሚመጡ መሪዎች ታሪኩን እንደፈለጉ የሚበርዙበት ፤ በሀገሪቱ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የራሱ አጀንዳ የሌለው እና በአጠቃላይ "የመብት ተመፅዋች" እንዲሆን ማድረግ ነው ዋና ዓላማቸው ፤ እያደረጉትም ይገኛሉ። እዚህ ላይ አንድ ታሪካዊ ሁነት ማንሳት ለአባባሉ ተገቢ አስረጂ ይመስለኛል፦ ጉዳዮ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እና በወቅቱ የሳዑዲ ንጉሥ በነበሩት ንጉሥ ፈይሠል መካከል የተደረገ ንግግር ነበር። በወቅቱ ሁለቱ መሪዎች ካይሮ ላይ በተካሄደው የገለልተኛ መንግስታት ጉባዔ ላይ ተገናኝተው በነበረበት ወቅት የተናጠል ውይይት ያደርጋሉ። በውይይቱም ንጉሥ ፈይሠል 'በኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ላይ ስለሚደርሰው የሀይማኖት ጭቆና እና መስጂድ መስራት እንዳይችሉ እንኳን መሬት እየተከለከሉ' መሆኑን ለአፄ ሀይለስ ስላሴ በቅሬታ መልክ ያቀርባሉ። ንጉሥ ኃይለ ሥላሴም የሰጡት ምላሽ ተፈላጊውን መሬት እንሰጣለን ፤ እናንተ መጥታችሁ መስጊዱን ራሳችሁ ስሩላቸው የሚል ነበር። ነገር ግን ምላሻቸው ወደ መሬት ወርዶ ተፈፃሚ ሊሆን አልቻለም። "የሚሰሰራው መስጊድና ክሊኒክ ለሳዑዲው ንጉስ ፈይሰል ቋሚ ውለታ መስሎ ከመታየትም በላይ ፤ ለእስላሞች የሞራል ጥንካሬና "የውጭ ረዳት አለን!" የሚል ስሜት

ሊያሳድርባቸው ይችላል”5 በሚል ምክንያት መስጂዱም ሆነ ክሊኒኩ እንደታሰበው ሳይገነቡ ቀርተዋል። ይሄ ታሪካዊ ሁነት የንጉሱ አገዛዝ የኢትዮጵያ ሙስሊም ምን ያህል ተቋም አልባ እንዲሆን ይሰራ እንደነበረ እና ሙስሊሙም ተቋም አልባ በመሆኑ ምን ያህል ውርደትን ለዘመናት ሲሸከም እንደኖረ የሚያስገነዘብን ይመስለኛል። ወደ ዘመናችን ብንመጣም ሁነቱ ተመሳሳይ ነው (ይሄንን ፅሁፍ በማዘጋጅበት ወቅት እንኳን የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር አንዳንድ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሀይማኖት አክራሪነትን ለማስፋፋት እንየተንቀሳቀሱ ነው ሲል አስታወቀ የሚል ዜና እየሰማሁ ነበር። ያው ያሉትን ድርጅቶች ሊበሉ እያመቻቻቸው መሆኑ ገባኝ)።

የተቋም ንፍጊያ እና መንግስታዊው የተቋም ኃሳብ ዝርፊያ

ከ1983 ዓ.ል ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የኢትዮያ ሙሊም እንዳይደራጅ ፤ የጋራ የማንነት መለያዎችን እንዳያጎለብትና ሁሌም ቢሆን ለጥቅም ብቻ ሲፈለግ የሚገኝ እና ከአገልግሎት በኋላ የሚጣል ማህበረሰብ እንዲሆን ይሄ መንግስት ምን ሲሰራ እንደኖረ መገንዘብ ተገቢ ነው። ሀሳቤን እንዲያስረዳልኝ ሶስት አበይት ምሳሌዎችን እጠቅሳለሁ፡- ሁሉም ከባንክ አሰራሮች ጋር የተገናኙ ናቸው።የመጀመሪያው ከዘምዘም ባንክ ጋር ያለውን ነገር እጠቅሳለሁ። የዘምዘም ባንክ ህጋዊ ሰውነት ተሰጥቶት ፤ የምስረታ ጎባዔ ካካሄደ እና አክሲዮን መሸጥ ከጀመረ በኋላ ለምን ተከለከለ? ከዘምዘም ባንክ በኋላ ለባንክ መመስረቻ በብሄራዊ ባንክ ተቀማጭ የሚደረገው ማስያዣ ከ70 ሚሊዮን ብር ወደ 500(?) ሚሊዮን ብር ለምን እንዲድግ ተደረገ? ከዚያ በኋላ የፋይናንሻል ኢንተለጀንስ ኤጀንሲ ለምን ተቋቋመ? መልሱ ቀላል ነው። ሙስሊሙ ማህበረሰብ አንድ ጠንካራ የፋይናንስ ተቋም መገንባት ከቻለ ፤ ከወለድ አሰራር እና ተቋማዊ ጥገኝነት ነፃ የሚወጣበትን መንገድ ጀመረ ማለት ነው። ይሄ ደግሞ ሙስሊሙ ሊነቃ ነው ማለት ነው ፤ ከነቃ ደግሞ መብቱን ጠያቂ እንጂ ተመፅዋች ሊሆን አይችልም። ስለዚህ እንደፈለጉ ለመቆጣጠር ይቻል ዘንድ ምኞቹን ከጉቱ በማድረግ ተስፋ ማስቆረጥን አልመው ባንኩ እንዳመሰረት አገዱ። ያ ሲሆን በእነርሱ መዳፍ ስር እንደወደቅን እንቀጥላለን ማለት ነው። ሌላው ከአባይ ግድብ ጋር በተያያዘ ያለው እውነታ ነው። የግድቡ መጀመር እስኪነገር ድረስ የትኛውም ባንክ ‹ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት› አልጀመረም ነበር። ነገር ግን የግድቡ የቦንድ ሽያጭ ሲጀመር ከወለድ ነፃ የቦንድ ሽያጭ ብለው መጡ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንኳን ሳያፍር በፓርላማ ፊት ቀርቦ “የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ ዜጎችን በስፋት ለማሳተፍ ነው፤” አለ። ይኼው ነው ለጥቅም ሲሉ እኛን እንዴት እንደሚፈልጉን የሚያሳይ እውነት። እኛ ከወለድ ነፃ አገልግሎትን ስንጠይቅ የምንከለከለው ነገር እነርሱ ሲፈልጉት ፤ እና ለጥቅማቸው የምናስፈልግ ሲሆን ግን በራሳቸው መንገድና ጊዜ ያደርጉታል። ከዚያ ደግሞ እንደ ሸንኮራ መጥጠው ይጥሉናል። ሶስተኛው ሀሳብ ከመጀመሪያው ጋር የተያያዘ ነው። የዘምዘም ባንክ አደራጆች ያቀረቡትን ምክረ-ሀሳብ (proposal) ብሄራዊ ባንክ ነጥቆ ለሌሎች ባንኮች ሰጠ። ”ወለድ አልባ የሚባል የባንክ አሰራር ስርዓት በሀገሪቱ አይፈቀድም፤” ብለው እኛን ከሸኙ በኋላ ፤ ይሄው ዛሬ ሁሉም ባንኮች በየሚዲያው ያደነቁሩናል። ተመልሰን “እኛም ወለድ ዓልባ ባንክ ይፈቀድልን እና እንስራ” ብለን ብንሄድ ግን “ባሉት ባንኮች ተጠቀሙ እንጂ ሌላ ባንክ ለምን አስፈለጋችሁ?” ይሉናል። ምክንያቱም በኢኮኖሚው ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ዓላማ ዙሪያ



ተደራጅተህ የምትመራው የራስህ ተቋም እንዲኖርህ አይፈለግም። እኩል መብት በገቢር ኖሮህ በተመጣጣኝ ደረጃ የመብት ተጠቃሚነትህ እንዲረጋገጥ ማንም አይሻም። ታዲያ ይሄ ትልቅ አልቦ-ተቋም የማድረግ ዘመቻ አይደለምን? ሌላም ምሳሌ መጥቀስ እንችላለን። በባሌ ሮቤ ሊቋቋም የነበረው ኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲ ቦታ ከተሰጠው በኋላ ለምን ግንባታው እንዳይጀመር ተፈለገ? ለምን የአወሊያ ኮሌጅ አረብኛ የትምህርት ክፍል ተመርጦ የበትሩ ሰለባ ተደረገ? ለምን በየመንደሩ ቂርዓት የሚያቀሩ መሻኢኾች ዒላማ ተደረጉ? መልሱ ያው ከላይ ተጠቅሶ የነበረው ነው። ማህበረሰቡ አልቦ ተቋም እንደሆነ እንዲቀጥል ለማድረግ። በንጉሱ ዘመንም ሆነ አሁን አይሁዳዊ እጆች ከሴራው ሁሉ በስተጀርባ መኖራቸውን መገንዘብ እንችላለን!

ቢያንስ ለነጋችን ስንል ምን እንስራ? ከላይ እንደተጠቀሰው በየዘመናቱ የመጡ መሪዎች ሁሉ እንዳሻቸው የሚያደርጉን ተቋም ስሌለን ነው። ተቋም ስለሌለን ታሪክ ፣ ኢኮኖሚም ሆነ ፖለቲካ የለንም ፤ እነርሱ ግን አላቸው። ትላንት በእጃቸው ስለነበረ ዛሬን በእጃቸው አድርገዋል። ስለዚህ ነገንም እነርሱ ይወስኑልናል ማለት ነው። እንግሊዛዊው ደራሲ ጆርጅ ኦርዌል እንዲህ ይላል:

"Who controls the past, controls the future: who controls the present controls the past. And yet the past, though of its nature alterable, never had been altered.... It was quite simple. All that was needed was an un ending series of victories over your own memory. 'Reality control' they call it." 6

ያለፈውን ታሪክ በቁጥጥሩ ስር ማድረግ የቻለ ፣ መፃኢውን ይቆጣጠራል ፤ ዛሬን የተቆጣጠረ ፣ ያለፈውን ታሪክ ይቆጣጠራል። ያለፈ ታሪክን መሰረዝ እና መደለዝ ከባድ ከመሆኑ ጋር እንዳልነበር ሆኖ ይበረዛል ፤... ያንን ያህል ቀላል ነው ፤ የሚያስፈልገው ነገር በአንተ/አንቺ/እናንተ አዕምሮ ላይ የሚያቋርጥ የበላይነትን መጎናፀፍ ነው። ይህንም "ኑነት ‹ተጨባጩን እውነታ መቆጣጠር› ይሉታል። ያለፉትም ሆነ የዘመኑ አገዛዞች እስልምና እና ሙስሊሞችን በተመለከተ በዚህ መርህ ነው የሚመሩት። ዛሬን በእጃቸው ስላስገቡ ትላንትን ተቀጣጥረዋል ፤ ታሪክን እንደፈለጋቸው በርዘዋል። ቴዎድሮስን የሀገር አንድነት አባት ያደረገ ታሪክ ፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ እንዲሁም ከሰሜን እስከ ደቡብ ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ አድርጎ የገዛውን ኢማሙ አህመድን ወራሪ አድርጓል። ምኒሊክን እምዬ ለማለት የደፈረ ታሪክ ብዝሃነትን የተቀበለውን ከአብራካቸው ክፋይ የተወለደውን ልጅ እያሱን ክዷል። የኢትዮጵያ ሙስሊም ይሄ ሁሉ የደረሰበት መደራጀት ፣ መሰባሰብ እና የራሱ የሆኑ ተቋማት መገንባት ስላልቻለ ነው። የራሱ የሆነ የታሪክ መዘገቢያ ወይም አጣርቶ መመዝገቢያ ተቋም ስለሌው ታሪኩ እየተዛባ ይነገራል። መብቱን የሚያስከብርለት የፖለቲካ ተቋም ወይም የመብት ተቅርቋሪ ድርጅት ስለሌለን በሁሉም መስክ መብታችን እንዳይከበር ይደረጋል። አለሁ ባይ ተቋም ስለሌለው የዘርፈ ብዙ ጭቆና ሰለባ ሆኗል ፤ ተቋም ስለሌለው አሁንም ሆነ ወደፊት እንዳዲስ ተቋም እንዳይኖረው ገዥ መንግስታት አበክረው ይሰራሉ! መፍትሄው ያለው ተቋማዊነት እና ተቋማቂ አሰራር ላይ ነው። እነዚህን ተቋማት ማደራጀት ሲችል ሙስሊሙ ማህበረሰብ ችግሮቹን መቅረፍ ፤ በሀገሪቱ ላይም ተፅዕኖ ማሳደር ይጀምራል። የማህበረሰብ ሳይንስ ባለሙያዎች አንድ ማህበረሰብ እንደ ህብረተሰብ የሚቆጠረው እና ለውጥ/ዕድገት ማስመዝገብ የሚችለው አምስት የማህበረሰብ ተቋማት(Social Institutions) ማለትም ቤተሰብ፤ ትምህርት ፤ ኢኮሚሚያዊ፤ ሀይማኖታዊ እና ፖለቲካዎ ተቋማትን መገንባት ሲችል እንደሆነ ያስረዳሉ። በዘመናችን ማህበረሰብ ውስጥ ደግሞ የጤና እና የሚዲያ ተቋማትም ሚና እና አስፈልጎት አሌ የማይባል ነው። እነዚህን ተቋማት በጠንካራ መሰረት ላይ መገንባት የቻለ ማህበረሰብ ህልውናውን ማስከበር ይችላል። እነዚህ የሌሉት ማህበረሰብ ግን ራሱንም ሆነ ተከታታይ ትውልዶችን ከአፈናና ጭቆና ነፃ ሊያወጣ አይችልም። የዚህ ትውልድ አባል የሆንን ኢትዮጵያውን ሙስሊሞችም ሆነ መጪው ትውልድ በሀገሪቱ ላይ አሻራ የማሳረፍ እና ለዘመናት ከመጣንበት አብላጫ ከመሆን ጋር ያለውን በታችነት አዙሪታዊ ክበብ (vicious circle) ሰብረን የመውጣት እጣ ፈንታችን እነዚህን ተቋማት በመገንባት ላይ የተንጠላጠለ ነው። እነዚህን ተቋማት ለመገንባት መደራጀት ፤ የእዝ ሰንሰለት ያለው መዋቅር መዘርጋት እና ሁላችንም በየሙያችን ላይ ሰፔሻላይዝ ማድረግ (መጠበብ እና መላቅ) ይጠበቅብናል። አሁን ያለብንን ወቅታዊ ችግር ለመፍታትም ሆነ ለረጅም ጊዜ ችግሮች መፍትሄ ማበጀት የምንችለው መደራጀች ስንችል እና ተቋማትን መገንባት ስንችል ብቻ ነው። እስቲ አሁን ያለውን ነበራዊ ሁኔታ እንመልከት፤ ያለብንን የመብት ጥሰት በውል ተረድቶ ጥያቄያችንን አንግቦ ፤ ወደ አንድ ዓላማ ሊያሰባስበን የሚችል እና ህገ-መንግስታዊ ጥያቄዎቻችን እስከሚመለሱ ድረስ አንድ አድርጎ ሊያታግል የሚችል ድርጅት አለን? ያለን አይመስለኝም። መቼም ድምፃችን ይሰማ ድርጅት ነው የሚል ሰው ያለም አይመስለኝም ፤ ድምፃችን ይሰማ ወቅታዊ ችግሮችን መፍትሄ ለማስገኘት በህብረተሰቡ የተፈጠረ ጊዜያዊ አመቻማች (Liaison group) እንጂ ድርጅ አይደለም። ድርጅት ለመሆን ከአንድ ማዕከላዊ አመራር (Core leadership) ወይም በተዋረድ ካሉ ያልተማከለ አመራር የሚወርድ ፣ የእዝ ሰንሰለት (Chain of command) እና የግንኙነት አግባቦችን (communication channel)፣ ሚዲያ ፣ ጠንከራ የፋይናንስ ዓቅም ወዘተ. ማሟላት ይጠቅበታል። ስለዚህ ድርጅቶችን- የማህበራዊ ተቋማትን- ወደ መፍጠር መትጋት ይኖርብናል። ድርጅቶችን ስንፈጥር በሀገር ደረጃ ተሰሚነት ያለን ዜጎች ፤ ፍትሃዊ ውክልና ያለን እና ጥቅማችንን ማስጠበቅ የምንችል ህብረተሰብ መሆን እንችላለን! ያንን እስከምናደርግ ግን በገዥዎቻችን የብረት ጫማ ስር መቆየት ዕጣ ፈንታችን ይሆናል።

ምንጮች

1 ሀጅ በሺር ዳውድ፣ በሕይወቴ ሂደት ዙሪያ፣ መጋቢት 2003፣ ገፅ 41

2 እዚያው፣ ገፅ 38

3 እዚያው፣ ገፅ 38


4 የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት፣ አንቀፅ 11

5 አብደላ አብዱረህማን ኑር፣ የዓይን ምስክር፣ ገፅ 76

6 George orwell, 1984, 1949 P 30

የሙሄታ ሣህያ

የመንፈስ እዳሴ ከመለኮታዊው ምንጭ በሚቀዱ የፅድቅ አስተምህሮቶች መንፈሰዊነትን በማደስ የተሻለ ኢስላማዊ ስብዕናን ለመገንባት የሚያግዙ መጣጥፎችን ያስተናግዳል



(ሰዒድ ካሚል)

ኡመር ኢብኑል ሃጧብ (ረ.ዐ) ልጃቸው አብደላህ ኢብኑ ኡመር አባቴ ሆይ ከረሱሉ ጋር ካሳለፍካቸው አስደሳች የህይወት ጊዜያቶች ሁሉ መቸም የማትረሳውን አስታውሰኝ ሲሉ ለጠየቋቸው ሲመልሱ «ለኡምራ ሳስፈፈቅዳቸው 'አንተ ኡመር ሆይ በመልካም ዱዓህ አትረሳን 'ያሉኝን መቸም አልረሳም» ማለታቸውን ስታስታውሰ... የሃበሻዊነት ኩራትህ ቢላል ኢብኑ ራባህ ከሙስጦፋ(ሰ.ዐ.ወ.ዐ ህልፈት በኃላ ክብር እና ልዕልና የተጎናጸፉባትን መዲነተል ሙነዎራ ሃቢቢን እንዳታስታውሳቸው አቀርቅረው ሲሰናበቷት ፣ አሊይ ኢብኑ አቡጧሊብ መልዕክተኛውን ሲያሳድጁቸው ስለረሱሉ ሊሰው እሳቸውን ተክተው ፍራሻቸው ላይ ለፍቅራቸው መስዋዕትነት ሊከፍሉ ካሳለፉት አስገራሚ ለሊት ስለሆኑላቸው ከሆኑት በላይ መልዕክተኛው ስለእንተ መንገድ ላይ ቁጭ ብለው አፈር እየጫሩ አንገታቸውን አቀርቅረው "እኔስ ወንድሞቸ ናፈቁኝ.'.ስሃቦችም 'ያረሱለላህ እኛ ወንድሞችዎ አይደለንም እንዴ ሲሏቸው ‹እናንተማ ባለደረቦቸ ናቸሁ ወንድዎቸ ግን እነሱ እነዚያ ናቸው እኔን በአካል ሳያዩ የሚያምኑብኝ..."ያሉት ለእንተ ምን ስሜት ፈጥሮብሃል ? ዛሬ ላይ ሁነህ በታሪክ አምድ 1400 አመት ወደ ኃላ አጠንጥንና አስባቸው .....ከመፈጠረህ በፊት የናፈቁህን አዛኝ ነብይ ¨ትናፍቃለህን ?እሳቸው እኮ የናፈቁህ አማኝ ጠፍቶ ሳይሆን ከዚያ ምድር ከተገረመችበት ምረጥ ትውልድ መሃከል ሁነው ነው ያስታወሱህ ፤ አላህ ሱበሃነሁ ወተአላ ሳይቀር 'አላህ ከእነርሱ ወደደ እነርሱም ከእርሱ ወደዱ' ካላቸው ሰሃቦች መሃከል ሆነው የናፈቅሃቸው ወንድም አንተ ነህ ፣በትካዜ መሬት አስጭረሽ በትዝታ አምድ ያን ያህል ዘመን አምጥተሽ ያሳሰብሻቸው... እህት አንች ነሽ ወደ ሌላ ሰው አትመልከች አንች ራስሽ ነሽ ... ሳያዩኝ ያመኑብኝ

ያሉት ወንድሞቸ ናፈቁኝ
ሃቢቡና እንዴት ነበር
ሁበይብ እያለ ባ'ገር
እኔ ሰላም ላይ ሁኜ እሾህ ወጋ'ቸውን ከመስማት
አመረጣለሁኝ ሞቴን ፣ ፊዳ መሆን መስ'ዋት
እያላቸው ፍቅር ወግዶት
....
ሁሉም ሲከድ እውነት ያለው
ዱንያ ውለታውን ያልከፈለች
እያለ ሲዲቅ ጓደኛው
አ-ቡ-በ-ክ-ር

ሳይለብሱ አፈር

ከዘመናቸው እልፍ አመታት ተሻግረው
ኡመቲ.. ኡመቲ..ኡመቲ አሉ ናፍቀው
....
አላውቅም በምድር
ምን እናዳለ ታአምር
ተናፋቂ ናፍቆ ናፍቆት ሲያጣ ፍቅር

አዎ ፀረ ረሱል ካርቶኖችና ፊልሞች በዴንማረክና በሆላንድ በቅረቡ ደግሞ በፈረንሳይ ሲሰሩ ያ ስነ-መግባሩ የሚራመድ ቁርአን፣ ያ ምድር እንደሱ አይነት ፍቅር እና እዝነት ቀድማም ደግማም ልታይ ያልቻለችውንና -የማትችለውንም የአላህ አገልጋይ በጭፍን የሚያጥላሉ ------መጽሃፍቶች ሲታተሙ ያን ያህል ገጾች ሲከተቡ አንተ እና አኔ የትኛው ጥግ ላይ ነበርን ? አስታውስ ይህ እየሆነ ያለው ደግሞ በእኔ እና አንተ ዘመን እንጂ በእረሳቸው ጊዜማ የወቅቱ ገናና የሮማው ንጉስ ሂረቅል ሳይቀር የእሳቸው አገልጋይነትን ተመኝቷል። ከአቡሱፍን ጋር ባደረጉት ቃለ- ምልልስ "...ስለ ዘሩ ሰጠይቅህ ከተከበር ዘር መሆኑን ነግረህኛል መልዕክተኞችም የሚነሱት ከተከበረ ዘር መሃከል ነው፡...ኑብይ ነኝ ከማለቱ በፊት በውሸታምነት ታውቁት እንደነበር ስጠይቅህ እውነተኛ መሆኑን ገልጸህኛል ፤በሰው ላይ ለመዋሸት ያልደፈረ በአላህ ላይ አይዋሸም...ምን እነደሚያዛችሁ ጠይቄህ አላህን በብቸኝነት እንድታመልኩና ከእረሱ ጋር ሌላን አካል እንዳታጋሩ እንደሚያዛችሁ ፣ጣኦት አምልኮን እንደሚከለክላችሁ... ገልጸህልኛል፡፡የተናገረከው እውነት ከሆነ ይህ ሰው እግሮቹ የረገጡትን ምድር ይቆጣጠራል፡፡..እንደማገኘው ባውቅ ኖሮ እረሱን ለማግኘት ሁሉንም አይነት ጥረት አደረግ ነበር፡ ፡አብሬ ብሆን ደግሞ እግሮቹን አጥብ ነበር፡፡"3በምጡቁ ስርአታቸው ተማረኮ ወዷቸዋል፡፡ከህልፈታቸው በኃላም ቢሆን ስሃባን የተካው ወርቃማ የታዓብይ ትውልድ መልካምን እንጅ ባለመስራት አስከብሯቸው ኗሯል...ለምን ታዲያ በእኔ እና አንተ ዘመን ይህ ይሁን ??? አውቃለሁ የጭፍን ጥላቻቸው መንስኤ እረሳቸውን ያለማወቃቸው ነው ፤ ይህ ደግሞ የማንም የቤት ስራ ሊሆን አይችልም የእኔ እና የአንተ እንጂ! ስለእሳቸው የሚናገር ትውልድ ደግሞ ከማንም በላይ እረሳቸውን መከተል አለበት "ሙሃመድ ሆይ፡ አላህን የምትወዱ እንደሆነ ተከተሉኝ በላቸው አላህ ይወዳቸኃልና" በአላህ ሚዛን ላይ ራስህን አሳርፍና አላህን በመውደድ ረሱሉን መከተልህን ግለጽ ፤ ያኔ በመጭው አለም እድለኛ በዚች ምድር ደግሞ ለኢስላምና ለመልዕክተኛው መነቀፊያ ከመሆን ድነህ ድል ትነሳለህ፤ ምክንያቱም ረሱሉን በመከተልህ አላህ ይወድሃልና ፤ሃሊቁና <<ሙሃመድ ሆይ፡ ለእለማት እዝነት አድርገን እንጂ አላክንህም » ሲል በእዝነት ለእዝነት የላከውን ናፋቂ ነብይ በዱንያ እርሳቸውን የማየት እድል ያለገኘ ሁሉ በአጄራ ናፋቂውን ለመገናኘት በመጡበት መንገድ ቢጸናስ????? ጎልተህ አርዓያ መሆን ባትችል አንተነትህ ወደ እምነቱ ባይጣራ አላዋቂዎች የዲኑን እና የመልዕክተኛውን ክብር እንዲያጎድፉ መንስኤ ግን ባከህ አትሁን !!! MIchael H.Hart 'The 100:A Ranking Of The Most Influential persons in history' በተሰኘው መጽሃፉ የታሪክ መዛግብትን ፈትሾ በሰው ልጆች ታሪክ መልካም ተጽዕኖ ለውጥ ፈጣሪዎች መካከል ረሱሉን በአንደኝነት ለማስቀመጡ ከእርሳቸው ጎደሎ ስብዕና አለማግኘቱ ፣ማራኪ ስነመግባራቸው እና ከፍተኛ ችሎታቸው /excellence/ እንደ ማረከው ከትቧል » 6 ወንድሜ አንተንስ ? አቡበከር አሲዲቅ በአንድ ወቅት መልዕክተኛው እንደራባቸው ተረድተው ከስንት ድካም በኃላ ያገኙትን ወተት ሰጥተዋቸው ነብዩ ከጠጡ በኃላ ምን እንዳሉ ታስታውሳለህ ?‹ ወተቱን ሰጠኃቸውና ጥሜ እስኪረካ እሳቸው ጠጡ » ረሱል እየጠጡ በአቡበከር መረካት የሚገርም ነገር አይታይህም ... ? ነብዩ አላህ ባዘዛቸው መንገድ ላይ ቀጥ ስላሉ -በተውሂድ ስለጸኑ ወደዳቸውና በሰዎች ዘንድም ተፈቃሪ አደረጋቸው፤ ለዚያም ስማቸው ሲነሳ ገድላቸው ሲዘከር ውስጥን ያሸፍታሉ፤ ክብራቸው ሲነካ ደግሞ ' ፊዳከ ነፍሲ.... ፊዳከ አህሊ ወማሊ...'የሚላቸው እርሳቸውን ከራሱ በላይ እስካልወደደ ድረስ እናዳላመነ እውነት ያለ ሁሉ ስህተቱን ለማረም ይተጋል :: እስኪ አንተም በመጡበትን ቀጥተኛ መስመር ላይ ብቻ እየተጓዝህ አላህ እና መልእክተኛው ባዘዙት ላይ ዙብ ቁም ፤ በእለተ - ትንሳኤ ሰው ሁሉ ከወደደው ጋር ሲቀሰቀስ...ቀድመው ወደው ከናፈቁን ነብይ ጋር በጀነት በመቀስቀስ በዱኒያ ያላየናቸውን ውድ ሰው አላህ ብሎ ጀነት ብንገናኛቸውስ.....፤

ሰው በሰራው ብቻ ሲመነዳ ያኔ ሰው ከወደደው ጋር ሲቀሰቀስ ያኔ ከአላህ እዝነት በቀር ምንም የለኝ እኔ፤ ቢላል አብኑ ራባህ(ረ.ዐ) በሞት አፋፍ ሳሉ ባለቤታቸው ‹ወይ እዝነቴ ወይ ጭንቀቴ› በምትልበት ወቅት ‹ወይ ደስታየ ወይ ስኬቴ በይ እንጂ ነገ እኮ...'ገደን ነልቀል አሂባ ሙሃመድ ወስሃባ'..ብሎ ያለው በሙሉ ልብ ተውሂድን ነው ተግብሮታል መውደድን ነው እርሱ አፍቅሯል ...በእሳቸው ሞት ሃገር ለቋል 'አዛን ትቷል ጀነት እንደሁ በሰላቱ› ኩቴው ›ቀድሟል ታዲያ ለምን በሞት አፋፍ ‹ዋ እዝነቴን› መስማት ይሻል? ይበል እንጅ ወይ ስኬቴ ወይ ደስታየ ..ከአላህ እንደሁ እርሱ ወድዷል ...ወዳጆቹን በውድ ሃገር ይገናኛል!!!!!! አንችስ ለነገ ምን አስቀደምሽ...የምትፎክሪበት ምንስ መልካም ስራ አለሽ?አንተስ እንደ ሃገሮችህ ልጆች ቢላል አሊያም ኡሳም ቢን ዘይድ ውድድ አድረገው የናፈቁህን ነብይ በመከተል በአላህም ተወደህ የዘላለም ማረፊያህ ጀነት ቢሆን አትወድምን.... ?

ዲሩል

አርቀም መፅሄት

እንኳን ለ1436 ኢድ-አል-አደሀ

አረፋ በአል በሰላም አደረሳችሁ



በመንፈሳዊነትና በአለማዊነት መካከል

ሙስሊሙ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ዘርፈ ብዙ ማህበራዊ ጉዳዬች ተነቅሰው ይዘከራሉ::ምሁራዊና ኢስላማዊ አቅጣጫ ይጠቆምበታል፡የሚስተዋሉ ችግሮች ተነስተው የመፍትሄ ጥቆማ ይደረግባቸዋል::



(በኑሩ ሙራድ)

መንደርደሪያ

ለመኖር ምቹ የሆኑ ሀገራትን ዝርዝር የሚያወጡ ተቋማት በመስፈርትነት የትምህርት ፣የጤና ፣የመሰረተ ልማት ፣የሰብዐዊ መብቶች መከበርና መሰል መመዘኛዎችን ይጠቀማሉ: : ከነዚህ መመዘኛዎች ውስጥ አለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው Human development Index ነው:: በዚህ ኤንዴክስ መሰረት ለመኖር ምቹ ተብለው ከሚዘረዘሩ የመጀመሪያዎቹ ሀምሳ ሀገራት መካከል ሁለት የሙስሊም ሀገራት ብቻ ናቸው የሚገኙት:: ሙስሊሞች ያለንበትን ተጨባጭ ለማሳየት የተለያዩ ሙስሊም ምሁራንም ይህንኑ ይጠቀማሉ: : በሳይንስ ፣በባህል ፣በጥበብ እና በሌሎች ዘርፎች አስተዋፅአ ላበረከቱ ግለሰቦች በየአመቱ በሚሰጠው የኖቤል ሽልማት የባለፈው አንድ መቶ አመት ታሪኩ ውስጥ አስራ አንድ ሙስሊም ተሸላሚዎች ብቻ ናቸው ያሉት::

በሌላኛው ጎን በሙስሊም ሀገራት ለመዘዋወር እድሉን ያገኘ ሰው የሚታዘበው የመጀመሪያው ነገር በርካታ መስጂዶችና አጅግ በጣም ጥቂት ሰጋጆች መኖራቸውን ነው:: የአለማዊ ስኬትን መለኪያ በሆኑ ነገሮች ስንመዘን ያለንበት ተጨባጭ ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊ ልኬትም እጅግ የ ሚ ያ ሳ ዝ ን ደ ረ ጃ

በምድር ጀርባ ላይ ላይ ተንቀሳቅሶ የአላህን ሲሳይ እንዲፈለግ ያዘዋል:: የሰው ልጅ አላህ የሰጠውን ምድርን የመገንባት ውክልና ለመወጣት ስራ አይነተኛ መሳሪያና ዋነኛ መንገድ መሆኑን ኢስላም ያስተምራል:: ለማህበረሰቡ ጠቃሚ የሆነና የግለሰቡን ዝንባሌና ክህሎትን ያገናዘበ ስራ እንዲሰራ ግፊት ያደርጋል::

ላ ይ እንገኛለን: :

ላለንበት አሳዛኝ ተጨባጭ ምክኒያቱ ምን ይሆን ለሚለው መጠይቅ ልሂቃኖች የሚሰጡት ምላሽ በአለማዊ ጉዳዬች ላይ ያለን ተሳትፎ አናሳ መሆንና የሰጠነው ትኩረት ዝቅተኛ ነው የሚል ነው:: በሌላ በኩል የሐይማኖቱ አሊሞች ደግሞ ላለንበት ተጨባጭ መንስዔው ከመንፈሳዊ ተግባራት መራቃችን ነው የሚል ነው: : ሁለቱም ጥቆማዎች እውነታነትን ያዘሉ ቢሆንም ቅሉ ጎዶሎ ናቸው: : የችግሩ መነሻ እንደሚሉት አንዱን ዘርፍ መተዋችን ቢሆን ኖሮ በሌላኛው ዘርፍ ላይ ከታች ባልተገኘን ነበር: :የችግሩን ምንጭ ስናጠና ምሁሩ ከአለማዊ አቅጣጫ ፣አሊሞች ደግሞ ከመንፈሳዊ አቅጣጫ ብቻ የተመለከቱት በ መ ሆ ኑ ሰ ለ ች ግ ሩ ም ን ጭ የ ተ ሟ ላ ም ስ ል አላገኘንም: : ይህ ደግሞ ለ መ ፍ ት ሄ ለ ሚ ባ ዝ ኑ አካላት ውጤታማ እ ን ዳ ይ ሆ ኑ አድርጎዋቸዋል:: በርግጥም ችግሩ በውል ካልታወቀ መፍትሄ ሊገኝለት አይችልምና:

ትኩረት ለእውቀት

ትምህርት የፍትህ፣ የልማት እና የስልጣኔ መነሻ መሰረት ነው:: ትምህርት ለእውቀት ማምረት መነሻ፣ ለስራ ዕድል እና ኢኮኖሚያዊ ተግባራት መዳረሻ፣ ለአመራርነትና ለውሳኔ

ሰጪነት መሸጋገሪያ ነው፡፡ እስልምና ለእውቀት ትልቅ ቦታ ስጥቷል የአላህ መልዕክተኛም እውቀት መቅሰምን አበረታተዋል፡፡ በበድር ዘመቻ ወቅት ከተያዙ የሙሽሪክ ምርኮኞች መካከል የተማሩትን መርጠው ከምርኮ ነፃ እንዲወጡ አስር አስር የሙስሊም ልጆቸን ማንበብና መፃፍ እንዲያስተምሩ ነበር ያዘዙት የአላህ መልእክተኛ፡፡ በረሱል (ሰ.ዐ.ወ.)ከመለኮታዊ ምንጭ በሚቀዳው አስተምህሮ ተኮትኩቶ ያደገው ያ ማህበረሰብ ለእውቀት ልዩ ትኩረት ሰጥተዋል፡፡ አስተሳሰባቸው ተራማጅ ሰለነበር በእውቀት መስክ የመንፈሳዊነትና የአለማዊነትን ሚዛን ጠብቀው ስኬታማ ትውልድ መገንባት ችለዋል፡፡ በአላህ (ሱ.ወ.) የተሰጠንን የምድር አምባሳደርነት ሚና በሚገባ ተጫውተዋል፡፡ እንደ ጎርጎራሳዊያን አቆጣጠር በ751 አሁን ክርጊስታን ተብሎ የሚጠራው ሀገር አካባቢ በአባሲዶች የሚመራው የሙስሊሞች ጦር ከቻይናው የሀን ሰርወ-መንግስት ጦር ጋር ተዋግቶ ነበር፡፡ ይህ ጠልዐስ የተባለ ዘመቻ አነስተኛና ብዙ የማይታወስ ቢሆንም የሰልጣኔን በር ከፋችና የአለምን ታሪክ ቀያሪ የሆነን ክስተት ይዞ ብቅ ብሏል፡ ፡ በዚህ ዘመቻ ሙስሊሞች ድል ቀንቷቸው የተወሰኑ ምርኮኞችን ይዘው ነበር፡፡ በወቅቱ መላው አለም ለፅሁፍ የሚጠቀመው ፓፒረስ፣ቆዳ፣ቅጠል ፣አጥንትና የመሳሰሉትን የነበረ ሲሆን ቻይናውያን ግን ወረቀት ፈልስፈው በገዳማት ብቻ ይጠቀሙት ነበር፡፡ በሙስሊሞቹ ከተያዙት ምርኮኞች መካከል ሁለቱ ወረቀት እንዴት አንደሚሰራ ያውቁ ስለነበር የሙስሊሞች መናገሻ ወደሆነችው ባግዳድ ተወሰዱ፡፡ ኸሊፋውም እነዚህን ምርኮኞች ከእስር ነፃ እንዲወጡ ወርቀት እንዴት እንደሚመረት ሙስሊሞችን እንዲያስተምሩ አዘዘ፡፡ በባግዳድና ሰመርቀንድ የወረቀት ማምረቻዎች ተቋቋሙ፡፡ አዳዲስ የወረቀት ማምረቻ ስልቶች ተግባራዊ ሁነው የተሻለ ጥራት ያለቸው ወረቀቶች በብዛት መመረት ጀመሩ፡፡ ፓፒረስና ቆዳ ቦታቸውን ለወረቀት ለቀቁ፡፡ ቻይናውያን ወረቀትን ለተወሰነ ግልጋሎት ብቻ ይጠቀሙበት የነበሩ ቢሆንም ሙስሊሞች ግን እያንዳንዱ አስተዳደራዊ የመዘጋበት ስራ ሳይቀር በወረቀት ፅሁፍ እንዲሰራ አደረጉ፡፡ ወረቀቶችን በመደራረብና በመጠረዝ ፣ብሎም ሽፋን በማበጀትና ርዕስ በማስቀመጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ወረቀቶቹ የመፅሀፍ ቅርፅ እንዲይዙ አደረጉ፡፡ ጥናትና ምርምር ተስፋፋ፡፡ በማህበራዊና የተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፎች ፈር ቀዳጅ የሆኑ ስራዎች ፣እንዲሁም በህክምናው መስክ ትልቅ እመርታዎች ታዩ፡፡ በዚህም የእውቀት አብዬት ተፈጠረ፡ ፡ እውቀት በሙስሊሙ ማህበረሰብ በቀላሉ መስፋፋት በመቻሉ የመጠቀ አስተሳሰብ ያለው ትውልድ ተፈጠረ፡፡

ስራ

ስራ ማለት ለምርት ወይም ለአገልግሎት አንድ ግለሰብ ብቻውን አልያም ከሌሎች ጋር በመተባበር የሚያደርገው እንቅስቃሴ ነው፡፡ኢስላም እያንዳንዱ ግለሰብ እንዲሰራ ይሻል፡፡ በምድር ጀርባ ላይ ላይ ተንቀሳቅሶ የአላህን ሲሳይ እንዲፈለግ ያዘዋል፡፡ የሰው ልጅ አላህ የሰጠውን ምድርን የመገንባት ውክልና ለመወጣት ስራ አይነተኛ መሳሪያና ዋነኛ መንገድ መሆኑን ኢስላም ያስተምራል፡፡ ለማህበረሰቡ ጠቃሚ የሆነና የግለሰቡን ዝንባሌና ክህሎትን ያገናዘበ ስራ እንዲሰራ ግፊት ያደርጋል፡፡ ሁለተኛው ኸሊፋ ዑመር ኢብኑል ኸጣብ (ረ.ዐ.)"በአላህ መንገድ ከሚደረግ ትግል ቀጥሎ የአላህን ሲሳይ በመፈለግ (አለማዊ ስራ በመስራት)ላይ እያለሁ ሞት ቢያገኘኝ እወዳለሁ፡፡ ከየትኛውም ሁኔታ ይህን እመርጣለሁ፡፡" ብለው ከተናገሩ በኃላ የሚከተለውን የቁርዐን አንቀፅ አነበቡ፡-

"ከፊሎቹ የአላህን ችሮታ ፍለጋ (የኑሮ ጉዳያቸውን ለማከናወን)በምድር ላይ አንደሚጓዙ "(አል ሙዘሚል 20) የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.)በተለያየ አጋጣሚ ስራን አበረታተዋል፡ ፡ ንግድን ሲያበረታቱ ፡-

" እውነተኛና ታማኝ ነጋዴ ከነብያት ፣ከአማኞችና ከሸሂዶች ጋር ይሆናል "(ትርሚዚ እና ሀኪም) ግብርናን ሲያበረታቱም ፡-

"አንድ አዝዕርት የዘራ ወይም ተክል የተከለ ከፍሬው ወፍ፣ሰው፣ ወይም እንስሳ በተመገበለት ቁጥር እርሱ ምንዳ ያገኛል"(ቡኻሪ ዘግበውታል) ዕደ ጥበብና ኢንዱስትሪን ሲያበረታቱም አንዲህ ብለዋል፡-

"አንድ ሰው ሰርቶ ከሚበላው የበለጠ ምግብ አልተመገበም" (ቡኻሪ ዘግበውታል)

ስኬታማው ነጋዴ

"ወላሂ!ከአቡበከር በስተቀር ከናንተው ውስጥ እኛ ዘንድ ውለታ ኖሮት ያልመለስንለት የለም፡፡ የአቡበከርን ውለታ ግን የመመለስ አቅሙ የለኝም፡ ፡ ውለታውን አላህ እንዲመለስለት ትቼዋለው " የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.)በመሰናባቻው ሀጅ (ሀጀተል ወዳዕ)ወቅት የተናገሩት ነው፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.)ወደ ኢስላም ጥሪ በጀመሩበት ወቅት ቀድሞ ምላሽ የሰጠው ወዳጃቸው አቡበከር ሲዲቅ ነበር፡፡ ከዚህ በሻገር በወቅቱ እጅግ የተከበረ ሀብታም ነጋዴ በመሆኑ ዳዕዋውን በገንዘብ በማገዝ በኩል ትልቅ ሚና ተጫውቷል፡፡ ቢላል ኢብኑ ረባህን ጨምሮ በርካታ ሰሀቦችን ከባርነት ቀንበር በማውጣት ለዚህ ዲን ያበረከታቸው አቡበከር ሲዲቅ ነው፡፡ አቡበከር ሲዲቅ እጅግ ቸር የነበሩ ሲሆን በእሳቸው እጅም በርካታ ቸርና ለዳዕዋ አጋዥ የሆኑ ሰሀቦችም እስልምናን ተቀብለዋል፡፡ ከአስሩ በጀነት ከተበሰሩት ውስጥ ስድስቱ በአቡበከር ሲዲቅ አማካኝነት ነው እስልምናን የተቀበሉት፡፡

ሰሀቦች ሁለንተናዊ ነበሩ፡፡ የአለማዊ ህይወትና የመንፈሳዊ ህይወትን ሚዛን በሚገባ ጠብቀው ህይወታቸውን መርተዋል፡፡ አሊምች ከአስሩ በጀነት ከተበሰሩት ሰሀቦች ውስጥ አብዘሀኛዎቹ ሀብታም የነበሩ መሆኑን በማውሳት

ያ ትውልድ ሁለቱንም አለም ሚዛኑን ጠብቆ በማጣመር ስኬታ እንደሆነ በዚሁ ሚዛን ላይም ስልጣኔን እንደገነቡ ይገልፃሉ፡፡ በመንፈሳዊ መስክ ብቻ ሳይሆን በንግድም ስኬታማ ነበሩ፡፡ አብዱረህማን ኢብኑ አውፍ ወደመዲና ከተሰደደ በኃላ ንግድን ከዜሮ ጀምሮ ስኬታማና የናጠጠ ሀብታም መሆን ችሎ ነበር፡፡ ታላቁ ሰሀባ አብደላህ ኢብኑ ዑመር የዛን ትውልድ መርህ እንዲህ ይገልፀታል “ለአኼራህ ስትሰራ ልክ ነገ እንደምትሞት ሁነህ ስራ ፣ለዱንያ ስትሰራ ድግሞ ልክ ዘላለም እንደምትኖር በርትተህ ስራ፡፡”

ተራማጅ እሳቤ

የኡመር ኢብኑል ኸጣብ ተራማጅ እሳቤ ለዚህ ዑማ የራሱ የሆነ የቀን መቁጠሪያ እንዲኖረው አስችሏል፡ ፡ የግምገማን እና የቢሮክራሲን ፅንሰ ሀሳብንም ተግባራዊ በማድረግ ዘመናዊ የአስተዳደር ስርዐትን ዘርግተዋል፡፡ የመሪዎች አመታዊ ጉዳዔን በማዘጋጀትም በተለያዩ አጀንዳዎች ዙሪያ ውይይት ያካሂዱ ነበር፡፡ ለስልጣኔና እድገት መንገድ ከፋች የሆነውን የከተማዎችን መቆርቆር ብሎም የመንገድ ዝርጋታን በሰፊው አከናውነዋል፡፡ በተበላሸ መንገድ ላይ አንድ በቅሎ ከወደቀ አላህ ይጠይቀኛል ሲሉ የሙስሊምን ምድራዊ የአምባሳደርነት ሚና አመላክተዋል፡፡ሶስተኛው ኸሊፋ ዑስማን ኢብኑ አፋን ከሙዐዊያ ኢብኑ አቡሱፍያን የቀረበላቸውን ጥናት ተቀበለው ለዐማው የመጀመሪያውን የባህር ሀይል አቋቁመዋል፡፡ የማህበራዊ ዋስትናን ፅንሰ ሀሳብም ተግባራዊ በማድረግ በወርሀ ረመዷን ለእያንዳንዱ ነዋሪ በቀን ሁለት ዲርሀም ተቆራጭ ይደረግለት ነበር፡፡ ሰዎች ቁርዐንን በቀላሉ ማንበብና መረዳት ይችሉ ዘንዳ “ነህው” የተባለውን የአረብኛ ቋንቋ ዘርፍ በስርዐተ-ትምህርት ተቀርፆ የማስተማሪያ መፅሀፍ የተዘጋጀለት በአራተኛው ኸሊፋ በኢለይ ኢብኑ አቡጣሊብ አዛዥነት ነው፡፡ የኢስላማዊ ስልጣኔን መሰረት ያኖረው የሰሀባ ትውልድ ተራማጅና ለውጥን የሚያሰተናግድ ክፍት አመለካከት ነበረው፡ ፡ የስኬታቸውም ምንጭ ይሄው ነው፡፡

- ለመጀመሪያ ጊዜ
- የታተመው ቁርዐን
- ጣሊያን ሀገር
- በሚገኝ ማተሚያ
- ቤት የታተመ ሲሆን
- ይህ ማተሚያ ቤት
- የካቶሊክ በመሆኑ
- አርማው መስቀል
- ነበርና በቁርዐኑ
- የውስጥ ገፆች
- ሳይቀር የመስቀል
- ምስል ነበረበት፡፡

በመንፈሳዊነት ረገድም ሙስሊሙ ከቁርዐንና ሱና በመራቅ አልባሌ ህይወትን መምራት የጀመረ ሲሆን መጤ አመለካከቶችና አስተምህሮቶች ተንሰራፍተው የማህበረሰቡ አቂዳ ብሎም የመልካም ስነ-ምግባር መርሆዎች ተሸርሽረዋል፡፡

የመንፈሳዊነት ጥማ

የሰሀቦች ትውልድ የተፈጠሩበትን አላማ የህወታቸው አብይ መርህ አድርገው ነበር የያዙት፡፡ ልባቸው በአላህ ፍቅር የተሞላ፣ሰሙ ሲወሳ ልባቸው የሚደነግጥ፣ የፍርሀትና የመተናነስ ስሜት የሚሰማቸው ፣እያንዳንዱ እንቅስቃሴያቸው ጌታቸውን እንዲያስደስት በጥንቃቄ የተቃኘ፣ የአምልኮ ተግባራት ላይ ዘወትር መነቃቃትና ብርታት የሚታይባቸው፣ሞትን ተዘጋጅተው የሚጠብቁ ነበሩ፡፡ ኑሮዋቸው ከቁርዐን ጋር ነበር፡፡ ያነቡታል ፣ቃላቸው ለመያዝ ጥረት ያደርጋሉ ፣እያስተነተኑ የጌታቸውን ታላቅነት ያወሳሉ፡፡ አላህን (ሱ.ወ.)በብዛት ያወሱታል፡፡ ለአሳ ውሀ ህልውናው እንደሆነ ሁሉ እነርሱም ዚክርን የቀልባቸው ህልውና አድርገውታል፡፡ ለሊት ሰዎች ሲተኙና ሲያርፉ እነርሱ ግን ከአለማዊ ጉዳዬች እራሳቸውን በመነጠል ከአላህ ጋር በመገናኘት ችሮታውን ይፈልጋሉ፡፡ ምህረቱን ይጠይቃሉ፡፡ እግሮቻቸው ወደመስጂድ ዘወትር ይመላለሳሉ፡ ፡ ከመስጂድ ከወጡም በኃላ ልባቸው ወደመስጂድ የተንጠለጠለ ነው፡፡ ቀን በተለያዩ ጉዳዬች የተጠመዱ ቢሆንም የአለማዊነትና መንፈሳዊነትን ሚና ጠንቅቀው የሚያውቁ በመሆናቸው ቀኑን በዖም ነው የሚያሳልፉት፡፡

የአመለካከት ለውጥ

በ1059 መስቀል ጦረኞች ከአውሮፓ ተነስተው የቁድስ ከተማና ወረሩ፡ ፡ ይህ በታሪክ ድርሳናት የመጀመሪያ የመስቀል ተብሎ የሚጠራው ወረራ በርካታ ሙስሊሞች ያለቁበት ሲሆን ለምዕራባውያኑ የለውጥ ሂደት ወሳኝ ወቅት ነበር፡፡ ምዕራባውያኑ በዚህ ወረራ ወቅት ነበር ወረቀትንና የተጠረዘ መፅሀፍን ለመጀመሪያ ጊዜ የተመለከቱት ፡፡ በወቅቱ ወረቀትና መፅሀፎችን ሸክፈው ወደሀገሮቻቸው ቢመለሱም እንዴት መስራት እንደሚቻል ግን ግንዛቤው አልነበራቸውም፡፡ በሙስሊሞች አስተዳደር የስልጣኔ ማማ የነበረችውን ስፔንን በ1151 ከሙስሊሞች ሲነጥቁ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ የወረቀት ማምረቻን ያገኙት፡፡ የወረቀት ማምረት እወቀቱ ያላቸውን ሙስሊሞችን ብቻ በምርኮ በመያዝና ባሪያ በማድረግ አገልጋዬቻቸው አደረጓቸው፡፡ በተለይም ለ200 አመታት በሙስሊሞች

አስተዳደር ሰር የነበረችው የጣሊያኗ የወደብ ከተማ ሲሲሊን መወረር ሳይንሳዊ እሳቤዎችና መፅሀፎች ወደ ጣሊያን እንዲገቡ መንገዱን ከፍቷል። በሂደትም ምዕራባውያኑ ይህንኑ የሳይንስ ጥናትና ምርምርን በማጎልበት በለውጥ ምህዋር ላይ እንዲጓዝ አስችለዋል። በአስራ አራተኛውና አስራ አምስተኛው ክፍል ዘመን ምዕራባውያን የወረቀት ምርትን ቴክኖሎጂ አሳድገው ጥራት ያለው ምርት ወደ ምስራቁ አለም ኤክስፖርት ማድረግ ጀምረው ነበር። በዚህ ወቅት ሙስሊሞች ኢስላማዊ መፅሀፎች ሳይቀር በምዕራቡ በሚመረቱ ወረቶቀች ነበር የሚፃፉት። መሰረታዊ ች ግ ሮ ቹ መ ነ ሻ ቸ ው በ ነ ዚ ህ ወ ቅ ቶ ች የተፈጠሩ የአመለካከት ለ ው ጦ ች ና ቸ ው ፡ ፡ ሙ ስ ሊ ሞ ች ቀዳሚ የነበሩበትን የ ስ ል ጣ ኔ ፣ የ ጥ ና ት ና ምርምር ፣የሳይንስና ኢንዱስትሪ ዘርፎች ላይ ያላቸው ተሳትፎ አናሳ ሆነ፡ ፡ አዳዲስ ግኝቶችን ማዳበርና ማጎልበት ቀርቶ በበጎ መመልከት አቆሙ። ለእለት ተዕለት ህይወት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳዊ ነገሮች ላይ በምዕራቡ ጥገኛ ሆኑ። ቁርዐንና ኢስላማዊ መፅሀፍት ሳይቀር የሚታተሙት በምዕራቡ አለም ሆነ፡ ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመው ቁርዐን ጣሊያን ሀገር በሚገኝ ማተሚያ ቤት የታተመ ሲሆን ይህ ማተሚያ ቤት የካቶሊክ በመሆኑ አርማው መስቀል ነበርና በቁርዐኑ የውስጥ ገፆች ሳይቀር የመስቀል ምስል ነበረበት። በመንፈሳዊነት ረገድም ሙስሊሙ ከቁርዐንና ሱና በመራቅ አልባሌ ህይወትን መምራት የጀመረ ሲሆን መጤ አመለካከቶችና አስተምህሮቶች ተንሰራፍተው የማህበረሰቡ አቂዳ ብሎም የመልካም ስነ-ምግባር መርሆዎች ተሸርሽረዋል። ውድቀቱ የጀመረው ለመንፈሳዊነትንም ሆነ አለማዊነትን የተሳሰተ አመለካከት በመዳበሩና ተራማጅ የሆኑ እሳቤዎች ከስመው የተገደቡ እሳቤዎች ቦታ በማግኘታቸው ነው።

ሶስተኛው ክሊፋ ዑስማን ኒብኑ ኧፋን ከመዑያ ኒብኑ ኧቡሱፍያን የቀረበላቸውን ጥናት ተቀበለው ከዑማው የመጀመሪያውን የባህር ሀይል ኧቋቁመዋል። የማህበራዊ ሳስትናን ፅንሰ ሀሳብም ተግባራዊ በማድረግ በመርህ ረመዳን ከኧያንዳንዴ ነዋሪ በቀን ሁለት ዲርሀም ተቆራጭ ይደረግለት ነበር።

ሌላኛው ለዱንያ የሚል የተለያዩ እና የተነጣጠሉ ሁለት መንገዶችን አያውቅም ሲሉ ዑለማዎች ያስረዳሉ። ኢስላም አምልኮን ለወዲያኛው አለም ክብርት፣ ስራን ደግሞ ለዚህኛው አለም ድሎት በሚል ኢባዳን ከስራ ስራን ከኢባዳ የገነጠለበት ክስተት የለም። ኢባድም ሆነ ስራ የሁለት አለም ትሩፋት አላቸው። ኢባዳና ስራ ጎን ለጎን አብረው የሚሄዱ ናቸው፡ ፡ ለአኼራ መስራት ከዱንያ ግንባት አያግድም ፣ዱንያን ማሳመር ከኢባዳ አያርቅም። የኢስላም ጎዳና የነፍስና የስጋና ፍላጎት ያዋሀደ ነው። አለማዊ ስራ በመልካም ኒያና ሃላል በሆነ መንገድ ሲከናወን ምንዳ የሚያስገኝ አምልኮ ይሆናል። ሁለቱን ነጣጥሎ መመልከት ኢ-ተፈጥሮዋዊ ነው። ነፍስን ከሰጋ ማራራቅ ብኩንነትን ይወልዳል። የሰው ልጅን የህይወት ግቡንም ሆነ መንገዱን በሁለት ተከፍሎ እንዲባዝን ያደርገዋል። ኢስላም የዘረጋው ጎዳና መንፈስንም ሆነ ስጋን በአንድዬ ማርካት የሚችል ፣ወደ አንድ ጠርዝ ሳያጋድል የመንፈሳዊነትና የአለማዊነትን ሚዛን ጠበቆ የሚራመድበት የሁለት አለም ስኬታማነትን የሚያረጋግጥ አንድ ጎዳና ነው።

ሁለት አለም አንድ ጎዳና

በርካታ ሙስሊሞች ዘንድ ሰለ ዱንያና አኼራ የተሳሳተ ምልከታ አለ። ሰራዎችንም የዱንያና የአኼራ ብሎ መከፈል ከዚህ የተሳሰተ ምልከታ የተወለደ ነው። ኢስላምን ከሌሎች ሀይማኖቶችም ሆነ ሰው ሰራሽ ሰርዐቶች ልዩ የሚያደርገው ለሁለቱ አለሞች የዘረጋው አንድ ጎዳና በመሆኑ ነው። ኢስላም አንደኛው ለአኼራ

https://www.face-book.com/darularqem1



(በአቡበከር ያሲን)

ሃጀር የፅናት ተምሳሌት

ሃጀር - የፅናት ተምሳሌት

ነቢዩ ኢብራሂም ዐለይሒ ሰላም ሃጀርንና ከሃጀር የወለዱትን ልጃቸውን ኢስማዒልን ይዘው ከሻም ሀገር ተነሱ። ለጉዟቸው ማረፊያ ሀገር ያሰቡት የተከበረውን የመካ ምድር ነው። ያኔ ኢስማዒል ገና ከአንቀልባ ያልወረደ ጡት ያልጣለ ጨቅላ ህፃን ነበር። ኢብራሂም እናትና ልጅን ወስደው የአላህ ቤት ከዕባ ዘንድ አኖሯቸው። ተምር ከያዘ አነስተኛ ስልቻ እና ጥቂት ውሃ ከያዘ ኮዳ ጋር። የያኔዋ መካ ምንም ሰው አልነበረባትም ፤ ህይወት የሚባል ነገር ዝር አይልባትም ፤ ከሰው ይሁን ከእንሥሣ ፍጥረት የተባለ አ ይ ታ ይ ባ ት ም ፤ በአካባቢው ውሃም ሆነ ወንዝ አ ል ነ በ ረ ም ። ነቢዩ ኢብራሂም በዚህ ሁኔታ ላይ ሚ ስ ታ ቸ ው ን ና የ አ ብ ራ ካ ቸ ው ክፋይ የሆነውን አንድዬ ልጃቸውን ኢስማዒልን ትተው ወደ ኋላ ዞረው ወደ ሻም ምድር ገሠገሱ። ... ታላቅ ጭካኔ ነበር። የ ኢ ስ ማ ዒ ል እናት ሃጀር ሁኔታውን ለማመን የሚቸግር በሚመስል እይታ ዙሪያዋን ለመቃኘት ሞከረች። ምንም ዓይነት ድምጽ የማይሰማበት እጅግ አስፈሪ ምድርበዳ ሆነባት። በቅርብ ርቀት የነጣጡና የገረጡ አለታማ ኮረብታዎች ይታያሉ። የበረሃው ሀሩር ያነደዳቸው ያገጠጡ ጥቁር ድንጋዮችም እንዲሁ። አካባቢው ምንም የአደም ዘር የለበትም ፤ ቢጮሁ የሚሠማ ዘመድም ሆነ የሚደርስ ጎረቤት የለም። የሃጀር የኋላ ታሪኳ በቅንጦት የተሞላ ነው። እድገቷ ሁሉ ነገር በሞላባቸው የግብፅ አብያተ መንግስታትና በዓባይ/ናይል/ ወንዝ ዳርቻ ነበር። ቀጥሎም ለተወሠነ ጊዜ የኖረችው በሻም ሀገር (የዛሬው ፈለስጤን ፣ ዮርዳኖስ እና ሶሪያ አካባቢ) ነው ፤ በለምለሙ አገርና በአረንጓዴው መስክ። አሁን ግን የምታየው ሁሉ ያልለመደቻው እንግዳ ነገር ሆነባት ፤ ፍርሃትም ውርር አደረጋት።... ተነሣችና ትቷት ለመሄድ ፊቱን ያዞረውን ባሏን ለመከተል አሠበች... ለመራመድም ሞከረች። ‹ኢብራሂም ሆይ! ወዴት ትሄዳለህ?› አለችው ፤ ‹በዚህ ሰውም ሆነ ወዳጅ ዘመድ በሌለበት ሸለቆ ትተህን የት ልትሄድ ነው?› በማለት ተጣራች። ነቢዩ ኢብራሂም መልስ አልሰጧትም ፤ ዞር ብለውም አላዩዋትም። መልሣ ተጣርታ ጠየቀቻቸው። ‹እዚህ ትተህን ወዴት ነው የምትሄደው?!› ነቢዩ ኢብራሂም አሁንም መልስ አልሠጧትም። ለሦስተኛ ጊዜ የሚሠማ ዘመድም ሆነ የሚደርስ ጎረቤት የለም። ብትጠይቃቸውም አሁንም መልስ የለም። ዞር ብለው እንኳን አለማየታቸውን ባስተዋለች ጊዜ ‹አላህ ነው እንዴ በዚህ ነገር ያዘዘህ?!› በማለት ጠየቀቻቸው። እርሣቸውም ‹አዎን!› በማለት መልስ ሠጧት። እሷም ‹እንዲያ ከሆነ እሱ በቂዬ ነው ፤ በአላህ ወድጀያለሁ። እንግዲያውስ በል ሂድ ፤ እሱ ጥሎ አይጥለንም!!› አለቻቸው። በአላህ ማመን ፣ በሱም መመካት ... ይሏል ይህ ነው። ሃጀር ከአላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ የመጣውን ነገር ሁሉ ለመቀበል ዝግጁ መሆኗን አረጋገጠች ፤ እሱ የወደደላትንም በፀጋ ተቀበለች። አሁን ፍርሃት ለቀቃት ፤ ብቸኝነትም ራቃት። በአላህ ላይ ሙሉ እምነት ያለው ሰው አይደለም በሞት በብዙ ሞቶች መካከል ቢሄድ እንኳን አይደነግጥም ፤ አይርበተበትም ፣ አይፈራም። በአላህ ላይ ጥሩ ተስፋን የሚያሣድር ሰው በእጁ ላይ ካለው ነገር ከአላህ ዘንድ ባለው ይበልጥ ይተማመናል። ወደ ታሪኩ እንመለስ፦ ነቢዩ ኢብራሂም ‹አዎን ከአላህ ነው ትዕዛዙ› ባሏትና ቁርጡን በነገሯት ጊዜ እርሣቸውን መከተል ትታ ወደ ኋላ ወደ ልጇ ተመለሠች። በእድሜ ገፍተው እርጅናም ተጫጭኗቸው የነበሩት ነቢዩ ኢብራሂም በዚህ መልኩ ሚስታቸውንና ልጃቸውን በቂ ስንቅ ፣ ውሃና ሰው በሌለበት ጭው ባለው በረሃ ላይ ትተው ጉዞአቸውን ወደ ሻም ሀገር ቀጠሉ። ጥቂት እንደሄዱም በመካ ዙሪያ ከሚገኙ ተራሮች መካከል በደረሱ ጊዜ ልጅና



እናት በማያዩበት ሁኔታ ፈታቸውን ወደ አላህ ቤት አቅጣጫ በማዞር እጃቸውንም ወደ ላይ በማንሣት እንዲህ በማለት ዱዓእ አደረጉ።

رَّبَّنَآ إِنِّيٓ أَسۡكَنتُ مِن ذُرِّيَّتِي بِوَادٖ غَيۡرِ ذِي زَرۡعٍ عِندَ بَيۡتِكَ ٱلۡمُحَرَّمِ رَبَّنَا لِيُقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ فَٱجۡعَلۡ أَفۡـِٔدَةٗ مِّنَ ٱلنَّاسِ تَهۡوِيٓ إِلَيۡهِمۡ وَٱرۡزُقۡهُم مِّنَ ٱلثَّمَرَٰتِ لَعَلَّهُمۡ يَشۡكُرُونَ

‹ ጌታችን ሆይ! እኔ ከዝርያዎቼ አዝርእት በሌለበት ሸለቆ ውስጥ ከተከበረው ቤትህ ዘንድ አሠፈርኩ። ጌታችን ሆይ! ሰላትን ደንቧን ጠብቀው ይሰግዱ ዘንድ ፤ የከፊሎችን ልቦች በነርሱ ፍቅርና ናፍቆት እንዲሞሉ አድርግልን። ያመሰግኑህ ዘንድም ፍራፍሬዎችን ለግሣቸው።› (ኢብራሂም ፡ 37) ይህንን ዱዓእ አድርገው አደራውን የባሮቹን አደራ ለማይዘነጋው ለአላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ሰጥተው ነቢዩ ኢብራሂም ወደ ሻም ሀገር ተመለሡ። ሃጀር ከያዘችው ጥቂት ውሃ ልጇን ማስጎንጨት ጀመረች። ጡት ማጥባቱንም ተያያዘችው። በኩዳው ውስጥ የነበረው ውሃ ግን ሊያልቅ ብዙ ጊዜ አልፈጀበትም። ስለሆነም በዚያ ሀሩሩ አናትን በሚበሣበት ምድር እናትና ልጅ የውሃ ጥም በረታባቸው። ህፃኑ ልጇ ከጥም የተነሣም ተዳከመና ተዝለፈለፈ ... ያለከልካል ፣ ከንፈሩን በምራቁ ያርሣል ... ጣቱን ይጠባል .. ሲብስበትም በእጅን በእግሩ መሬቱን ይደበድባል .. ያለቅሣል። ሃጀር ጭንቅ ሲለት ዳግም ዙሪያዋን ቃኘች። አጋዥና ፈጥኖ የሚደርስላቸው አንዳች ፍጡር ይኖር ይሆን!። ጠበቀች .. ነገርግን ምንም አላገኘችም። እናት በፈጣሪዋና ተንከባካቢዋ አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ላይ ከፍተኛ ተስፋና የሠከነ እምነት አላት። ለዚህም ነበር ለባሏ ‹አላህ ጥሎ አይጥለንም!› ያለችው። ሆኖም ግን ‹አላህ አለልን ምንም አንሆንም!› ብላ እጅ እግሯን አጣጥፋ አልተቀመጠችም። ስበቡን ማድረስ ነበረባትና ዓይኗ እያየ ልጇ እንዲሞትባት አልፈቀደችም። እናም ተነስታ ቆመች .. ረሃቡ አዳክሟታል .. ጥም አጎሣቁሏታል .. ወዴት እንደምትሄድ ግራ ተጋባች። ያ አሏህ!!.. እስኪ የዚህችን ፅኑ የአላህ ባሪያ ታሪኳንና ብክነቷን አብረን እንከታተል ... በሀሣብም አብረናትም ወጥተን እንውረድ ... አዎን... ተነሣችና ቆመች። በቅርብ ወደሚታያት ወደ ሶፋ ኮረብታ አመራች። ከአናቱም ላይ እንደምንም ወጣች። አርቃ በዓይኗ ውሃ ፈለገች .. አሻግራ በአካባቢው ፍጥረት ይገኝ እንደሆን ተመለከተች .. ቁልቁል ወደ ሸለቆዎችም ጎልጉላ አየች። ሀሣቧ ሁሉ ውሃ ነበር ፤ በአካባቢው ሰው ካለ አለያም የሚያልፉ ቅፍለቶችንም ባገኝ ብላ ነበር። ነገር ግን ምንም ልታይ ልታገኝ አልቻለችም። ሆኖም ግን ተስፋ አልቆረጠችም ፤ ፍለጋዋንም አላቆመችም። ከኮረብታው ወረደችና ወደ ሸለቆው ሆድ ተንደረደረች። ከዚያም ትንፋሿ ቁርጥ እያለ የደከመው ሰው ሩጫ ዓይነት ትሮጥ ጀመር። እንዲህ እየገሠገሠች ባዶ እጇን ከሸለቆው ወጣች። እንደገና ወደሌላኛው ኮረብታ ወደ መርዋ አመራች ፤ እላዩ ላይም ወጥታ ቆመች። አሻግራና አርቃም ተመለከተች። ሰው ፈለገች .. ውሃ ፈለገች .. ፍጥረት ፈለገች። ጭው ጭልል ያለ ሰው አልባ ሀገር ሆነባት። አሁንም ተመልሣ ወደ መጀመሪያው ኮረብታ ወደ ሶፋ መጣች። ዳግም አርቃ አየች። ሆኖም ግን ምንም አዲስ ነገር አላየችም። ጠንካራዋ እመቤት እንዲህ ባከነች። ሰባት ጊዜ ያህል በሶፋና በመርዋ ኮረብታዎች መካከል ተመላለሠች። (በሐጅ ላይ የምናደርገው ፈጠን ያለ እርምጃ ይህን ክስተት ለማስታወስ መሆኑን ልብ ይሏል።) ከሰማይ ቤት ምን ያህል እውቅና ቢሰጣት ነው አላህ ድርጊቷን ሴቶችም ይፈፅሙ ዘንድ መንገድ ያደረገው!! ሱብሓነላህ!! እስልምና ሴቶችን አያውቅም ስለ ሴቶችም ግድ የለውም የሚሉ ተከራካሪዎች ለዚህ ጉዳይ ምን ይሆን መልሣቸው?? ታሪኩን እንጨርስ... ሃጀር ሩጫዋ ውጤት አላስገኘላትም፤ ብክነቷም ፍሬ አላመጣላትም። በመጨረሻም በሰባተኛ ዙር መርዋ ላይ በወጣች ጊዜ የሆነ ድምፅ ሰማች። ለራሷም ‹እሽ .. እሽሽ..› አለችና ጆሮዋን አቅንታ ወደ ድምፁ አቅጣጫ ማዳመጥ ያዘች። ‹የሆነ ድምፅ ሠምቻለሁ .. እባክህ ረጂ ከሆንክ እርዳኝ ድረስልኝ!› በማለት ተናገረች። መልስ አላገኘችም። ወደ ልጇ ዘወር አለች። በዚህን ጊዜ አንድ መልዓክ በክንፎቹ መሬቱን ሲጭር ተመለከተች። መልዓኩ ውሃው እስኪፈልቅ ድረስ መሬቱን ቆፈረው። የኢስማዒል እናት ደስታ ፈንቅሏት ወደ ውሃው ፈጠነች። ፈስሥ እንዳያልቅባት ብላ በድንጋይና በአፈር ትገድበው ያዘች። አቤት! ጉጉቷ። በመዳፎቿ እየዘገነችም ወደ ውሃ መያዣው እቃ ጨለፈች። ጨልፋ በጨረሠች ቁጥርም የተጫረው ውሃ ዳግም ይሞላል። ውሃው የዘምዘም ውሃ ነበር። የኢስማዒል እናት በደስታ ስሜት ተውጣና ሰክራ ባትገድበው ኖሮ ትልቅ ምንጭ በሆነ ነበር። ‹ዋ ! ምነው በተወችው አላህ ይዘንላትና› ይላሉ የኛ ነቢይ ሰለላሁ ዐለይህ ወሰለም። ‹ኢዘን ላ ዩደይዑና!.. ‹እንግዲያውስ ጥሎ አይጥለንም።› ያለችውና እውነተኛ መመካትን በፈጣሪዋ የተመካችው የአላህ ባሪያ ጌታዋ እውነትም ጥሎ አልጣላትም። የተወኩሏን ፍሬ አየች ፤ የትእግስትን ጥፍጥና ቀመሠች ፤ የየቂኗንም ውጤት በዚህ መልኩ ቀጠፈች። እንዲህ አላህ (ሱ.ወ.) ባሮቹን ያክማል ፣ ወዳጆቹን ይሸልማል። ቀጥሎም ሌላ ለሃጀር ሌላ መፅናኛ መጣላት። መልዓኩ ጅብሪል እንዲህ በማለት አረጋጋት ‹አይዞአችሁ ችግርን አትፍሩ። በዚህ ቦታ ላይ የአላህ ቤት ይሆናል ፤ ይህ ልጅና አባቱም ይገነቡታል።› ይህ ጣፋጭ ታሪክ የኢስማዒል እናት የሃጀር የበረሃ ላይ ብክነት ነው። ታሪኩ በዋናነት የሃጀር ትእግስትና ተስፈኝነት ጎልቶ የወጣበት ነው። ጥንካሬዋና ፅናቷ በተለይ ለኛ ለሙስሊም ሴቶች በርካታ ቁምነገሮችን ያስጨብጠናል። በታሪክ ውስጥ በየዘመኑ ምርጥ ሴት የአላህ ባሮች ማለፋቸውንም ያስታውሰናል። ፈተናዎች ቢደራረቡም በእምነታችን ላይ እንዴት መፅናት እንዳለብንም ያስተምረናል። ይህች በርግጥም ሃጀር ናት። ጽናት ተምሳሌት ፣ የተስፋ አብነት። ትዕግስቷ ይገርማል። ሁኔታዋ ያስደንቃል። በመከራ ላይ ታገሰች ፣ የቀረበላትንም ፈተና በብቃት አለፈች። በአላህ ቁርአን ውስጥም ለዘላለሙ ተወሳች። ልጇም ለነቢይነት ተመረጠ። እሷም የነቢያት እናት ሆነች። ለአላህ ወዳጆች ምሳሌ ሆና ቀረበች። አዎን የህች ሴት መጨረሻዋ እንዲህ አማረ። መጀመሪያ አካባቢ እልም ባለው በረሃ ብቸዋን መሆኗን ባስተዋለች ጊዜ ፈርታ ነበር። ረሃብም ጥምም አጎሳቁሏት ነበር። ሆኖም ግን ነገሩ ከአላህ (ሱ.ወ.) መሆኑን ባወቀች ጊዜ አላህ (ሱ.ወ.) የወደደላትን ወደደች። ከልብም አምና ተቀበለች። በአላህ

በአላህ መንገድ ባይተዋር ሆና ኖረች። በመጨረሻም አላህ (ሱ.ወ.) ደስታና ሀሴትን ላከላት። አዎን! የባይተዋሮች መጨረሻ እንዲህ ነው። በበዙ መጥፎ ሰዎች መካከል የሚኖሩ ባይተዋሮች መጨረሻቸው ድል ብቻ ነው።

ከአዛኞች



(ሙባረክ አብዱረዛቅ)



ሚዛናዊ ዕውቀት ፈለጋ

እስልምናችን በሁለ ነገሩ ሚዛናዊነትን ያዛል። ሙስሊሞችም በዱንያዊ እና በኣኺራዊ ጉዳይ ማለትም ቁሳዊነት እና መንፈሳዊነትን በተመለከተ ፤ በመስጠት እና በመንፈግ (የተወሰነውን ለራስ ቆጥቦ በማስቀረት) ረገድ ፤ በእምነት እና በእውቀት ፤ በኃሳብ እና በእውን ፣ በንግግር እና በተግባር ፤ እንዲሁም በራሳችን እና በሌሎች ጉዳይ ላይ ሚዛናዊ ፣ ፍትሃዊ እና ማእከላዊ እንድንሆን ይደነግጋል። ለዚህም ሲባል ነው መንፈሳዊነትን እና መንፈሳዊ እውቀትን ብቻ ሳይሆን ለምድራዊው ዓለም የሚበጁ ፣ በቁሳዊ ህይወታችን ስኬትን የሚያቀዳጁ የእውቀት ዘርፎችን እንድንማር የሚሰብክልን እስልምና። ቀደምት ሙስሊሞችም በሁለቱም የህይዎት መስክ የዳበረ እውቀት እና የላቀ ተመክሮ ነበራቸው። በዓለም ላይ ያላቸው የታሪክ ፋናም ለዚህ ተጠቃሽ ነው። የላቀ ስልጣኔ እና የረቀቀ ጥበብን አዋህደው የያዙ ቀደምት ትውልዶች ለአንጸባራቂው እስልምና መር ስልጣኔ አንኳር ተዋናይ ነበሩ። የ"ጨለማ" ተብሎ በተሰየመው ዘመን እንኳ ሳይቀር ፣ ለዓለም ብርሃን የፈነጠቀው ማህበራዊ ምጥቀት ምንጩ ፣ ድንቅ መንፈሳዊነትን አላብሶ ጥልቅ ሰብዓዊነት ያወረሳቸውን ፣ የጽድቅ ዕሴቶች ዓምባ እስልምናን ከሌሎች የዕውቀት ዘርፎች ጋር አዋህደው መገንዘባቸው ነው። ያም በመሆኑ የሰው ልጅን ያማከለ ፣ ለሰብዓዊ ክብር የቆመ ሁለገብ ብልጽግና ተመዘገበ። ወደሐገራችን ስንመለስ ሁለቱን ዘርፎች አጣምሮ የማስኬድ ተመክሮ ያንሰናል። ቀደምት አባቶቻችን ለኃይማኖታዊ ትምህርቱ ህይወታቸውን ለግሰዋል። የዕድሜያቸውን ዋነኛ ክፋይ ዲናዊ ዕውቀት በመቅሰም አሳልፈዋል። ሌላውን ዓይነተኛ የህይወታቸው ክፍል ደግሞ ከኃይማኖት ምሁራን የተጋሩትን ነብያዊ ውርስ ለሌላው ሲያከፋፍሉ ኖረዋል። በዚህ ረገድ ህዝባችን ኃይማኖታዊ ግንዛቤው ተጠብቆ ለእምነቱ ሚች እንዲሆን አስችለውታል። ህዝበ ሙስሊሙ በሁሉም ዘመናት በኃይማኖታዊ ማንነቱ ላይ የዘመተበትን ሁሉ ሳያሰልስ እንዲታገል ያስቻለው ፤ እስካሁንም እጅ ሳይሰጥ የዘለቀው በዚሁ መንፈሳዊ ትጥቅ ታግዞ ነው። ይሁን እንጅ በሌሎች የህይወት ዘርፎች የነበረው ተሳትፎ ተገትቶ ኖሯል። ለዚህም ሁሌ ተከላካይ ሆኖ ወደፊት እየሄዱ በሚመጡ አጥቂዎች ጫና ስር ወድቋል። ለምን? ቢባል ደግሞ ካላበት የተከላላካይ ክልል ወጥቶ



በአጥቂነት ወይም እንደሌላው በተመላላሽነት ሊጫዎትበት የሚችልበት ሜዳ አልነበረውም። ሁሌም ባጥቂዎች የሚደፈርበትን የተከላካይ ክልል ብቻ ታቅፎ ለረጅም ጊዜ ተጫውቷል። ይሁን እንጅ በቅርብ ጊዜያት ያሰላለፍ ለውጥ ባይባልም ያጨዋወት ስልት መቀየሩን ማንም ያስተውለዋል። ሙስሊሙ ከተከላካይነትም ከአጥቂነትም ሳይሆን መሐል ተጫዋች እየሆነ ያለበት ሁኔታ ይታያል። እንዴት? ካልን ዝርዝር መልሱን በቀጣይ ለማየት እንሞክር። አንዱን ጥሎ ፣ አንዱን አንጠልጥሎ፤ ብዙ የኃይማኖት ምሁራንን ያፈሩ ፤ ከደረጃ ደረጃ እያሸጋገሩ በብዙ የእውቀት ዘርፎች ሺዎችን ያበቁት የእውቀት ማዕከሎቻችን ባዶነት ከተሰማቸው ፤ ብቼኝነቱ በዝቶባቸው የደረሳ ናፍቆት መስሰማት ከጀመራቸው ቆየ። ብዙዎቹ የሚልም ማዕዶች የሚያቀርቡት ሳይሆን የሚበላላቸው ጠፍቷል። ቀደም ባሉት ጊዜያት ከየቤተሰቡ ወይም ከየሰፈሩ ለደረስነት ወደሌላ ቦታ የሚሄድ ልጅ ነበር ማለት ይቻላል። ቀሪው የቤተሰቡ ልጆች ደግሞ ባቅራቢያ ባለ ሼይኽ አማካኝነት ከቁርዓን ንባብ ባለፈ የፊቅህ ኪታቦች እና የሐዲሥ ትምህርቶችን አልፎ ተርፎም የቁርዓን ትንታኔዎችን የሚማሩበት ዕድል ሰፊ ነበር። ነገር ግን ይህ አግባብ እየቀረ የብዙሃኑ ልጅ እና ቤተሰብ ትኩረት ዓለማዊው ትምህርት ብቻ ላይ እየሆነ ነው። ለአስር ፣ አስራ አምስት ወይም ኃያ ዓመታት ያህል ወሳኝ የዕድሜያቸውን ክፍል በትምህርት የምናሳልፍ በርካቶች ነን። ይሁን እንጅ ብዙ ጊዜ እና ወጭ ለማይሹት የዲን እውቀት ፍለጋ የምንመድበው ጊዜም ሆነ በስኬታማ መልኩ እውቀትን ቀስሞ ለመተግበር የምናወጣው ኃይል እዚህ ግባ የማይባል ነው። በርካቶቻችን ልጆቻችንን ወይም እህት ወንድሞቻችንን ለማስተማር "ምርጥ" ለሚባሉ ውድ ትምህርት ቤቶች ፣ የትርፍ ጊዜ አስጠኝ እና የትምህርት ማገዣ ቁሳቁስ ለማሟላት የምናወጣውን ወጭ የሚስተካከል ይቅር እና ተመሳሳይ ትኩረት እንኳ ነፍገነዋል - ለቁርዓት። ሙስሊሙ ባገራችን ላይ ከማህበረ-ፖለቲካ ህይዎቱ የተገለለው ወዳንድ ጎን ባጋደለው የትምህርት ዘይቤ ምክንያት ነበር ማለት ይቻላል። ለዚህ ደግሞ እኩል የትምህርት ዕድልን ነፍገው የነበሩ እኩይ ስርዓቶች ድርሻ ቀላል አይደለም። ይሁን እንጅ ያሁኑ ትውልድም ሌላኛው ጠርዝ ላይ መቀመጥን የመረጠ ይመስላል። ዓለማዊ ትምህርቱን አቋርጦ ገጠር ወደሚገኙ የኢልም መቅሰሚያ ቦታዎች ይሂድ ማለት አይደለም። ነገር ግን ባካባቢው ባሉት መድረሳዎች ፣ መስጅዶች ፣ ኡስታዞች እና መሻሂኾች አማካኝነት የዲኑን መሰረታውያን ለመማር መትጋቱ የግድ ነው። ካልሆነ በደርግ ዘመን የመማር ዕድል አጋጥሟቸው እንደነበሩት ውስን ሙስሊሞች ከኃይማኖት

የዘመን መለወጫ ወይስ ቅዱስ ዮሐንስ? - አዲስ ዓመት ከ’’የኢትዮጵያ የዘመን መቁጠሪያ’’ነት ባሻገር

ሐገራዊ ማንነታችን ላይ ተጽዕኖ ያሳደሩ የታሪክ ፣ የባህል ፣ የእምነት ፣ የአስተዳደር እና ማህበራዊ ህጸጾች ተነቅሰው ከሙስሊሙ መገለል ጋር የሚሰናሰኑበት ክፍል ነው። በዚህ ዓምድ ወቅታዊም ይሁን ያለፉ ክስተቶችን ያማከሉ ስር ሰደድ የተዛቡ አመለካከቶች በሙያዊ ቀረቤታ ይተቻሉ። ሙስሊሙ በማህበረ ፖለቲካ ጉዳዮች ዳግም ንቃተ ህሊናው እንዲጎለብት የሚረዱ የፊቸር ስራዎች ይቀርቡበታል። ሐገራዊ እና ማህበረሰባዊ መግባባትን የሚገነቡ ፤ የእኩል መብት እና ተጠቃሚነት መርህን ያነገቡ ጽሁፎች ይስተናገዱበታል።



አህመዲን ሙኒር)

በዘንድሮ ማለቴ ሰሞኑን ባለቀው ነባር ዓመት ለዚህኛው ዓመት የተዘጋጀው የቀን መቁጠሪያ ብዙ አወዛግቦ ነበር። ጉደኛዋ አስራ ሶስተኛ የጳጉሜ ወር የባዕዳን አገር ሰዎችን ብቻ ሳይሆን እኛንም ታምታታን ጀምራለች። እንዴት ቢሉ ብዙሃኖቻችን የስሌት ህጉን ባንረ’ዳውም ለሶስት ዓመታት አምስት አምስት ቀናትን እየኖረች ለጥቃ ስትመጣ ፤ ባራተኛው ዓመት ዕድሜዋ ባንድ ቀን ይረዝምና ስድስት ትሆናለች አሉ። ታዲያ በርካታ ያገራችን ተቋማት ባዘጋጁት የቀን መቁጠሪያ መሰረት ይህኛው ዓመት ይጀምራል የተባለው ጁማዓ ቀን ነበር ፤ በተለምዶ ጳጉሜ ባምስት ታልቃለች ተብሎ ታስቦ መሆኑ ነው። ነገር ግን በኋላ ላይ “የጉዳዩ ዓዋቂዎች” እንዳሳወቁት “ያላቀው ዓመት እኮ ዘመነ ሉቃስ ነበር ፣ ለጣቂውም ዘመነ ዮሐንስ ፤ ስለዚህ አባ ዮሐንስ ረጋ ብለው ፣ አንድ ቀን ዘግይተው ነው የሚደርሱት ተባለ”። ሉቃስም ዘና ብለው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ጨምሮ ሌሎች በርካቶች ካሳተሙት ዘመን መቁጠሪያ እንዲሁም እነሸገር ሬድዮ ካስነገሩለት ዕለት አንድ ሙሉ ቀን ዘግይተው ተዝናንተው ወጡላችሁ። ይህ ዓይነት ልዩነት እንዴት ሊፈጠር ቻለ ለሚለው ወደኋላ ላይ ያጣቀስኩትን ጽሁፍ ፈልገው ሊያዩት ይችላሉ። ነገር ግን ዕለቱ የዘመን መለወጫ ነው ፣ አዲስ ዓመት ፣ እንቁጣጣሽ ወይስ ቅዱስ ዮሐንስ በሚለው ጉዳይ ላይ ዳዊት ደስታ በተባሉ ግለሰብ “ርእሰ ዓውደ ዓመት ቅዱስ ዮሐንስ” በሚል ርዕስ በማህበረ ቅዱሳን ድህረ ገጽ ላይ የሰፈረውን መጣጥፍ ፈልጎ ማንበብ ይቻላል።



ታዲያማ እንደ ድሮው ሁሉ ዘንድሮም ዘመን መለወጫ በካላንደሩ መሰረት ከሁለት ሺ በኋላ ያለችው 7 እና 8 ቁጥሮች የሚፈራረቁበት አልሆነም ፤ አራቱ ወንጌላውያን (ሉቃስ ማርቆስ ማቲዎስ እና ዮሐንስ) በጊዜ መቁጠሪያው ሳይሆን በኃይማኖታዊ ቀኖናው መሰረት አንድ ቀን ዘግይቶ የተለዋወጡበት እንጅ። በዓሉ እውን ብሄራዊ (ማለቴ የሐገራችን ፣ የጋራ ፣ መንግስታዊ) በዓል ቢሆን የሐገሪቱ ህግ አውጭ የሆነው የህዝብ ምክር ቤት ባሳተመው ካላንደር/አጀንዳ መሰረት በተከበረ ነበር። ግንማ ይህን በደንብ የሚያውቀው እና የሚወስነው ሌላ አካል ነውና ቀኑ ተቀይሮ ተከበረ። ከዚህ ጋር በተያያዘ ዳንዔል ክብረት በዓመቱ መገባደጃ ላይ “ዕውቀት ቦታ ሲያጣ” በሚል ርዕስ ባስነበበው መጣጥፉ የዚህን ዘመነ ቆጠራ እምነታዊ ዳራ እንዳለው ያትታል። በኃይማኖት መጻህፍት ቁልጭ ብሎ የቀረበ ያቆጣጠር ዘይቤ እያለ እና የኃይማኖት ምሁራን ስለ ዘመን ቅማሬ ሊያስረዱ እየቻሉ ፤ ጉምቱው የሐገራችን የህግ አውጭ አካል ካራት ዓመት በፊት ባዘጋጀው አጀንዳ ላይ ስድስተኛዋን የጳጉሜ ቀን መቀነሱ ሳያንስ ዘንድሮም መድገሙን ይኮንናል። “ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ” ሲል የኮነነውን ብሄራዊ ምክር ቤት “በሕገ መንግሥቱ በዐንቀጽ 51 ቁጥር 20 ላይ ፓርላማው «አንድ ወጥ የመለኪያ ደረጃዎችና የጊዜ ቀመር ያወጣል» ይላል፡፡ ይኼንን አውጥቶ ከሆነም የሕግ አወጣጥ ሥርዓትን ጠብቆ በዐዋጅ ማውጣት አለበት እንጂ በሚያሳትመው ካላንደር በኩል ሊነግረን አይችልም።” ይለዋል። ምን ዋጋ አለው ሁለቴም ፓርላማው ያወጣውን የዘመን መቁጠሪያ ተከትሎ ዘመን መለወጫን የማስፈጸም ዓቅም አነሰው ይሆን?! በሁለቱም ያፈጻጸም ችግር ታይቶበታል ፤ ምክንያቱም የዘንድሮው ጁማዓ ቀን ሳይሆን በዕለተ ቅዳሜ ነውና የዋለው። ኢትዮጵያዊውን ሙስሊም በተለይ የሰሜኑን ያገራችን ክፍል ሳስብ ብዙ ጊዜ ያስደምመኛል ፤ ሙስሊሙ ህዝብ ህይወቱን ለመምራት “በማን ሜዳ ላይ ነው የሚጫወተው?” ካልን በ”እነሱ” ነው!! “እነኛስ እነማን ናቸው?” ከተባለ ደግሞ የአማራውቹ አማራዎች ናቸዋ (ድሮ ድሮ አማራ ማለት ክርስትያን ማለት ነበር)። ሙስሊሙ ዘመን መለወጫን ብቻ ሳይሆን የወር መባቻንም በተዘጋጀለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በጥሩ አፈጻጸም በደንብ ያከብረዋል። በየወሩ ውስጥ ያሉ “የቅዱሳን” ክብረ በዓላትንም ያከባብራል። “የኢትዮጵያ የዘመን መቁጠሪያ የማን ነው?” ከሚለው መጀመር አልፈልግም። እዚያው የሚፈላሰፍ ይፈላሰፍበት። እኔ እንደሆንኩ ከላይ ያለችዋን ነገር ብየ ጥቆማ ሰጥቻለሁ ፤ በዚህ ጽሁፍ መጻፍ ያማረኝ ስለሰሜኑ አካባቢ ቅዱስ ዮሐንስ ነው።

ቅዱስ ዮሐንስ በሙስሊሙ መንደር

የዘመን መለወጫ (አዲስ አመት) ሌላኛው የአማራኛ ስሙ "ቅዱስ ዮሐንስ" ነው። የሚከበረውም ነጭ በነጭ ተለብሶ ፤ አባቶቻችን ባት ተሁለት በኩታ አጣፍተው ነው። ሴቶች ደግሞ "ባለመስቀል" ጥልፍ ቀሚስ ላይ ነጠላ አሸርግደው (ልክ "የኢትዮጵያ" ፎቶ ላይ ቡና የምታፈላው ሴት የለበሰችው ዓይነት (የኢትዮጵያ ካርታ አላልኩም ፎቶ ነው ያልኩት። እናንተ ካርታና ፎቶ ለዩንጅ! ፤ ኢትዮጵያ ካርታ ብቻ ሳይሆን ፎቶም አላት እኮ ፤ የዚያች ሴትዮ ፎቶ የኢትዮጵያም እማይደል? ፤ ሌሎቹ ሴቶች ግን ኢትዮጵያ የሚሆኑት መቼ ነው? ፤ ሐረር ፣ አፋር ፣ ሱማሌ ፣ አደሬ ፣ ኦሮሞ ... ብቻ ሆነው ሊቀሩ ነውን?!)። እነኝህ ልብሶች ባመት አንዴ ወይም ሌላ ተመሳሳይ አጋጣሚ ሲኖር ብቻ ነው የሚወጡት - ብዙዎቹ ባለ ቀይ ጥለት ናቸውምኮ - ስለዚህ ክትት ያሉ የክት ናቸው። ቀይ ጥለቱ የራሱ ትርጉም አለው። እነኝህ አልባሳት ላዘቦት ይቅርና ለሁለቱ ዒድ ወይም ነጭ እና ንጹህ ልብስ መልበስ ለሚወደድበት ጁማዓም ይወጡ ይሆናል ብላችሁ እንዳታስቡ። ማን ያውቅላችኋል?!! ሌሎቹ ልብሶች እድፍ የሚችሉ ቀለሞች ናቸው። ለክ'ት (በዓላት እና ልዩ አጋጣሚዎች የሚሆን) አንድ ልብስ ካለ ይበቃላ - እሱም ለቅዱስ ዮሐንስ የተዘጋጀው!! ለምን ቢሉ ከነስሙ ራሱ "ቅዱስ" (ቅድስናውን/ቅዱስነታቸውን እንዳትረሱት) ዮሐንስ ነዋ!! ዓመቱ ከማርቆስ ፣ ሉቃስ ፣ ወይም ማቲዎስ ወደፈለገው ይሸጋገር ዕለቱ ቅዱስ ዮሐንስ ነው። ዓመቱ ቅዱስ ዮሀንስ ነው ተብሎ በሚታሰበው የዘንድሮው ዓይነት ዘመን አብቅቶ ወደሌላኛው ሲሸጋገር እንኳ ያው መጪው አዲስ ዓመት ቅዱስ ዮሐንስ ነው። በአርቶዶክስ ክርስትና ቀመር እና አስተምህሮ መሰረት "ዘመነ ዮሐንስ" በየአራት ዓመቱ አንዴ ጳጉሜ ስድስት በሆነችበት ዓመት "ከዘመነ ሉቃስ" ቀጥሎ የሚመጣው ዓመት ስያሜ ይሁን እንጅ እንቁጣጣሽ ወይም አዲስ ዓመት ሁሌም በቅዱስ ዮሐንስ እንደተሰየመ ነው። በሙስሊሙ ማህበረሰባችን ዘንድ በ"ዕለተ ቅዱስ ዮሓንስ" ብዙ ዓይነት የስራ ቦታዎች አይከፈቱም ፤ ለዒድ ቀን ከሰላት መልስ ግልጋሎት ቢሰጥ ግን ምን ጣጣ አለው? የተባለ ይመስላል!! ለጁማዓ ሰላትስ የስራ ቦታን መዝጋት (ስራን ለጊዜው ማቆም) ለምንስ ያስፈልጋል? ብላችሁ?!! ምክንያቱም ባብዛኛው ቤት የገባው ዕሳቤ እና በህይወታችን የሰረጸው ገዥ ባህል የቅዱሳኑ እንጅ የራሳችን አይደለም። ስለ ሂጅራ ወራት እና ባመቱ ውስጥ ስላሉት ወሳኝ ኃይማኖታዊ ክንውኖች ወይም በእስልምና መንፈሳዊ ዋጋ ካላቸው የተመረጡ ቀኖች ይልቅ ለሌሎች በዓላት ያለን ዕውቀት እና አክብሮት ይልቃል።



ቅዱስ ዮሐንስን የምናከብረው በውዴታ ወይስ በክርስትያናዊ ባህል ግዴታ?

አባ ቅዱስ ዮሐንስ በዚህ ሁሉ ዘመን ስንት የእስላም የልብ ወዳጅ አፍርተዋል መሰላችሁ?!! እንዲያውም ነጭ ይሁልንዎት ወይስ ቀይ? (ቀለሙ ሊለይ ቢችልም) በግ ወይስ ዶሮ? - ከፈለጉ ሁለቱም አለ። አያስቡ! "አባታችን" እርስዎ ብቻ ይንገሩን - ብሎ አስመርጦ ሒሳብ ከፍሎ እንደሚመመገብ የሬስቶራንት ደንበኛ የሚያርድላቸው - ለዚያውም!! ኧረ ለሬስቶራንት ደንበኛ ከታረደው - የሰነባበተም ቢሆን - ተቆራርጦ ይቀርብለታል እንጅ ማን አስመርጦ "ለክብሩ በስሙ ያርድ" ብላችሁ? እኔ በስማ በለውም ቢሆን አልገጠመኝም። ታዲያ እኮ - ምናልባትም - ይሄኔ ለቅዱስ ዮሐንስ ደፋ ቀና ከሚለው ሙስሊም መካከል ብዙሃኑ እናቱ ወይ አማቱ በእንግድነት ቢመጡበት ፤ ካልሆነም ሚስቱ አማረኝ ብትለው ግን ያለው ሙሉ ዓቅም "እንስት ዶሮ ገዝቶ የሚያሳርድ ነው" ፤ ተባዕት ዶሮማ ለነ ቅዱስ ዮሐንስ በልዩ ትዕዛዝ ካለበት ስለሚፈለግ ዋጋው አይቀመስም ፤ ማንም ደግሞ እንስት ዶሮ ይቅርና እንስት በግ ለማረድ አይደፍርም - በምንልቡ። ሌላው ቁም ነገር ታዲያ ለርሳቸው ተመርጦ የሚቀርቡ እንደ ሞዴል የሚታዩ ተባዕት የዶሮ ዓይነቶች መኖራቸው ነው!! መለያቸውም - ቀይ ፣ መልከ መልካም ፣ ደረተ ጥቁር (ልበ ወርቃ) ፣ ማንቁርቱ (ከንፈሩ) ነጭ አይስከሬም መስሎ ፤ አንገቱ ላይ ያለው ተንጠልጣይ ቀይ ሐብል የበሰለ እንጆሪ የመሰለ ፤ ጉትያው ድምድም (ፍሪዝ) ፤ እግሮቹ እንደ መስታወት ንጹህና ለስላሳ ፤ ወጣት ፣ ትከሻው ደልዳላ እና ባረማመዱ ቀብራራ። ብዙ እጅግ በጣም የሙስሊም ቤት ውስጥ አባባ ዮሐንስ እና አጋፋሪወቻቸው በየጊዜው በያመቱ ደጋግመው ሲመጡ (ዓመት ዓመት ይድገሙ ፡ የከርሞ ሰው ይበላችሁ - አፌሪም "ይልመድባችሁ" እየተባሉ) የሚታረድላቸው - ኳሊቲ እንዳለው የውጭ ሐገር እቃ ዋጋው የፈጀውን ፈጅቶ- የዚህ ዓይነቱ ሞዴል ዶሮ ነበር ፤ አሁንስ ኑሮ ያሳቀቀው ግማሹ ያመጡትን ያምጡ ብሎ ችላ ያላቸው ይመስላል። ይህ ሞዴል የዶሮ ዓይነት በቅርበት ከሌለ እና በሁሉም ዘንድ ባለው ተፈላጊነቱ ምክንያት ያቅርቦት ዕጥረት ተከስቶ በቀላሉ ካልተገኘ "ከላይ እስከ ታች ነጭ የለበሰ የዘመናችንን ሙሽራ የመሰለው አንዱ ነጭ ተባዕት ሊተካው ይችላል። በግም ሲሆን የተለየ ምርጫ አለላቸው - ለቅዱስ ዮሐንሱ - (የቀይና ነጭ በግ ዋጋ ምንጊዜም ቢሆን የተለየ ነው በነኝህ ወቅቶች ደግሞ ይንራል - የታወቀ የገበያ ህግ። ግን እሳቸው አይከፍሉበት ፤ አይሞቃቸው አይበርዳቸው። መስከረም አንድ ክረምት ሊያልቅ ሲያኮበኩብ ፣ ጸሃይ ብቅ ስትል ወደ ሙስሊሙ ቤት በያመቱ ካላንደር ላይ ደግሞ ካራትቴ አንዴ ጎራ ይላሉ ። አሪፍ ወቅት መራጭ ወይም አስመራጭ ናቸው ፤ ታዛቢ ግን አይደሉም። ለነገሩ ስንት ጦም አዳሪ ታዛቢ ሞልቶ ምን በወጣቸው የሚታዘቡ። ከታዘቡም "ዘንድሮ ሳታርድልኝ ቀረክ አይደል?! ቆይ አኩርፌ'ካለሁ" ብሎ ማግባባት እና ይሉኝታ ማስያዝ ለምናቸው? ... በግልጽ "ታዝቤ'ካለሁ ፤ የልክህን አሳይ'ካለሁ ፣ ጠብቀኝ፤" ብለው ያስፈራራሉ ወይም አስፈራሪያቸውን በሰው በኩልም ቢሆን ይልካሉ እንጅ!! ህዝቤ ቅዱስ ዮሐንስን ግን ለምንድን ነው ይህን ያህል የሚፈራቸው? ካላረድኩ አለቀልኝ ብሎ መስጋቱ ከየት የመጣ ነው? ከአክብሮት ፣ ፍቅር ወይስ አድናቆት የመነጨ? ዝምድና እና ወዳጅነት ለማስቀጠል ከመፈለግ ወይስ ...? ፍርኃቱ እኮ ግን የምር ነው። የምስሳቸውን ካልገበርኩ እሞታለሁ ፣ እይያዛለሁ ፣ እታመማለሁ ፣ አንዳች ክፉ ነገር ይደርስብኛል ብሎ ማሰቡ የጤና ነው? ይህ እኮ የአምልኮ እና የአቂዳ ጉዳይም ነው።

ቅዱስ ዮሐንስን ማክበር "ኢትዮጵያዊነት" ፤ መተውስ አክራሪነት ይሆን?!

ቅዱስ ዮሀንስን ድል አድርጎ ደግሶ ማክበሩ ለመኗኗር ፣ ለማህበራዊ ህይዎት ሲባል የተወሰደ የባህል ውርርስ ብቻ አይደለም። የእምነት ማንነትን የሰለበ ሰርጎ ገብ የባህል ወረራ ቢሆን እንጅ። ሙስሊሙ ታቦት መሸኘት ብቻ አይደለም "ማህበራዊ ግዳጅ" ሆኖ የተጫነበት።

ቅዱስ ዮሀንስንም በስመ እንቁጣጣሽ አርዶ መሸኘት እንጅ! ዘመን ሲለዋወጥ ሳይሆን አራቱ ወንጌላውያን "ኢትዮጵያ መጥተው" ላመት ከርመው ሲሄዱ እነሱም ለቀጣይ ሶስት ዓመት መሸኘት ፤ በምትኩ ሌላኛውን ተቀብሎ በእንግድነት መሸኘት። ነገር ግን ሙስሊሙ ዘንድ በነሉቃስ ማቲዎስ እና ማርቆስ ስም ሁልጊዜ የሚስተናገዱት እርሳቸው ቅዱስ ዮሐንስ ናቸው። ቅዱስ ዮሐንስ ሙስሊሙ ዘንድ "ቅዱስ" ተብለው ቢታሰቡም በጣም እንደ ጦር ይፍራሉ ፤ "ቅዱስ"ም እንዲህ ይፈራል እንዴ?። በርሳቸው ቦታ ሆነው የሚያስፈራሩላቸው ብዙ ጋሻ ግሬም አላቸው። "ዘንድሮ ዓቅም የለኝም ፤ ያስለመድኩትን አላርድም" ካልክ እንዴ እንዴ እንደው የቅዱስ ዮሐንስ እለት እንኳ በሰላም ውለህ/ሽ ብታልፍ/ፊ "ከዚያስ በኋላ ምን ሊውጥህ/ሽ ነው? ባዩ ብዙ ነው። ለዚያም ነው አከባሪያቸው - እስላሙ ሁሉ - በግና ዶሮው የተወደደ ቢወደድ ፤ ከእሳቸው እና 'ደህንነቶቻቸው' ማስፈራሪያ ለማምለጥ ፤ ከሳምንታት እና ወራት በፊት አስፈላጊውን ጥንቃቄ በመውሰድ ፤ የሚታረደውን ቀድሞ ገዝቶ ቤቱ አስሮ ያስቀምጣል። ለነገር አመላላሻቸው ነገረኛ ሁሉ ያሳያል ፤ ሰውየው ላይ እኔን ለቀቅ ያድርጉ ፤ ነገር እንዳይፈልጉኝ ፤ የሚሹትን አሟልቻለሁ እንደማለት። እንጅ ዋጋውን "ተወደደ" ብሎ መተውን ማንም አይሞክራትም - ነበር!! - ነበር ያልኩበት ምክንያት - ከሚሊኒየሙና ህዳሴው ወዲህ ማለቴ ኢኮኖሚያችን የማደግ ዝንባሌ (የጉርምስና ምልክት) ማሳየት ከጀመረ በኋላ ህዝቡ በኑሮው የሆነውን እንዳያችሁት ነው ፤ ቢሆንም ሁሉም ቤት አልደኸየም እና አሁንም ድረስ በየሰፈሩ አራጅ አጎብዳጅ አይጠፋም። የቅዱስ ዮሐንስን ዓመላቸውን ሁሉም ከትዳር አጋሩ ይበልጥ በቅርበት ጠንቅቆ ያውቅላቸዋል። ህዝቡ ለያንዳንዱ የተለየ ትዕዛዝ ያስተላለፉለት ይመስል ፤ አንዱ ከሌላው በበለጠ መልኩ በየቤቱ ሽር ጉድ ብሎ ያስተናግዳቸዋል። "ቤት ያፈራውን ..." መርህ እዚህ ላይ አይሰራም። ይህ የዓረፋ ዑዱሂያ አይደለም - ያኔማ ምናለበት ከሌለህ ይታለፋል። ይህ ግን "ቅዱስ" ዮሐንስ እና ባልደረቦቹ ናቸውና እንዴት ተደርጎ በምን ስለምንስ ይሸወዳል?!!

ቅዱስ ዮሐንስ ሳያንሱ እነ አቢ-ሚካዔል በሙስሊሙ ቤት ምን ባይ ናቸው?

ደግነቱ ይህን የእኛ ቤት ሁሉ ሳይቀር ለ"ቅዱሱ" የቸራቸውን ማህበራዊ ክብር በአነስተኛ መጠንም ቢሆን በእስላሙ አማራ ውስጥ ተቀዳጅተው የሚገዳደሯቸው የሰኔ ሚካዔል (12ኛው ቀን) ፤ የሐምሌ አቦ (5ኛው ቀን - ያመቱ ቤስት) እና ህዳር ሚካኤል ...ም የሚባሉ ባለዘመን አካላት አሉ። ይህ ነገር እኮ ቀደም ሲል በቦታው እንደነበረው ዘመነ መሳፍንት ዘመን ሆነ። ሁሉም የየራሱ ግዛት እና ስልጣን አለው። ይህን ገደብ የለሽ ፤ ዘመን ተሻጋሪ የበላይነትን ድል ያደረጉ የ"ቅዱሳን"ን ጉዳይ ግን ልዩ የሚያደርገው ባንድ ህዝብ ላይ አብረው (አላልታችሁም አጥብቃችሁም አንብቡት) በተዋረድ ይሁን በጥምረት ውሉ ባልለየለት መልኩ ባንድ የግዛት ዘመን የነገሱ የብዙ ነገስታት ሰንሰለት መምሰሉ ነው። ይህ ደግሞ ላንዳንዱ አግራሞትን ለሌላው ደግሞ እንዳቅሙ ቁጭትን ሊያጭር ይችላል። ይህን ማውገዝ ደግሞ አክራርነት እና ማህበራዊ ሰላም አደፍራሽ እንዳያስብል እንጅ!! በሉ ለማንኛውም ለመቻቻል ስንል ነው ከበዓል ማግስት የጻፍነው ብለን እናስተባብል እንዴ?! ኧረ ጉድ! እንዲህም መቻቻል አለ። ብቻ ቸሩ የእስላም ህዝብ ለሁሉም በረዶ የመሰለ አበባ ቆሎ (ፈንዲሻ በዘመንኛው ቋንቋ) ፤ እንደወሎው ጠላ ባይዘወተርም ታናሽ ወንድሙ ቡቅር/ቡቡኝ/ቀሪቦ/የሃገር ውስጥ 'ኮካ' የመሳሰሉ ስሞች ሊሰጡት የሚችል ባህላዊ መጠጥ ከሳምንታት በፊት ተዘጋጅቶ በጉጉት ይጠብቃቸዋል። በዛሬ ጊዜ አየር ማረፊያዎች ላይ ሰውን ባበባ መቀበል አዲስ እንዳይመስል - ስንትና ስንት ጊዜ አባ ዮሐንስን ህዝብ በነቂስ ወጥቶ በእንቁጣጣሽ (አደይ አበባ) ተቀብሏቸው እያለ?። ወይ ጉድ! "ሰው ካላስተዋለ በመንገድ ላይ የወደቀ ሳንቲምን ሳያይ ያልፋል" አሉ። ምን በአበባ ብቻ ቤት ሲገቡ ደግሞ - ከነ ጭስና ጉዝጓዙ - ቄጤማው- በየቤቱ ከነድ/ሰንደል ጋር ይጨሳል ይጫጫሳል - ለእርሳቸው። እዚያ የሚከበሩት ቅዱስ ዮሐንስ ብቻ ና ብቻ ናቸው - ሉቃስ ፤ ማርቆስ ፤ ማቲዎስ ተቀያየሩ በዚያው ቀጠሉ ለሙስሊሙ አማራ ሃጃ የለም - የሳቸው ብቻ ሞሃባ በልቡ ላይ ነግሷል። መገን አለማለቱ ብቻ ነው ቀረ ሊባል የሚችለው። አንዴ ተለክቶ የተሰፋለት ፤ ተሞልቶ የተሰጠ መከረኛ ዮሐንስ ላይ ደም ይፈሰሳል (አንገቱ የተቆረጠው (አንገት ቀዩ) እኮ አይደለም - 'ቅዱሱ' ላይ ነው እንጅ!! ያኛውማ ቅዱስ ነው እንዴ? እናንተ ደግሞ አበዛችሁት። እናንተየ ያኛው ዮሐንስ አንገቱን እንደታረደው ፤ እነዚህ እንቁጣጣሽን አስታከከው በቅዱስ ዮሃንስ ስም ዶሮ እና በግ የሚያርዱ ሙስሊሞች በያመቱ ሃዘናቸውን (ደስታቸውን እንዳትሉ) በየሙት ዓመቱ እየገለጹ ይሆን ወይ?!! እስኪ ከመተማ ይዛችሁ ወደዚህ ቀን ቁጠሩ!! ወይስ እንዳይነቃባቸው በዚችኛዋ ዮሀንስ ተጠልለው ነው። በሉ ከፈለጋችሁ እዚያው ድረስ ሄዳችሁ ራሳችሁ አጣሩ - ፊደል የቆጠረ ሰው ሰውን አያምን መቼም። እንጅ ብታምኑኝ ኖሮ በቀላሉ ግልግል ብንል መልካም ነበር። ይህን ሁሉ ለምን እከትብ (አንዳንዶቹ ከትባት አድርገውም ከቆጠሩት መልካም) ነበር። ታዲያ "ይህን የመስከረም አንድ 'ኡዱሂያ' (ዋጅብ እንጅ ሙዓከዳ ነው ፤ ሱና ነው ብሎ ማወላወል የለም)"። ሰው ዋጅብን ሲተው ይጠይቅበታል አይደል?! ስለዚህ ላለመጠየቅ ሁሌ ማረድ የውዴታ ሳይሆን የግዳጅ ግዴታ ነው። ... አዋጅ!!! እናንተ ሰዎች ሆይ!! በደርግ ዘመን በግዳጅ ነው በውዳጅ ይከበር የነበረው መስከረም ሁለት እንጅ አንድ አይደለም። ስለዚህ በመስከረም አንድ አርዶ ኃዋርያንን ማክበርን ዋጅብ ያደረገው አስገዳጅ ሐይል ደርግ እንዳይመስልና ነገር እንዳይበላሽ። ... ቢቃ ደርግ ባያስገድድም ከዚያ በፊት ካለው ይዞ ያን እለት "ካልታረደ አዲጋ አለው" ተብሏል። ጸጥ ለጥ ብሎ ሁሌም ማረድ ነው ፤ ካልሆነ ይጣላኻል ትባላለህ። ማንም ደግሞ ከአላህ ጋርም ሆነ ተው ለባዕድ አካላት አትረድ ከሚለው ሙስሊም ጋር ቢጣላ ይሻለዋል እንጅ "ከቅዱስ ዮሐንስ" ጋር መጣላት አይፈልግም። "ኧረ ሽርክ (የባዕድ አምልኮ) ነው" ብትል ከተጣላኝ አካል "አንተ ታስጥለኝ ይመስል" መደበኛ መልስ ነው። ሳያውቀው የተሸከመውን በአገራዊ ካባ የተጀቦነ መሸንገያ ልትገፍለት ሳይሆን ፤ እስልምናውን ልታፈርስበት የከጀልክ ይመስለውና ወሃቢ - እልፍ ካለም "የሙስሊም ጴንጤ" - ብሎህ እርፍ ይላል። ሌላኛው ወገንም አንድ ካባ ለብሰን ከኖረው የቅዱሳኖቻችን ወዳጆች ጋር ልትለያዩን የምታስቡ ሊሉህ ይዳዳቸዋል። በሌሎች ካባ ውስጥ ያሉትን እና የራሳቸውን የእስልምና ካባ ለብሰው የጠራ ማንነት የሚሻ ሁሉ አክራሪ ፤ ጽንፈኛ እና አሰባሪ ተብሎ ይቀጸልለታል። አዎ አክራሪ ነኝ ፤ በሉኝም ጽንፈኛ ፤ ቅዱስ ዮሐንስን ፤ ማላከብር ቀበኛ ፤ በኢትዮጵያዊ ሽፋን የክርስትያን ባህል ፤ ላላከብር ወሰንኩ አሸባሪም ብባል። ከማለት ውጭ አማራጭ የለም።

ብቻ ቸሩ የእስላም ህዝብ ለሁሉም በረዶ የመሰለ አበባ ቆሎ (ፈንዲሻ በዘመንኛው ቋንቋ) ፤ እንደወሎው ጠላ ባይዘወተርም ታናሽ ወንድሙ ቡቅር/ቡቡኝ/ ቀሪቦ/የሃገር ውስጥ 'ኮካ' የመሳሰሉ ስሞች ሊሰጡት የሚችል ባህላዊ መጠጥ ከሳምንታት በፊት ተዘጋጅቶ በጉጉት ይጠብቃቸዋል።



ተቅዋ የህይወት ሰንቅ

ሙሰሊሙ ህብረተሰብ መካከል የተፈጠረውን የመንፈሳዊ አስተምህሮ ክፍተትን በጥቂትም ቢሆን የመሸፈንን አላማ ያነገበ ከተንጣለለው የኢስላም አድማስ አንገብጋቢ ርዕሶችን በመምረጥ በጥበብ በማስተማር በእለት ተዕለት ህይወታችን ተግባራዊ የሚደረግበትን ስልቶች መጠቆምን ያለመ ዓምድ ነው።

(በሰዒድ ካሚል

ህይወት አቀበትና ቁልቁለት የሞላባት መሆኗ ያለና የነበረ ነው። የሰው ህልውና ምሶሶና ማገሩ ህይወት ውጣ ውረድ ያለባት እንድትሆን በማድረጉ ዙሪያ የተማከለ ነው። እናም አንድ ጊዜ ችግርና መከራን ሌላ ጊዜ ደግሞ ሀብትና ምቾትን የሰው ልጅ ያስተናግዳል። ሀዘንና ጭንቀት የሚገርፉት ያክል ደስታና ፍሰሀም ይጎበኙታል። ከሞላ ጎደል የዚህችን አለም አካሄድ ካስተዋልናት ሰው ከደስታው ይልቅ መከራው ፣ከፍሰሀው ይልቅ ጭንቁ የበለጠ ሆኖ እናገኘዋለን ። ታዲያ የህይወትን ሚዛንን ጠብቆ መኖርና የመከራና የጭንቅ ጊዜው እንዴት ነው የሚታለፈው የሚለው የሁሉም ጥያቄ ነው። መልሱን ቁርዐን እንዲህ ሲል ይነግረናል።

“አላህን የሚፈራ ሰው ለርሱ መውጫን ያደርግለታል “(ሱረቱል ጠላቅ፣2)

አንድ ጊዜ የሆነ ሰው ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.)መጣና እንዲህ አላቸው የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ጉዞ ላደርግ ነውና ዱዐ ያድርጉልኝ አላቸው። ረሱሉም “አላህ ተቅዋን ይስጥህ “ሲሉ ዱዐ አደረጉለት። ሰውየው ሌላ ዱዐ እንዲጨምሩለት ፈለገ። ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ.)”አላህ ሀጢያትህን ይማርልህ “በማለት አከሉለ ። በዚህ ጊዜ ይህ ባልደረባቸው ፡ -“እናትና አባቴ መስዕዋት ይሁንልዎ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ እባክዋ አሁንም ይጨምሩልኝ” አላቸ። የአላህ መልዕክተኛም(ሰ.ዐ.ወ.) “ የትም ሆነህ መልካም ነገር መስራት ትችል ዘንድ አላህ ያግራልህ “ ሲሉ ጨመሩለት። ረሱሉ(ሰ.ዐ.ወ.) ለዚህ ባልደረባቸው በመጀመሪያ ያደረጉት መሰረታዊ ዱዐ ተቅዋን በሚመለከት ነው። ከዚያም ሀጢያቱ ምህረት ያገኝ ዘንድ ፀለዩለት ።በመጨረሻም በየትም ስፍራና ጊዜ መልካም ስራ መስራትን ገር እንዲያደርግለት አላህን ለመኑለት። ይህ ማለት አንድ ሰው ተቅዋ ካለው ለሀጥያቱ ምህረት ማግኘትም ሆነ መልካም ስራ ለመስራት መገጠሙ ቀላል ይሆንለታል ማለት ነው። ታዲያ ተቅዋ ማለት ምን ማለት ነው ?

አራተኛው ኸሊፋ የሆኑት አሊይ ኢብኑ አቡጣሊብ ተቅዋን አላህን መፍራት ፣ባወረደው መፅሀፍ መስራት፣በተገኘው መብቃቃትና ለፍርዱ ቀን መዘጋጀት ነው ሲሉ ገልፀውታል።

የአላህ ወዳጅ የሆኑ ቀደምት አበው ተቅዋን በብዙ መንገድ ይተረጉሙታል። ቃሉ በግርድፉ ሲተረጎም ራስን ከማንኛውም አይነት አላህን የማያስደስት ከሆነ ደርጊትና ንግግር ማቀብ ፣መጠበቅና ማራቅ ማለት ይሆናል። ተቅዋ ብለን የምንጠራው አንድ ሰው አላህ የከለከላቸውን በመራቅ ያዘዘውን አቅሙ በፈቀደለት መሰረት በመስራት የእርሱን እገዛ በመሻት የሚያገኘው ጥቢቃና ከለላ ነው ማለት ይቻላል። ይህም በመሆኑ ተቅዋን በራስ ላይ ለማምጣት ስጋዊ ፍላጎትንና የነፍስን ዝንባሌ በመግታት ለመንፈሳዊ ህይወት ከፍ ያለ ዋጋና ትርጉም መስጠትን ይጠይቃል። ተቅዋ የኢስላምን የስነ-ምግባር መርሆዎች በሙሉ ልብና ፍላጎት መተግበርን ፣አላህን መፍራትና በተገኘው መብቃቃትን ያመላክታል። አራተኛው ኸሊፋ የሆኑት አሊይ ኢብኑ አቡጣሊብ ተቅዋን አላህን መፍራት ፣ባወረደው መፅሀፍ መስራት፣በተገኘው መብቃቃትና ለፍርዱ ቀን መዘጋጀት ነው ሲሉ ገልፀውታል። ኢብኑ መስዑድም (ያ አዩሀለዚነ አመኑ ኢተቁላህ ሀቀ ቱቃቲሂ ወላ ተሙቱነ ኢላ ወአንቱም ሙስሊሙን)የሚለውን አንቀፅ ሲያብራሩ ተቅዋ ማለት አላህን መታዘዝ እንጂ አለማመፅ ፣እርሱ ማስታወስ እንጂ አለመርሳት ፣እርሱን ማመሰገን እንጂ አለመርሳት ነው ብለዋል፡ ፡ ሀሰነ በሰሪ (አላህ ይዘንላቸው) ተቅዋ ያለው ሰው አላህ ያዘዘውን ይሰራል ። የከለከለውን ደግሞ ፈፅሞ ይርቃል። በርካታ የተፈቀዱ ነገሮችን ሀራም ላይ እንዳይወድቅ በመስጋት ይተዋል ያሉ ሲሆን ሱፍያን አስ-ሰውሪ (አላህ ይዘንላቸውና)ተቅዋ ስላላቸው ሰዎች ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል አላህን የሚፈሩ ሰዎች ተቅዮች ይባላሉ ምክኒያቱም ብዙሀኑ ሰው የማይፈራውን አላህ ፈርተዋልና። አምስተኛው ኸሊፋ እንደሆኑ የተመሰከረላቸው ዑመር ኢብኑ አብዱል አዚዝ ደግሞ ተቅዋ ቀን መፆም ለሊት ቆሞ ማሳለፍ አይደለም። ከዚያ ይልቅ የከለከለውን ነገር መታቀብና በትዕዛዙ ላይ ቀጥ ማለት ነው። ከመታዘዝ የላቀ ነገርን ያገኘ ሰው በፀጋ ላይ ሌላ ፀጋን ተሰጥቷል። በማለት ገልፀውታል። የኢብኑ ረጀብ አስተያየት ደግሞ የተለየ ነው። እንዲህ ይላሉ ፡-የተቅዋን ፅንሰ ሀሳብ ስንመረምረው ከአላህ ቁጣ ለመዳን በራስ ላይ ጋሻን ማበጀት ሆኖ እናገኘዋለን። ያ ጋሻ ደግሞ ሌላ ሳይሆን አላህን

መታዘዝና ከክልከላዎቹ መራቅ ነው፡፡ እውነተኛ ተቅዋ ያለው ሰው ሁሉንም ግዴታ የሆኑበትንና ሱና የሆኑ ተግባራትን የሚፈፅም ሲሆን ሀራም ከሆኑ ነገሮችና ከአጠራጣሪ ጉዳዮች መራቅ ይኖርበታል፡፡ ተቅዋ ለአንድ አማኝ ሰው ከስንቆች ሁሉ በላጩ ሲሆን እርሱ ካለፈ በኃላም ለልጆቹና ለዝርያዎቹ የሚተላለፍ መለኮታዊ በረከት ነው፡ ፡ ተቅዋ የአላህን ውዴታ መሸመቻ ካፒታል ነው፡ ፡ የሰው ልጆች ልቅና መስፈሪያ ሚዛንም ነው፡፡

የህይወት ሰንቅ፤የስኬት ቁልፍ


እምነት የአዕምሮ ብርሀን ነው ፡፡የህሊና መወልወያ መሳሪያ ነው ፡፡ልብን ማለስለሻ ቅባት ነው ፡፡አላፊና ጠፊ ከሆነችው ከዚህቸኛዋ አለም ወደ ቀጣዩ ዓለም በስኬትና በደስታ ለመጓዝ ልባዊ እምነት ወሳኝ ነው ፡፡የእምነት ብርሀን የተነፈገች ነፍስ መጨረሻ ውርደት እንጂ ሌላ አይደለም ፡፡ የሰው ልጆች በምድር ላይ ህልውና አግኝተው መኖር ከጀመሩ አንስቶ ያለ እምነተ እንዳይባዝኑና እንዳይዋትቱ – መለኮታዊ አመራርና ነብያት በየዘመናቱ ሲላኩላቸው ቆይተዋል ፡፡የአላህ ወዳጆች በነዚህ ሁለት መመሪያዎች እየታገዙ የህይወታቸውን ቅኝት ሲያስተካክሉና ሲመላለሱ ኑረዋል ፡፡እየኖሩም ነው ፡ ፡ እምነት ሲባል ከመለኮት የሚሰጥ የሆነ ምርጥ ፀጋ ነው ፡፡በምድር ላይ የሰው ልጅ ፈተናዎች ያጋጥሙታል ፡፡አንድ አማኝ በመከራና በፈተና ጊዜያቶች የሚያሳየው ትዕግስትና የአላህን ፍርድ ወዶ መቀበሉ በመጪው አለም ለሚያገኘው ታላቅ ሽልማት እንደሚከፍለው ቤዛ ይቆጠራል ፡፡የአለማት ጌታ አላህ ባሮቹ የሚከፍሉትን ይህን መስዕዋትነት እንደ ታላቅና እምነታቸውን ከፍ የሚያደርጉበት አጋጣሚ በማየት ከፍ ያለ ዋጋ ይሰጠዋል ፡ ፡ ቃሉም አላህ ከምዕመናን ነፍሶቻቸውንና ገንዘቦቻቸውን ገነት ለነርሱ ብቻ ያላቸው በመሆኑ ገዛቸው ይላል፡፡ በህይወት አውድ ላይ አማኞች የሚያጋጥማቸውን ፈተናና ትግል በፅናት ተቋቁመው በአላህና በመልዕክተኛው መንገድ ላይ በመሆን ፍፃሜያቸውን በዚሁ ረከተው እንዲያሳርጉ ይጠበቅባቸዋል ፡፡ እያንዳንዱ አማኝ የሆነ ሰው የልቅና ባለቤት የሆነውን አላህን ውዴታ ለማግኘትና ተቅዋን ለመላበስ ብዙ ዋጋዎችን የመክፈል ግዴታ አለበት ፡፡አንድ ሰው ያልለፋበትንና ምንም ዋጋ ያላወጣበትን ነገር የራሱ ለማድረግ በመጣሩ ግዜውን ያለ አግባብ ከማባከን ውጪ ምንም የሚፈይደው ነገር የለም፡፡ በእምነት ደረጃዎች ወደላይ ከፍ ለማለት መልካም ስራዎችን አብዝቶ መስራት እና ዘውታሪ መሆን የግድ መሆኑን ማወቁ ጥበብ ነው፡ ፡ መልካም ስራ ማለት የተስተካከለ አቂዳ ፣ ሰናይ ምግባር ፣እውነተኛ ኒያ ፣አላህን የሚያስደስት የሆነ ንግግርና ድርጊት እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ ለዚህም ነው በቁርዐንና በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.)ሀዲሶች እምነትና መልካም ስራ ተቆራኝተው የሚጠቀሱት፡፡ እምነት ሲባል እንዲሁ ደረቅ የሆኑ ሀቆችን በነባቤ ቃል ማነብነብ ሳይሆን ሀቅን መረዳት ከዚያም በልብ ውስጥ አምኖ መቀበል ፣እንዲሁም በስብዕና ላይ በማንፀባረቅ መግለፅ ነው፡፡ እምነት ከአምልኮ ይልቅ ከፍ ያለ ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ነው ፡ ፡አላህን እንደሚገባውና እርሱ እንደሚፈልገው አድርጎ ማምለክ የሚቻለው ንፁህ እምነት ሲኖር ነው፡፡ አምልኮትን ለመከወን የሚያሰፈልጉት ጊዜያት ከቀን ውስጥ የተወሰኑት ናቸው፡፡ ለምሳሌ ሰላትን ብንወስድ የሚሰገደው በቀን ውስጥ ለአምስት ጊዜ ብቻ ነው ፡፡እምነትን ካየን ግን በእያንዳንዷ ቅፅበት በልባችንና በስብዕናችን ውስጥ የሚያድርና የሚገለፅ ረቂቅ ነገር ነው፡፡ ለዚህም ነው ልባችንን ከሚያደነዝዙና ግዴለሽ እንድንሆን ከሚያደርጉ ኃጢያቶች ሁልጊዜም መራቅና መጠንቀቅ የሚኖርብን፡፡ እንዲሁም እምነታችን እንዲያብብና እንዲያፈራ በየጊዜው መልካም ምግባራትን እየፈፀምን መንከባከብ አለብን፡፡ የእምነትን ጌጥ በልቡ ማኖር ለአንድ አማኝ ሰው ከምንም በላይ ታላቅ የሆነ ሀብቱ ነው፡ ፡ ልባችንን መጠበቅ ከቻልን ሁልጊዜ በእምነት የጋለና በጎ ምግባራትን ለመከወን የተነሳሳ ይሆናል ፡፡በመልካም ስራ ላይ ዘውታሪ በመሆንም የማይናወጥ አቋም ይኖረዋል፡፡ የእምነታችን ጌጥ እንዲጎላና ይበልጥ እንዲደምቅ የአላህን ታላቅነት ማወጅና በጎ ምግባራትን ማብዛት እንዲሁም አላህን ዘወትር ማስታወስ ይኖርብናል፡፡ ይህ ልብን ከገፍላና ግዴለሽነት ያላቅቀዋል ፡፡የእምነት ጥፍጥናን ማጣጣም ተቅዋን መሰነቅ ያስችላል፡ ፡ ፍፁማዊ የሆነ ሰላምና መረጋጋት ያላብሳል፡ ፡ ተቅዋን የታደሉ ባሪያዎቹ ፍቃዱን በመሙላት የምጥቀት ደረጃ ላይ በመድረሳቸው በዚህ አለም የሚገጥማቸውን ችግርና መከራ አሳንሰው ነው የሚያዩት፡፡ ምክኒያቱም በሞት፣በቀብር ውስጥና በዚያኛው ዐለም ያለውን መከራ ከዚህችኛው አለም መከራ ጋር ሲያነፃፅሩት የዚህችኛው አለም እዚህ ግባ የሚባል ሆኖ ሰለማያገኙት ነው፡፡ በፈረአን ጊዜ የነበሩ አሰማተኞች የነብዩላህ ሙሳን ተዓምር ካስተዋሉ በኃላ የእርሱን አምላክነት በማስተባበላቸው ሊሸከሙት የሚከብድ ቅጣት ሊቀበሉ ግድ ሆነ፡፡ ይሁን እንጂ እነርሱ ይህንን መከራ ከተስተካከለው እምነታቸው በመነጨ ድፍረት ፊት ለፊት ተጋፈጡት፡፡ ወደ ኃላ አላፈገፈጉም፡፡ አንባገነኑን ፈርዐውን ከመጡልን ተዐምረኞችና ከዚያም ከፈጠረን አምላክ ፈፅሞ አንመርጥህም፡፡ አንተም የምትፈርደውን ፍረድ፡፡ የምትፈርደው በዚህች አነስተኛይቱ ህይወት ብቻ ነው አሉት ፈረኦንም የእነዚያን ሰዎች እጅና እግሮች እያፈራረቀ ቀኝ እጅና ግራ እግር ወይም ግራ እጅና ቀኝ እግር ቆረጠ፡፡ በዘንባባ ግንዶች ላይ ከመሰቀላቸው በፊትም የቀራቸውን እጆች ወደ ሰማይ ከፍ አድርገው በጌታቸው ፊት ፍፁም በመተናነስ ጌታችን ሆይ በእኛ ላይ ትዕግስትን አፍስስ፡፡ ሙስሊሞችም ሆነን ግደለን አሉ፡፡ በቅፅበት የተገኘች እምነት ልብ ውስጥ በመስረፅዋ የህይወት ሰንቅ ሆና ከስኬት አድማስ አሻገረች ፡፡

መንገድ ባይተዋር ሆና ኖረች። በመጨረሻም አላህ (ሱ.ወ.) ደስታና ሀሴትን ላከላት። አዎን! የባይተዋሮች መጨረሻ እንዲህ ነው። በበብዙ መጥፎ ሰዎች መካከል የሚኖሩ ባይተዋሮች መጨረሻቸው ድል ብቻ ነው። የመልካም ሥራ ባለቤቶች ስለሆኑ ብቻ በሰዎች መካከል ባይተዋርና እንግዶች የሆኑ ሴቶችም ይሁኑ ወንዶች የአላህ ባሮች በዲናቸው ላይ ከፀኑና ከታገሱ ፣ የአላህን ቃልኪዳን ከተጠባበቁ መጨረሻቸው ስኬት ብቻ ነው። በእሳት ላይ እየሄዱ ፍም ጨብጠው የኖሩ ፣ ዓይኖቻቸውን ማየት ካልተፈቀደላቸው ነገር ዝቅ ያደረጉ ፣ ብልቶቻቸውን ከዝሙት የጠበቁ ፣ ሐራም ከተባለ ነገር ሁሉ የሸሹ ፣ በመጨረሻም ብስራትና ደስታ ይላከላቸዋል። በሀብት ፣ በልጅ ልጆቻቸውና በዝርያዎቻቸው ሁሉ ይባርከላቸዋል። የኢስማዒል እናት ውሃውን ባገኘች ጊዜ ተረጋጋች። በከዕባ ዙሪያም የመጀመሪያዋ ሰፋሪ ሆነች። የአሞራዎችን በአካባቢው ላይ ማንጎበብ ያዩ መንገደኞች ‹በዚህ አካባቢ ውሃ አለ ማለት ነው› በማለት በመካ ሠፈሩ።

በዚህ መልኩም የነቢዩ ኢብራሂም ባለቤት ሃጀርና ልጃቸው ኢስማዒል ለቅድስቲቷ የምድራችን ከተማ መካ መቆርቆር ምክኒያት ሆኑ። የነቢዩ ኢብራሂም ልጅ ከሆኑት ነቢዩ ኢስማዒል የዘር ሀረግ ደግሞ የዓለማችን ሁሉ እዝነትና በረከት የሆኑት ታላቁ ነቢይ ነቢያችን ሙሀመድ ሰ.ዐ.ወ ተወለዱ።

ከስኬታማ ወንድ ጎን ጠንካራ እንስት አለች

ዓምዱ ጾታ ነክ ርዕሰ ጉዳዮች እየተነሱ ለውይይት የሚጋብዙ ጽሁፎችን ያስተናግዳል። የታላላቅ ሴት ስብዕናዎችታሪክይዘከርበታል። የሴቶችን ማህበራዊ ሚና የሚያጎሉ ሐተታዎች እየቀረቡ ለማህበረሰባችን ዕድገትየሚረዱ ዕሳቤዎች ይቀረጹበታል።



(መርየም ኡሽተል ፈትህያ)

ከስኬታማ ወንድ ጀርባ ጠንካራ ሴት አለች የሚለው አባል ሴቶች ያላቸውን ሚና በጉልህ ያሳያል በሚል በስፋት ጥቅም ላይ ይውላል፡ ፡ የኢስላማዊ ታሪክ የሴቶች ሚና ትርክት ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ ሴት ከወንድ ልጅ የነን አጥንት እንደመፈጠሯ በህይወት ውስጥ የሚኖራት ሚና የሚገለፀው ከስኬታማ ወንዶች ጎን ጠንካራ ሴት አለች በሚለው ነው፡፡ አብሮነት ፣ያልተቋረጠ ድጋፍን ስንገልፅ ሁሌም ከጎኔ የሚለው ቃል ቀዳሚ በማድረግ የሆነውም ለዚህ ነው፡፡ ከኃላ በመሆንና ከጎን በመሆን መካከል ሰፊ ልዩነት አለ፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ሰ.ዐ.ወ. ውድ ባለቤት የሆነችውን ኸዲጃ ሚና ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ.)ጎን ነበረች ብለን እንጂ ከኃላ አይደለም፡ ፡ ከኃላ ያለ አካል ሚናው መደገፍ ብቻ ነው፡፡ ከጎን ያለ ግን ከድጋፍ ባሻገር ቀጥተኛ ተሳትፎም አለው፡፡ ከቁርዐን በመቀጠል ለኢስላማዊ አስተምህሮ ምንጭ የሆነውን ሀዲስ ለትውልድ በማድረስ የረሱል ውድ ባለቤት የሆነችው አሚሻ የተጫወተችው ሚና ጉልህ ነው፡፡በሺ የሚቆጠር ሀዲስ አስተላልፋልናለች፡፡ የቁርዐን ፍቺ የሆነውን የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.)የህይወት ታሪክ ለትውልድ በማድረስ ሚናዋ ከኃላ ድጋፍ መሆን ብቻ ሳይሆን ከጎን የቀጥታ ተሳታፊነት ነበር፡፡ እንደ የፀደይ ሰማይ ከተንጣለለው ሰማያዊ ከሆነው የኢስላም ታሪክ ውስጥ ሴት ልጅ የነበራት ፋና ጉልህ ነው፡፡ ከስኬቶቹ ሁሉ ጎን ነበረች፡፡ በታሪክ ምዕራፍ ላይ ዘመናትን ተሻግረን ተጉዘን ከወርቃማው ዘመን ውስጥ ካለ ወርቃማ ታሪክ አንድ አብነት እንመልከት፡፡

ኸሊፋ ተደርጎ ከመሾሙ በፊት ይኖር የነበረው ህይወት በምቾት የተሞላ ነበር፡፡ ሹመቱን ካገኘ በኃላ ግን ተቀይሯል፡፡ ብዙዎች ስልጣን ሲያገኙ ህይወታቸው በድሎት ይሞላል ፡፡የርሱ ግን በተቃራኒው ነው የሆነው፡፡ አምስተኛው ኸሊፋ እየተባለ የሚወደሰው ዑመር ኢብኑ አብዱል አዚዝ፡፡ የኡመር ኢብኑ አብዱል አዚዝ የኸሊፋነት ጊዜ በፍትህና በስኬት የታጨቀ ነው፡፡ የታሪክ ድርሳናት ስሙን ከፍ አድርገው ነው የሚያወሱት ፡ ፡ የዑመር የስኬት ታሪክ ሲወሳ ታዲያ የ ባ ለ ቤ ቱ ም የፋጢማ ቢንት አብዱል መሊክ ታሪክም አብሮ ይወሳል፡ ፡ ፋጢማ የተወለደቸው ቤተመንግስት ውስጥ ነው፡፡ አስተዳደጓ በምቾት የተሞላ ነበር፡ ፡ የምትመገበው በብር ማንኪያ ፣የምትዋበው በወርቅ ነበር፡ ፡ ይህች እንስት ከዚህ የምቾት ህይወት ወጥታ ከአብደላህ ኢብኑ ዑመር ጋር ያሳለፈችው ህይወትና ለርሱ የነበራት እገዛ ወርቃማ የሆነ ተምሳሌት ነው፡ ፡ በአንድ ወቅት አንዲት የየቲም ልጆች አሳዳጊ የሆነች እናት ለልጆቿ የሚሆን ወርሀዊ አበል አንዲቆርጥላት ለመጠየቅ ከኢራቅ ተነስታ ኸሊፋው ድርስ ትመጣለች፡፡ አጠያይቃ ወደቤቱ እንደደረሰች የአብደላህ ኢብኑ ዑመር ባለቤትን ዳቦ ለመጋገር በማሰብ እሳት ለማያያዝ ስትቸገር ተመለከተቻት፡፡ ቤታቸውም ስትመለከት ምንም የሌለው ባዶ ቤት ነው፡፡ እጅግ አዝና እርዳታ ፍለጋ ነበር አመጣጤ ነገር ግን ከኔ የባሱ ችግረኞች ቤት ነው የመጣሁት ብላ ተናገረች ፡፡ በዚህ ጊዜ ፋጢም ቢንት አብዱልመሊክ የመጣሽው ትክክለኛው ቦታ ነው፡፡ የኛ ህይወትን አጉደለን ነው የዑማውን ህይወት የምንሞላው በማለት ወደ ባለቤቷ ወስዳ ከበይተል ማል እርዳታ እንዲሰጣት አደረገች፡፡ ፋጢማ የዝነኛው ንጉሥ አብዱልመሊክ ልጅ የነበረች ቢሆንም ባልዋ ጥቅማቸውን ወደ ጎላ ጥለው በህዝበ ሙስሊሙ ጥቅም ሲለውጡ ያለምንም ማማረርና መሰላቸት ከባሏ ጎን በመሰለፍ ከምቾት ህይወት ወጥታ በየአይነቱ የዱኒያን ችግር ስትጎነጭ ቆይታለች። ዑመር ኢብኑ አብዱል አ ዚ ዝ ከሹመታቸው በ ፊ ት የነበራቸውን ሀብትና ንብረት ለበይተል ማል ያስገቡ ሲሆን አገልጋዬቻቸውን አንዱን ብቻ አ ስ ቀ ር ተ ው ሁሉንም ነፃ አውጥተው ነበር፡፡ ይህም አገልጋያቸው ቢሆን ድህነታቸው ጥግ ከመድረሱ የተነሳ መቋቋም ተስኖት ጥሎ ለመጥፋት ተገዷል፡፡ በአንድ ወቅት ፋጡማ ለዚህ አገልጋያቸው ምግብ አዋረበችለት ልጁም ስልችት በማለት “ ኡፍ ሁልጊዜ ምስር!

ፋጢማ የተወለደቸው ቤተመንግስት ውስጥ ነው፡፡ አስተዳደጓ በምቾት የተሞላ ነበር፡ ፡ የምትመገበው በብር ማንኪያ ፣የምትዋበው በወርቅ ነበር፡፡ ይህች እንስት ከዚህ የምቾት ህይወት ወጥታ ከአብደላህ ኢብኑ ዑመር ጋር ያሳለፈችው ህይወትና ለርሱ የነበራት እገዛ ወርቃማ የሆነ ተምሳሌት ነው፡

ሁልጊዜ ምስር! “ በማለት ምስር መብላት ብቻ ያሰመረረው መሆኑን ተናገረ:: ፋጡማም እንዲህ ስትል መለሰችለት “ ልጄ ሆይ ! ይህ ለአሚር አልሙእሚኒን የሚቀርብ ምግብ ነው ! ሌላ ምግብ የለኝም “ በማለት መለሰችለት።የኡመር ኢብኑ አብዱልአዚዝ ዘመን ድሃ ጠፍቶ እባካችሁ ዘካ ተቀበሉን እያሉ ሃብታሞች በአፍሪካና በኤስያ ሲዞሩ ሁሉም በድሎት ስለሚኖር ሶደቃና ዘካን የሚቀበል የጠፋበት ዘመን ነበር ። የዑመር ኢብኑ አብዱል አዚዝ ጎጆ ግን ይህ ይመስል ነበር :: የዚህ ጎጆ ልዕልት ደግሞ ፈጡማ ቢንት አብዱል መሊክ ነበረች:: ከእለታት ላንድ ቀን አሚር አልሙእሚኒን ወይን ላማራቸውና ሚስታቸውን “ አንቺ ፋጡማ ወይን የምንገዛበት ዲርሃም (ገንዘብ) የለሺም?” ብለው ጠየቋት እሷም መልሳ “ አንተ አሚር አልሙእሚኒን ከሊፋ ሆነህ ወይን የምትገዛበት ገንዘብ እንዴት የለህም?” ስትል ጥያቄያቸውን በጥያቄ መለሰችላቸው :: እሳቸውም መልሰው “ እባክሽ ከዚች መሬት በስተቀር ምንም ነገር የቀረኝ የለም ከእሷም የማገኘው ገቢ በቂ ላልሆነልኝም። ይሁን እንጅ አሁን ፍላጎቴንና ላምሮቴን መቆጣጠሬ ነገ ጀሃነም እሳት ውስጥ ከመግባት ይሻለኛል “ በማለት መለሱላት። ኸሊፋው ሁሉንም ንብረታቸውን ወደ ቤተልማል ከመለሱ በኋላ ከእሷ ጋር የቀረ ንብረት የዚህች ልዕልት ጌጣጌጥ ብቻ ነበር። ዑመር በሃላል ላላገኘሁትም ብለው ያሰቡትን ነገር ሁሉ መልሰው ባዶ እጃቸውን ቀርተዋል ነገር ግን የፋጡማ ጌጣጌጥ ያሳስባቸው ነበር። ከእለታት ላንድ ቀን እንዲህ በማለት እንቅጩን ለፋጡማ ተናገሩ “ ፋጡማ ሆይ ! እንደምታውቂው እነዚህ አንቺ የምታጌጭባቸው ጌጣጌጦች ኸሊፋ የነበረው አባትሽ ከሙስሊሞች ንብረት (ከቤተል ማል) በመውሰድ እንደገዙልሽ ታውቂያለሽ እኔ ደግሞ በእንደዚህ ላይነት ሁኔታ የመጣ ንብረት ሁሉ ቤቴ ውስጥ እንዳይቀመጥ በጣም እጠላለሁ። ስለዚህ ሁለት ላማራጭ ነገሮችን እስጥሻለው ከሁለት አንዱ መምረጥ ያስፈልግሻል። በመጀመሪያ እኔ ጋር ለመኖር ከፈለግሽ እነዚህ ጌጣጌጦችሽን ወደ ቤተልማል መልሻቸው ላለዚያ ለመመለስ ካልፈለግሽ ግን መለያየት ላለብን” አሏት:: ይህ ጉዳይ በተለይም ለሴቶች በጣም ላስቸጋሪ የሆነ ውሳኔ እንድትወስን የሚያስገድድ ነው:: ፋጡማ ቢንት አብዱልመሊክ ግን ላስገራሚ በሆነ መልሷ ለምትወደው ባሏ እንዲህ ስትል መለሰች “ በእውነት እኔ ከላንተ የሚበልጥብኝ ምንም ነገር የለም ከዚህ የበለጠም ነገር ቢሆን ለአንተ የተመቸህን ነገር ብትጠይቀኝም አንተን ለመለየት አልፈልግም “ ካለች በኋላ አቧቷ ገዝተውላት የነበረ ጌጣጌጧን ሁሉ ወደ በይተልማል (ግምጃ ቤት) መለሰች። ይህች ወደር የሌላት ወይዘሮ ከባሏ ጎን በመሰለፍ ለጠቅላላ ሙስሊሞች ጥቅም እንዲሁም ባሏ ሀላፊነቱን ለመወጣት ለሚከፍለው መስዕዋትነት ሁሉ አጋር ሆነች::

በሁሉም የህይወት መስክ የአምስተኛው ኸሊፋ ዑመር ኢብኑ አብዱልአዚዝ አጋራቸው የነበረችው ፈጢማ ዑመር በሞት አፋፍ ላይ ሳሉ ወንድሟ ሊጠይቃት መጥቶ ነበር:: በወቅቱ ዑመር ኢብኑ አብዱልአዚዝ የለበሱት በርካታ ቦታ የተጣጣፈ ልብስ በመሆኑ የፋጢማ ወንድም ልብሳቸውን አንድትቀይርላቸው ጠየቁዋት ::ፋጢማም የምዕመናን መሪ የሆኑት ዑመር ኢብኑ አብዱልአዚዝ ያላቸው ልብስ የለበሱት ብቻ መሆኑን ነገረቻቸው:: ወንድሟ እጅግ በሀዘን ውስጡ ተነካ:: ያቺ በምቾት ውስጥ ያደገች የንጉስ ልጅ ህይወት በድህነት መጨረሻ ላይ ሆኖ መመልከቱ አሳዝኖት አነባ :: ፋጢማ ቢንት አብዱል መሊክ ባለቤቷ ዑመር በሞቱ ጊዜ ከፍተኛ ሀዘን ላይ ወድቃለ ። ወርቃማውን የኢስላምን ታሪክ አብረው የፈጠሩት

እንደ የፀደይ ሰማይ ከተንጣለለው ሰማያዊ ከሆነው የኢስላም ታሪክ ውስጥ ሴት ልጅ የነበራት ፋና ጉልህ ነው::

እነዚህ ጥንዶች ከስኬታማ ወንድ ጎን ጠንካራ ሴት አለች ለሚለው እሳቤ ጥሩ ማሳያ ናቸው:: ይህች ልዕልት ባሏ ከሞቱ በኋላ የዚድ የሚባለው ወንድሟ ከሊፋ ሆነ። በዚህ ጊዜ ወደ ቤተል ማል የመለሰችውን ጌጣጌጧን ወንድሟ መልሶ በሰጣት ጊዜ የሰጠቸው መልስ እንዲህ በሚል ነበር “ ባሌን በህይወቱ እንደነበር ታዝዠው እሱ ከሞተ በኋላ ላላምፀውም “ በማለት የመለሰችውን ጌጣጌጥ ላልቀበልም አለች። ወንድሟም ጌጣጌጧን ሁሉ ላይኗ እያየ ለቤተሰቦቹና ለሚስቶቹ ሲያከፋፍል ምንም ነገር አልጸጸታትም ነበር። በታሪክ ምዕራፍ ላይ ከተጻዝንበት ትላንት ወደ ዛሬ ስንመለስም የዚህች አይነት በርካታ ሴቶችን በአይናችን እየተመለከትን ነው:: ከስኬታማ ወንድ ጎን ጠንካራ ሴት አለች የሚለውን እሳቤ በተግባር ያረጋገጡ ፣የሰኬቱ ሁነኛ ተካፋይና ባለ ድርሻ የሆኑ ሴቶች:: ተወዳጁ ዑስታዝ ያሲን ኑሩ በቅርቡ ባሳተመው የህይወት ግብህን ቅረፅ በተሰኘው መፅሀፉ ውስጥ ምስጋና በሚለው ምዕራፍ ጥግ ይህችን አስፍሯል፡-

በመጨረሻም ሶስቱ ልጆቻችንን በብቸኝነት የማሳደግን ሀላፊነት ላለፉት ሶስት አመት ከመንፈቅ ለብቻሽ ለተወጣሽው ፣እኔ ጋ በመመላለስ ለተንገላታሽው ፣ይህን መፅሀፍ በመተየብ እንቅልፍ ላጣሽው ለዚህ መፅሀፍ ብቻ ሳይሆን ፣ለሙሉ ህይወቴ ስኬት ሁሌም ከጎኔ ለሆንሽው ውዷ ባለቤቴ ለአንቺ ያለኝ ፍቅርና ክብር የተለየ ነው፡ :// የህይወት ግብህን ቅረፅ /ገፅ 26 /// የታሪክ ምሁሩ አህመዲን ጀበል የኢትዬጲያ ሙስሊሞች የበደልና የጭቆና ታሪክ በሚል ያሳተመው መፅሀፍ በሀገር ፍቅር ቲያትር አዳራሽ በሚመረቅበት ወቅትም በስራው ከጎኑ የነበረቸው ባለቤቱ ለስኬቱ ትልቅ ድርሻ እንዳላት መድረክ ላይ ተናግሮ ነበር:: የጋዜጠኛ ዩሱፍ ጌታቸው ባለቤት እርሱ ቢታሰርም አንኳ እሷ የጋዜጠኝነቱን ሙያ ገፍታበት የባለቤቷንም የርሷንም ሚና ደርባ መሸፈን የቻለች ስኬታማ እንስት ናት:: መቼ በውል እንደሚፈቱ ያልታወቁትንና በሀገሪቷ ከፍተኛውን ቅጣት በሚያስቀጣው የሽብር ድርጊት የተከሰሱትን ሙባረክ አደምንና ካሊድ ኢብራሂምን ያገቡ እንስቶችን የሚገለፃቸው ቃላት ፣ ሊያወድሳቸው ብቁ የሆነ ቅኔ ፣ሊዘክራቸው አቅም ያለው የታሪክ አንቀፅ ይኖር ይሆን //// በኢስላማዊ አስተሳሰብ የተቀረፁና ሚናቸውን በሚገባ የተረዱ ሴቶች ሁሌም ከስኬታማ ወንድ ጀርባ ሳይሆን ከስኬታ ወንድ ጎን ሁነው የስኬቱ ተካፋይ ባለድርሻ ናቸው:: ይህን ስል በራሳቸው ያስመዘገቡት ሰኬት የለም ማለት ግን አይደለም፡ ፡ በመግቢዬ ላይ እንዳወሳሁት የነብዩ (ሰ..ዐ.ወ.) ውድ ባለቤት የሆነችው እናታችን አሚሻ የስኬት ጣራ የተቆናጠጠ አሻራ አኑራለች::



ሀጅ ፤አለም አቀፍ ጉባዔ



እንደ ዜጋም ይሁን በሐይማኖታችን ምክ ንያት ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ጋር ቀጥተኛ ወይም የሩቅ ተዛምዶ ያለው በአራቱም የዓለም ማዕዘናት የተከሰተ ዓብይ ክንውን የሚዳሰስበት የዓለማቀፍ ጉዳዮች ዓምድ ነው።

(በ "ሙሐመድ አቡበከር ")

ውድ ልጃቸውን መጀመሪያ በባዶ በርሀ ጥለውት እንዲመጡ የታዘዙት ነብዩላህ ኢብራሂም (ዐ.ሰ.) አሁን ደግሞ ሌላ ከባድ ትዕዛዝ ታዘዙ::በእርጅና እድሜ ያገኙትን ልጃቸውን እረዱት ተባሉ ::ልጅህን በራስ እጅ ማረድ ምን ያህል ከባድ ነው //ኢብራሂም ግን ለምን ብለው ሳይጠይቁ በአላህ በመመካት ትዕዛዙን ለመፈፀም ተዘጋጁ ::አባት ልጅን ስለጉዳዩ በመንገር ምን እንደሚታይህ አስተውል አለው ::ልጅ እሰማዔልም የታዝዝከውን ፈፅም ከታጋሾች ታገኘኛለህ ሲል በመመለስ የኢብራሂም ቤተሰብን የታዛዥነት ዳርቻ አመላከተ ::ለአላህ መታዘዛችን ዘወትር የእግር እሳት የሚሆንበት ሰይጣን እስማኤልን ትእዛዙን አሻፈረኝ እንዲል ለመጎትጎት ሞክሮ ነበር ::እስማዔል ግን ቦታ አልሰጠውም ::ሰባት ጠጠር አንስቶ ወረወረበት :: በሀጅ ወቅት ጀመራት በተባለው ቦታ ሰባት ጠጠሮችን የምንወረውረው ይህንኑ ፈለግ በመከተል ነው :: ኢብራሂም ልጃቸውን ወደ ማረጃው ስፍራ ወሰዱት ::እስማዔል አባት ልጁን ለማረድ እንዳይሳሳ በጎን እንዲያጋድሙት ጠየቀ ::የሚታረደው እርሱ ሆኖ ሳለ አባቱን አፅናና ::አባት ትዕዛዙን ለመፈፀም ቢላ አነሱ ::የልጃቸው አንገት ላይ አሳረፉት :: ቢላዋው ግን አላርድ ብሎ አስቸገረ ::ሞከሩ አሁንም አልሆነም ::አሁንም ሳሉትና ሞከሩ ::አልተሳካም : :በዚህ ወቅት ለመስዕዋትነት የሚሆን ድልብ ሙክት መጣ ::ኢብራሂም በፈተናው እስከመጨረሻው በመፅናታቸው በታላቅ መስዕዋትነት ምትክ ተደረገላቸው ::ከመስዕዋትነት በኃላ የሚመጣ ብስራት እንዴት ደስ ይላል ::

ይህ ጥሪ ዘመን ተሻግሯል ::ዛሬም በሚሊየን የሚቆጠሩ ሰዎች ለዚህ ጥሪ ምላሽ ለመስጠት ለቢይክ አላሁመ ለቢይክ በማለት ወደ ተቀደሰው ስፍራ አቅንተዋል ::

ከዚህ በኃላ ሌላ ታላቅ ብስራት መጣ ::ኢብራሂምና ልጃቸው ካዕባን የማነፅ ክብር ተሰጣቸው :: ካዕባን መጀመሪያ ያነፁት ነብዩላህ አደም ናቸው ::

ህዝብ ላይ የደረሰው ውሀ መጥለቅለቅ ግን አጥፍቶታል :: መሰረቱ ብቻ ግን ነበር ::አላህ ለነብዩላህ ኢብራሂም መሰረቱን አመላከታቸው ::ያኔ ሲምንቱ አልነበረም :: ግንባታው የታነፀው በጭቃ ነው ::ኢብራሂምና ልጃቸው ለግንባታው ብርቱ ጥረት አድርገዋል ::ተስማሚ የሆኑ ድንጋዮችን እያፈላለጉ ደረደሩ ::በሚገርም ሁኔታም ለሰኗቸው ::በስተመጨረሻም አንዲት ክፍተት ቀረች እሷን ለመሙላት የሚያስችል ደንጋይ አጡ ::ከእስማዔል ጋር በመሆን ይህችን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል ድንጋይ ፍለጋ ወጡ :: ተስማሚ ያሉትን ደንጋይ ይዘው ሲመለሱ ቦታው በነጭ ድንጋይ ተሞልቶ አገኙት ::ጅብሪል ከጀነት ደንጋይ አምጥቶ ከድኖታል :: ግንቡ ወደ ላይ አድጎ በኢብራሂም ቁመት ልክ ሆነ ::ልጃቸውንም የምቆምበት ደንጋይ አምጣልኝ ሲሉ አዘዙት :: አመጣላቸው ከርሱ ላይ ሁነው ቁመቱ ሰባት ክንድ እሰኪሆን ድረስ አነፁት :: በሚያምር ሁኔታ አጠናቀቁት ::ለረጅም ጊዜ ቆመው ሲያንፁበት የነበረው ቦታ ላይ የእግራቸው ፋና አረፈ ::ያ ቦታመቃሙ ኢብራሂም ይባላል ::አላህ (ሱወ)ኢብራሂም ለእስልምና የለፉትን ያህል ዝንታለም እንዲታወሱ በመሻት ፋናው ተጠብቆ እንዲቆይ አደረገ:: ህንፃው ተገንብቶ እንዳለቀ አላህ ኢብራሂምን ከሰዎች መካከልም የሀጅን አዋጅ አሰማ ፣እግረኞች ከሩቅ መንገድም መንገዶች በሚመጡ ከሲታ ግመሎች ላይ ሁነው ይመጡሀል ሲል አዘዛቸው ::ጌታዮ ሆይ እንዴት አድርጌ /ያረፍኩት ምድረበዳ ላይ ነው ::የምጠራቸው ሰዎች የታሉ /ድምፄስ እሰከ የት ሊደርስ ይችላል // ኢብራሂምን ያሳሰቡ ጥያቄዎች ነበሩ::አላህም አንተ ተጣራ እኛ የማደረሱን ሀላፊነት እንወስዳለን

አላቸው ::ኢብራሂምም በትዕዛዙ መሰረት ጥሪውን ለማሳማት የአረፋ ተራራ ጫፍ ላይ ወጡ ::ሰዎች ሆይ !አላህ ሀጅን ግዴታ አድርጎባችኃልና ሀጅ አድርጉ ሲሉ በከፍተኛ ድምፅ አስተጋቡ ::ይህ ጥሪ ዘመን ተሻግሯል ::ዛሬም በሚሊየን የሚቆጠሩ ሰዎች ለዚህ ጥሪ ምላሽ ለመስጠት ለበይክ አላሁመ ለበይክ በማለት ወደ ተቀደሰው ስፍራ አቅንተዋል ::

ሀጅ የአለም ቋንቋ

ብዙዎች እንደመልካቸው ሁሉ ቋንቋቸው የሚለያዩትን የሰው ልጅ በሙሉ የሚያግባባ ቋንቋ ነው ብለው የሚያስቡትን መላምት ያስምጣሉ: : ሙዚቃና እግር ኳስ በብዙዎች ዘንድ አለምን ሊያግባቡና ሰዎች ተመሳሳይ ስሜት እንዲያስተናግዱ ማድረግ የሚችሉ ቋንቋዎች እንደሆኑ ይሞግታሉ: : ቋንቋ መግባባትን የሚፈጥርና መንገድ ነው:: ሙዚቃ በሁሉም የአለም ክፍል ቦታ ያለ ቢሆንም የሚፈጥረው ስሜት ግን አጅግ የተለያየ ነው:: አንዳንድ ጊዜም ተቃራኒ የሚሆንበት አጋጣሚ አለ:: ይህ ደግሞ ለመግባባት አቅፋት በመሆኑ የቋንቋን ሚና እንዳይኖረው ያደርገዋል::እዚሁ ሀገራችን የወላይታ ብሄር አባላት አንድ ሰው በሞት ሲነጠቁ ሀዘናቸውን የሚገለፁት ድምቅ ባለ ሙዚቃ እየጨፈሩ ነው:: ይሄ ለነርሱ የሀዘን ድባብ የሚፈጥርላቸው ባህላቸው ነው: : ይህንን ሙዚቃ ከሌላ አካባቢ የመጣ ሰው ቢሰማው ግን ከሀዘን ይለቅ የጭፈራ ስሜት ነው የሚፈጥርበት: : አንድ ሙዚቃ ሁለት ተቃራኒ ስሜት የሚፈጥር ከሆነ ፈፅሞ መግባቢያ ቋንቋ ሊሆን አይችልም:: ሌሎች አለምን ያግባባል በማለት የሚሞግቱለት እግር ኳስ ነው:: በርካታ ተመልካች ያለው ይሄው እስፖርታዊ ውድድር አሁንም ድርስ ከሁከት ፣ከዘረኝነት ፣ከመጠላለፍ የፀዳ አይደለም:: በተጨማሪ ውድድር መሆኑ በራሱ የሚፈጥረው ሁለት የተለያያ ስሜት እንጂ አንድ የሚያግባባ ስሜት አይደለም: : የደረጃ ልዩነት መገለጫ፣ በድሀና በሀብታም መካከል ያለውን ሰፊ መራራቅ ማሳያ ነፀብራቅ እንጂ ፈፅሞ መግባቢያ የሚሆንበት ማዕቀፍ የለውም:: ዘወትር በየአመቱ የሚከናወነው የሀጅ ሰነ-ስርዐት የአለም መግባቢያ ቋንቋ ለመባል የሚያስችለው ልዩ ማዕቀፍ አለው:: ሀጅ የእኩልነት መገለጫ ፣ተመሳሳይ ስሜት የሚንፀባረቅበት መድረክ ፣ የመተሳሰብ :የመተዛዘንና የመከባበር ድንቅ እሴቶች የሚልቁበት አፀድ ነው:: በሀጅ ላይ በሰዎች መካከል ለዘመናት ሊናዱ ያልቻሉ የልዩነት አጥሮች ይናዳሉ:: ጥቁርና ነጩ፣ሀብታምና ደሀው ፣ባለስልጣኑና ተርታው ህዝብ እኩል አንድ ቦታ ላይ አንድ አይነት ልብስ ለብሰው አንዲት ቃልን ደግጋመው እያሉ ተመሳሳይ ስሜት የሚያስተናግዱበት መድረክ ነው:: በሀጅ ላይ ሁሉም ተመሳሳይ ልብስ ነው የሚለብሰው: : ከ50 ሪያል በላይ የማያወጣ ነጭ ፎጣ:: የተለየ ጫማም ቢሆን የሚጫማ የለም:: 10 ሪያል የማታወጣ ነጠላ ጫማ ቢሆን እንጂ:: በሀጅ ለሀብታም ፣ለዝነኛ ፣ለባለስልጣን ተብሎ የተዘጋጀ የተለየ ቦታ የለም: : ሁሉም እኩል ነው:: ሁሉም ተመሳሳይ ቋንቋ ነው የሚናገረው:: ለበይክ አላሁመ ለበይክ እያለ ለጌታው ጥሪ እሺ ብሎ መምጣቱን ይመሰክራል:: በሚና እና በሙዝደሊፋ ማደር የሀጅ መሰረቶች ናቸው:: ታዲያ በነዚህ ሁሉም የሚያድረው ደንኳን ውስጥ ነው:: ክብር፣ስልጣን ፣ሀብት ቦታ የላቸውም:: ምድራችን ላይ ከሀጅ የተሻለ የእኩልነት ማሳያ ፈፅሞ የለም::

አለም አቀፍ ጉባኤ

በሀጅ ወቅት ከሁሉም የአለም ጥግ ከሚገኙ ሀገራት ምዕመና ለጌታቸው ጥሪ ምላሽ በመስጠት በአንድ ቦታ ይሰባሰባሉ:: ይህ የያንዳንዱን ሀገር ተወካይ የያዛ ታላቅ ጉባኤ ከመንፈሳዊ ፋይዳው ባሻገር በድንበር የማይገደብ የወንድማማችነት ፣የመከባበር እና የመተሳሰብ እሴቶች የሚጎለብቱበት ነው:: በቋንቋ ፣በባህል ፣በመልክ ፣በኢኮኖሚያዊ ደረጃ ፍፁም የተለያዩ ከሆኑ ሀገራት የተሰባሰቡ ተወካዬች ሰለአንድ ጉዳይ በተመሳሳይ ስሜትና በተመሳሳይ መፈክር ለበይክ አላሁመ ለበይክ በማለት ከሰው ሰራሽ አስተሳሰቦችና ከፍጡራን አምልኮ ነፃ ወጥተው የፍጡራን ሁሉ ፈጣሪ የሆነው አምላክ የሚያመልኩበት ፣ ከአምልኮዎቸው በሚወጣው መንፈሳዊ አየር ድባቡ ልዩ ስሜትንና የማይረሳ ትዝታን የሚፈጥርበት መልካም አጋጣሚ ነው:: በዚህ አለም አቀፍ ጉባኤ ፍቅር ይሰበካል ፣ሰጋና አጥንት ለብሶም በተግባር ይኖራል: : አለም ላይ እልቂትና ጦርነት ተወግዶ ሰላም እንዲሰፍን ፣ጥላቻ በፍቅር እንዲተካ የሰው ልጅ ችግሮች ሁሉ ተቀርፈው የሀሴት ድባብ ምድርን እንዲያካባት ሁሉም ጌታውን የሚማፀንበት ፣ተያያተውም ሆነ ተገናኝተው በመካና በመዲና አድርገው የብዙዎች ፀሎት ነው::ከቻሉ እዛው ደርሰው ከዚህ የመልካም መዐድ መቃደስን ካልሆነ በመንገድ ላይ መሞትን መርጠው በረሀውን በእግር አቋርጠው ፣ባህሩን በታንኳ አሳብረው ፣አየሩን በጠያራ ሰንጥቀው ወደዚህ ወደተቀደሰ ስፍራ ይገሰግሳሉ:: ሴናድ ሀዲዚች የተባለው ቦሲኒያዊ ወደዚህ የተቀደሰ ስፍራ ለመጓዝ 5700 ኪ.ሜትርና ሰባት ሀገራትን በእግሩ አቋርጧል:: በዚህ ጉዞው እሰከ ኔጌቲቭ 33 ዲግሪ ሴሊሺየስ የሚደርሰውን የቡልጋሪያ ቅዝቃዜ እንዲሁም ከ44 ዲግሪ ሴንትግሬድ በላይ የሆነውን የጆርዳንን ሙቀት ተጋፍጦ አልፏል:: አጠቃላይ ጉዞውም 314 ቀናት ፈጅቶበታል:: አንድ ፓኪስታናዊም ከዚህ የማይውቁት ግን ከሚናፍቅ ሀገር ለመድረስ 6378 ኪ.ሜትር በእግር ተጉዟል: : የሀገራችን ታላለቅ ሸሆችን ሀጅን ለማድረግ በተደጋጋሚ በእግር ይጓዙ ነበር:: አስፈሪውን ቀይ ባህርም በታንኳ አስብረው ፣የየመንን በርሀ አቋርጠው በተራሮች ከተከበበችው ቅዱስ ስፍራ ታድመው ወደ ሀገራቸው ይመለሱ ነበር:: ሰዎች ከሌላ ሀገር ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ እጅግ የደስታ ስሜት ነው የሚሰማቸው:: ለሀጅ የተጓዙ ግን መካና መዲናን በመመልቀቃቸው የሀዘን እንባ እያነቡ ዳግም ተመልሰው እንዲኖሩባት ግብዐተ መሬታቸውም ከአሸዋማ አፈሯ ስር እንዲሆን ጌታቸውን እየተመፃኑ በሀዘን ድባብ ተውጠው ነው ወደ ሀገራቸው የሚመለሱት::



የሚያውቁ የተለያያ አለም ሰዎች ተመሳሳይ ሰብዕና ተላብሰው ሳይነጋገሩ የሚግባቡበት መድረክ ነው::

የሚያውቁት ሀገር ይናፍቃል

የሚያውቁት ሀገር አይናፍቅም የሚል ብሂል አለ:: ይህ ብሂል ለሀጅ ግን አይሰራም:: ሀጅ የማያውቁት የሚናፍቁት ያወቁትን ሳይሰለቹ ደጋግመው የሚናፍቁት መንፈሳዊ ስርአት ነው:: በነዛ ልቅናን በተቸሩ ሁለት ከተሞች መኖር ብቻ ሳይሆን መሞትም ክብር ነው:: ሞቴን በሀገሬ ሳይሆን ሞቴን

በመደገፍ ፣ ገንዘብ ያነሰውን ስራ ፈጣሪ (ኢንተርፕሪነር) ገንዘብ በመሙላትና የተለያዩ ኢንቨስትመንት አማራጮች ላይ በቀጥታ በመሳተፍ ትርፋቸውን ያሳድጋሉ ፤ ምክንያቱም ከወለድ የሚገኝ የትርፍ ገቢ የላቸውም። የኪሳራ እድላቸውንም ለመቀነስ ሲሉ ወለድ አልባ ባንኮች የተወሰኑ ትልልቅ ኢንቨስትመንቶች ላይ ታብታቸውን ከማፍሰስ መካከለኛና አነስተኛ የሆኑ ብዙ ኢንቨስተመንቶች ላይ መሰማራትን ይመርጣሉ። ይህ አካሄድ በአንድ በኩል የቢዝነስ ሃሳብ እንጂ ገንዘብ የሌላቸውን እና ገንዘብ ያጠራቸውን ግለሰቦች በማገዝ አዳዲስ ኢንቨስተሮችን ማምረቱ ላይ ሲሰማሩ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በታችኛው የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኘው ህብረተሰብ ሰፊ የስራና የመለወጥ እድል በማመቻቸት ለሃገር እድገት የጎላ አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ያደርጋቸዋል። ቀደም ብለን ስለቬኑስ ስናወጋ እንዳነሳነው ኮሜንዳ አዳዲስ ባለሀብትን በማፍራቱና ቬኒስን በማሳደጉ ላይ የጎላ ሚና እንደነበረው ሁሉ የኮሜንዳ ዓይነት ውሎችን በስፋት የሚይዘው ዘምዘምን የመሰሉ የወለድ አልባ ባንኮችም ላገራችን እና ህዝባችን ተመሳሳይ ሚና መጫወት በቻሉ ነበር።

ተመሳሳይ እጣ ፈንታ

ኮሜንዳ የቬኑስን ልሂቃንና ባለታብቶች የሚገዳደር አዲስ የህብረተሰብ ክፍል ማፍራቱን መሪዎቿ አልወደዱትም። የኢትዮጵያ ሙስሊም ምንም እንኳን በአብዛኛው በንግዱ ላይ የተሰማራ ቢሆንም የባንኪንግ ሴክተሩ ከማደጉ ጋር ተያይዞ ለሌሎች የሚመቻቸውን እድል ተጠቃሚ መሆን ባለመቻሉ እድገቱ ከጊዜ ወደጊዜ እየቀጨጨ ይገኛል። ስራቸውን ወለድ ላይ ያንጠለጠሉት የሀገራችን ባንኮች ፣ ሙስሊሙ ህብረተሰብ ወይ ከሐይማኖታዊ ቀኖናው ጋር እንዲጋጭ ፤ ካለዚያም የኢኮኖሚ ድቀትን እንዲመርጥ በሁለት አስከፊ አማራጮች መካከል አጣብቂኝ ውስጥ አስገብተውታል። ዘምዘምን የመሰሉ ባንኮች ሊባክኑ ለነበሩ አዕምሮዎች እድል በመፍጠርና ሰርቶ ለማደግ የወለድ አሰራሩ እክል ለሆነባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የተመቻቸ አማራጭን በመፍጠር በግለሰብም ይሁን በሀገር ደረጃ ሰፊ ለውጥን ማምጣት ያስችል ነበር። ዘምዘም ፣ ኮሜንዳ ቬኒስ ላይ እንዳደረገው ህብረተሰባችን ውስጥ በጉልህ የሚታይ የሀብት ስብጥር ለውጥን የማምጣት አቅም ነበረው። ሙስሊሙን በዓይነ ቁራኛ ለሚመለከተው አገዛዝም ሆነ የሀገሪቱ ልሂቃን ግን እንደዚህ ዓይነት ነባሩን ያጋደለ ሚዛን ሊያዛባ የሚችል ዕድል መፈጠሩን ስጋት አድርገው ይቆጥሩታል። ሙስሊሙ የሀገሪቱ አንድ አካል መሆኑን በመዘንጋት የሚገባውን በሃብቱ የመጠቀምና የመጥቀም መብቱን ያለ ማንም ጠየቂ ነፍገውታል። ሀገሪቱንም ሆነ በተለይ ሙስሊሙን በኢኮኖሚ እድገት ጎዳና ሊያራምደው የሚችለው የነበረውን ዘምዘምና መሰሎችን በመከልከል በ14ኛው ክፍለ ዘመን የቬኑስ ጥቂት ልሂቃን የፈፀሙትን ሀገራዊ ሸፍጥ አይናቸውን ሳያሹ በ21ኛው ክፍለ ዘመን በኛ ላይ ፈፅመውታል። ሀገር የጋራ መሆኗ ቀርቶ ግማሽ ዜጋዋን የዘነጋች የጥቂቶች መፈንጫ መሆን የቬኒስና የኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ ሆኗል። እውን ግን ዘምዘም እንደ ኮሜንዳ ሁሉ ታግቶ ይቀር ይሆን? ሙስሊሙስ ቬኒስ ለጎብኝዎች መዳረሻ እንደሆነችው ጽልመት የወረሰው ታሪክ አድርጎ በመዘከር ይጠመድ ወይስ ዳግም ጥሮና ታግሎ ታሪክን ይቀይራል?።



ማንነቱ የተነጣጠለ ስር የለሽ ሙስሊም ይሆናል። ያ ደግሞ አባቶቻችን ካጡት ሐገራዊ ማንነት (የባህል ውክልና ፣ የማህበረ ፖለቲካ ተሳትፎ እና ምጣኔ ኃብታዊ ባለድርሻነት) የበለጠ ክስረት ይሆናል። በተለይ ሙስሊሙ ወጣት አሁን ያለውን የዜግነት ግንዛቤ አጠንክሮ እንደ ሙስሊም ደግሞ በራስ ማንነቱ ኮርቶ በክብር መኖር ካለበት ሁለቱን ሊያመጣጥን ይጠበቃል። በዚህ ዘመን ስፍር ቁጥር የሌላቸው የእውቀት አማራጮች ይገኛሉ። በተዓማኒ ጸሃፍት የተዘጋጁ እና የተተረጎሙ መጻህፍትን በተለያየ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ፣ እምነት ማጎልበት እና መንፈሳዊነትን መላበስ ይቻላል። በሌላ መልኩ ደግሞ በድምጽ እና ድምጽ ከምስል የተዘጋጁ የቂርዓት እና የዳዕዋ ስራዎች ባገርኛም ሆነ በውጭ ቋንቋ ተትረፍርፈዋል። መጽሃፍ እና ኪታብን ተሸክሞ ሳይዞሩ በሞባይል እና ኮምፒውተር ላይ በርካታ የእውቀት ምንጮችን አጭቆ በየትኛውም ሰዓት እውቀት የሚሸመትበት ጊዜ ላይ መሆናችን ደግሞ ምንም ማስተባበያ ምክንያት ያሳጣናል። ከቤታችን ተቀምጠን በቴሌቪዥን እና በሲዲ የምናያቸው ወይም በካሴት የምናዳምጣቸው በርካታ የዕውቀት ባለኃብቶች አሉን።ከዚህ አንጻር የጉዳዩን አሳሳቢነት ተረድቶ ለለውጥ መነሳሳት እና በቁርጠኝነት መትጋትን የመሰለ መፍትሄ አይኖርም።

የተመጣጠነ የትምህርት

ስርዓት ወይም ዕውቀት ቃረማ

ሙስሊም ሁለገብ ሊሆን ይገባል ፤ ለማህበረሰቡ ፋይዳ ያለው። እንደ ግለሰብ ደግሞ ቅን የአላ ባሪያ መሆን ያስፈልገዋል። አላህን አውቀን ፣ ነብዩ በህይወት በኖሩበት ልኬት ልንኖር የሚቻለን ደግሞ የአላህን እና የነብዩን ትዕዛዛት እና ክልከላ የያዙ እስላማዊ መመሪያዎችን ስንማር ነው። እስልምናን አውቆ መተግበር እና ያለ ዕውቀት አላህን ማምለክ ለየቅል ናቸው። የሰው ልጅ ተፈጥሮው አካላዊ እና መንፈሳዊ ቀለብን ይሻል። ምድራዊ ዕውቀት በራሱ ካለው ቁም ነገር ባለፈ ለአካል መገንቢያ የሚሆን የኑሮ ጣጣን ማጣኛ መንገድ ነው። ይህ ደግሞ ባጭር የዕድሜ ገደብ የተወሰነ ነው። መንፈሳዊው የዲን እውቀት የዝንተ ዓለም አስፈልጎታችን ነው። አውቆ ያሳወቀን የመሰለ ተመራጭ ሙስሊም ከየት ይገኛል። አላህን ፣ መልዕክተኛውን እና ኃይማኖቱን ጠንቅቆ የሚያውቅ የተማረ ትውልድ የመፍጠር ግዳጅ ሁላችንም ጋር ይገኛል። ተምረናል የምንል ወጣቶችም ራሳችን ከዲን ሐለቃ መራቅ አስኒ ችግራችን ሆኖ ይስተዋላል። የቂርዓት እና የዲን ኪታቦች ንባብ ከበብ መስርቶ በእስልምና ጉዳይ ከዓዋቂዎች ጋር ሁሌም መተዋወስ ያስፈልገናል። አብዛኞቻችን ለበርካታ ዓመታት ትምህርት ቤት መመላለሳችን እና ከትምህርት ጋር እጅና ጓንት መሆናችን ከዕለት ጉርስ ማግኘነት ለዘለለ ዓላማ አይደለም። ያውም ተሳክቶልን ትምህርታችን ካጠናቀቅን እና አላህ ብሎት የስራ ዕድል ጋር ከተገጣጠምን። ያም ሆኖ ለብዙኃኑ ትምህርት የተፈለገው የዕውቀት ደረጃ ላይ ሳያደርስ ፣ የታሰበው እንጀራ ሳይበላበት ፣ የታለመው ክብር እና ማህበራዊ ደረጃ ላይ ሳያዘልቅ በእንጭጩ ይቀራል። እናም ለዱንያ የምንሰጠውን ትኩረት ለዘላለማዊው ይዎትም አንንፈግ። በተቻለን መጠን እንደ ትርፍ ስራ ሳይሆን በቁም ነገር ራሳችንን ከአላህ ጋር እናስተሳስር። ልጆቻችን ሳሊህ ሆነው ያድጉ ዘንድ ከፊደል ያለፈ የዲን ዕውቀት ለማስጨበጥ እንትጋ። ካልሆነ ነገ ወላጆቻቸውን ዘወር ብለው የማያዩ ራስ ወዳድ ዜጎች ሆነው ይገኛሉ። ያለንን ኃብት አፍስሰን ያስተማርናቸው ዓለማዊ ትምህርት ብቻውን የተሟላ ስብዕና አያላብሳቸውም። ከማህበራዊ ተጠያቂነት ይልቅ እኔነት የገዛቸው የዱኒያ ባሮች ሆነው ለራሳቸውም ለወላጆች እና ማህበረሰብም ሳይሆኑ ይቀራሉ። ካሁኑ የሚያስፈልጋቸውን የመንፈስ ስንቅ እና የቀልብ ቀለብ

ቢዲን ላይ በቂ እውቀት ለማግኘት የግድ ዩኒቨርስቲ እና ኮሌጅ መግባት አያስፈልግም ፤ ከታማኝ የእውቀት ምንጮች የሚገኙ ያቅራቢያ ሐይማኖታዊ ማዕከላትን በቀላሉ መጎብኘት በቂ ሊሆን ይችላል። ቀደም ሲል የተጠቀሱ የመማሪያ አማራጮችን እንዳመችነታቸው ጥቅም ላይ ማዋልም ተገቢ ይሆናል።

እናስይዛቸው።

ያኔ መንገድ ላይ አይቀሩም ፤ ያለሙበት ደርሰው እኛን ተመልሰው ያስባሉ። የዛሬው መንፈሳዊ ስንቅ ያኔ ከልቦና እየወጣ ውለታ ያስከፍላቸዋል። ለወላጆች ጧሪ እና ተንከባካቢ መልካም ልጅ ያስገኛል ፤ ለልጅ ደግሞ የጀነት መግቢያ የሆነ የወላጅ ዱዓ። ወቅቱ አስፈልጎት - የዓለማዊ እና ኃይማኖታዊ ዕውቀት ጥምረት ተጨባጩን ዓለም መገንዘብ የሚችል ሙስሊም መሆን ካስፈለገ ነገሮችን የምናይበት አግባብ እስላማዊ ሊሆን ያስፈልጋል። ከወቅታዊ የዓለም ኹነት የተፋታ ሙስሊም ጉድለት እንዳላበት ሁሉ በሙያዊ እና ትምህርታዊ ዕውቀት ብቻ የመጠቀውም ጎደሎነቱ አያጠያይቅም። ሁለቱን ያስተሳሰረ ንቁ ወጣት ያስፈልገናል። ሁለቱንም ጎን በሚዛናዊነት ያመጣጠነ። ከዘመኑ ጋር እኩል መራመድ የሚችል ትውልድ እንሁን። ከሌላው ወገን የሚመጣውን አስተሳሰብ ሁሉ በገፍ ያለመቀበል እና የማነጻጸር ዓቅም የሚኖረን ለማንጠሪያነት የሚውል የዲን ግንዛቤ ሲኖረን ነው። ዘመናዊው እውቀት ሲያንስ ደግሞ የሚጠቅመንን አሰራር ፣ ቴክኖሎጅ እና ዕውቀት ሁሉ በጭፍን የመገፍተር አስማሚያ ይኖራል። ስለዚህ እውነተኛ የሙስሊም ስብዕና መላበስ የሚችል ሙስሊም ኢትዮጵያዊ እስልምናውን የተረዳ ፣ ኃገራዊ አጀንዳ ላይም በንቃት የሚሳተፍ መሆን አለበት። ያ ሲሆን ከዱኒያም ከአኺራም ባግባቡ የሚጠቀም ለሌላውም የሚፈይድ አልሚ ዜጋ መሆን ይቻላል። ካልሆነስ? ካልሆነማ ሚዛን መሳት ይመጣና ማህበራዊ ብቁነት ይታጣል። በዲን ላይ በቂ እውቀት ለማግኘት የግድ ዩኒቨርስቲ እና ኮሌጅ መግባት አያስፈልግም ፤ ከታማኝ የእውቀት ምንጮች የሚገኙ ያቅራቢያ ሐይማኖታዊ ማዕከላትን በቀላሉ መጎብኘት በቂ ሊሆን ይችላል። ቀደም ሲል የተጠቀሱ የመማሪያ አማራጮችን እንዳመችነታቸው ጥቅም ላይ ማዋልም ተገቢ ይሆናል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በተወሰኑት የርቀት ትምህርት ማዕከላት እና አንላይን (በኢንተርኔት የቀጥታ) ትምህርቶችን ተመዝግቦ መከታተል ጥሩ አማራጭ ናቸው። ዋናው ቁም ነገር ቀስ በቀስ ራስን ከእውቀት ጋር ማስተሳሰር ነው። ከጀመሩ በኋላም ተሰላችቶ ላለመተው በሚዛናዊ ልኬት ጀምሮ ቀጣይነት እንዲኖረን መሞከር የተሻለ ነው። እውቀትን በመፈለግ ሂደት አብሮን የሚጓዝ የዲን ጓድ ሲኖረን ደግሞ የበለጠ እንበረታለን። ስንዘነጋ ለመተዋወስ ፣ ያልገባንን እየተጠያየቅን እርስ በርስ ለመማማር ይረዳናል። የተጣበበ የህይዎት እንቅስቃሴ ካለን እንኳ ለዚሁ ዓላማ ጊዜ ማስተረፍ ለነገ የማይባል ቀዳሚ ተግባር ነው። በጉዞ ላይ እና የእረፍት ሰዓትን አጣብቦ ለዚሁ ተግባር ማዋል ደግሞ ያለንን ራስን የመለወጥ ጥረት የበለጠ የሚያስመሰግን ያደርገዋል። አላህም ዘንድ የበለጠ ምንዳ ያስገኝልናል - ኢን ሻ አላህ። በተለይ በተለይ ቁርዓንን አንብቦ ትርጉሙን እና መልዕክቱን ለመረዳት እንሞክር። የሐዲስ ኪታቦች የያዟቸውን ዕምቅ ነብያዊ ውርስ እንቃርም። ከኪታብ ይዘትነት አውጥተን በህይወታችን ላይ እንተግብራቸው። ምርጥ ተምሳሌት አለላችሁ የተባልነውን ሁለገብ የነብዩ ሞዴል እንከተለው። በሂደት ምርጥ ሰው እንሆናለን ፤ ጥሩ ባል/ሚስት እና ወላጅ እንሆናለን። ለወላጆቻችን መልካም ዝርያ ሆነን እንገኛለን። በህይወት ሳሉ ያይን ማረፊያ ከሞቱ እንኳ የማያልቅ ሰደቃ (ሰደቀተል ጃሪያ) የሆነውን የሳሊህ ልጅ ዱዓ አይነፈጉም። ከጓደኞቻችን ፣ ዘመድ አዝማዶቻችን እና ጎረቤቶቻችን አልፎ ለሌላው የሩቅ ሰው ሁሉ መልካምነታችን ይተርፋል። ስብዓዊነታችን ሰፍቶ ሌሎች ፍጡራንን ያቅፋል። ለዚህ ደግሞ ከቁርዓን እና ሐዲስ የተመዘዙ የፊቅህ እና የተርቢያ (ስብዕና ኩትኮታ) አስተምህሮዎችን በራስ ላይ መተግበር ወሳኝነት አለው። መልካም ማህበራዊ መስተጋብር እና በህይዎት ግልጽነትና ተጠያቂነትን የሚሰብኩ እስላማዊ ዕሴቶችን መውረስ የምንችለው ተምሳሌታዊውን የነብያት እና ባልደረቦቻቸው ታሪክ ስንዘክር ፣ የአላህን ድንበር እና ክልከላ አውቀን ስንተገብር ነው። ባጠቃላይ እስልምና በህይወታችን ላይ ተንጸባርቆ የህይዎት ቀመርነቱ ሲረጋገጥ የመጠቀ ስብዕና ባለቤት የሆኑ ግለሰቦች የላቀ ማህበራዊ ስርዓት ይሰፍናል። ለዚህ ደግሞ ሁላችንም ለውጥን ከራሳችን እንጀምር። ለለውጥ ጅማሮ ወሳኙ ነገር ታዲያ እንዴት እና ወደምን በምን አማካኝነት እንደምንቀየር ማወቅ ነው። ስለዚህም ዓላማችን የተዋጣለት ሁለገብ ስብዕና ያለው ሙስሊም ሆነን ማየት ከሆነ ራሳችን በአካዳሚክ እና በዲን ዕውቀት እንገንባ።

ቬኒስ እና ዘመናዊው ባንክ



ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ኢኮኖሚ ነክ ጉዳዬችን የምንዳስስበት አምድ ነው

ፀሀፊ ፡ስለሞን

በመካከለኛው ዘመን የጣሊያኗ ቬኒስ ከተማ በዓለም ላይ በጣም ኃብታም ከሚባሉ ቦታዎች መካከል በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሽ ነበረች። ይቺ ከተማ በ810 እኤአ ነፃነቷን አግኝታለች። ያ ዘመን የሮማን ኢምፓየር ከፈራረሰ በኋላ የአውሮፓ ኢኮኖሚ እንደ አዲስ ማንሰራራት የጀመረበት ጊዜ ነበር። በወቅቱ የተፈጠረው የተሻለ መረጋጋት ፣ ሰላምና የንግድ መስፋፋት ቬኒስን በእጅጉ ጠቅሟታል። ከተማዋ የነበረችበት ቦታ ስትራቴጂካዊ ስለነበረና ብዙ የባህር በሮችም ስለነበሯት ከምስራቅ የሚመጡት ቅመማ ቅመሞች ፣ ከቤዛንታይን የሚመጡት የፋብሪካ ምርቶችና የባሪያ ንግዱ ከተማዋ ከፍተኛ የንግድ መናኸሪያ እንድትሆን አድርጓት ነበር። በ1330 እኤአ ከተማዋ ከፈረንሳይዋ ፓሪስ እኩል የሆነ ህዝብ ሲኖራት ታላቂቷን የለንደን ከተማን በሶስት እጥፍ በልጣታለች።

ኮሜንዳ (Commenda)

ለቬኒስ አስገራሚ ብልፅግና እንደ ሁነኛ ምንጭ ተደርጎ የሚቆጠረው በወቅቱ መፍጠር ችላ የነበረቻቸው የተለያዩ የንግድ ውል ዓይነቶች እና ውሎችን ማስፈፀም የሚችሉ ተቋማት መመስረት መቻሏ ነበር። ከነዚህም የውል ዓይነቶች ለዚህ እድገቷ በጉልህ የሚጠቀሰው ኮሜንዳ (commenda) ተብሎ የሚጠራው ነው። ኮ ሜ ን ዳ ለ አ ን ድ ዙ ር ንግድ የሚደረግ ስ ም ም ነ ት ነው። በስምምነቱ ሁለት አካላት ሲሳተፉ ፤ አንደኛው ተቀማጭነቱን ቬኒስ ላይ ሲያደርግ ፣ ሁለተኛው ደግሞ ከንግድ ቅፍለቱ ጋር ይንቀሳቀሳል። ተቀማጩ ንግዱን በገንዘቡ ሲደግፍ ፣ ሌላኛው ግለሰብ ወደሌላ ቦታዎች በመጓዝ ይገበያያል። በንግዱ ላይ ባዋሉት የገንዘብ መጠን ሁለቱ አካላት ኪሳራውንም ሆነ ትርፉን ይከፋፈላሉ። በአንድ ንግድ ጉዞ ወቅት መቶ ፐርሰንቱን ካፒታል ያዋጣው ተቀማጩ ባለሀብት ከሆነ የትርፉን 75% የሚወስድ ሲሆን የንግዱን 67% ወጪ ሲሸፍን ደግሞ ለንግድ ከወጣው ግለሰብ ጋር ትርፉን እኩል ይከፋፈላሉ። የካፒታሉን ሲሶ ሸፍኖ ሲያበቃ በሲራራ ንግዱ ወቅት በጉልበት ፣ ጊዜ እና እውቀት ተሳትፎ ያደረገው የካፒታሉን ሁለት ሶስተኛ ካወጣው ጋር እኩል ትርፍ ይጋራል ማለት ነው። ይህ የንግድ ውል በህብረተሰቡ ው ስ ጥ የ መ ነ ገ ድ ፍላጎት እና አቅሙ እያላቸው ፤ ነገር ግን ገንዘብ የሌላቸውን ወይም በቂ መነገጃ ላላከበቱ የህብረተሰብ አካላት ጥሩ የሃብት ምንጭ ሆኖ ማገልገል ጀመረ። በኃብታቸው ከሚያስነግዱት ባለጸጎች ጋር ተሻርከው

> ከሸኑበትም በፊት በሒሪቢያ ተግባር ላይ ሲውል የነበረ ነው። ከነቢያችን (ሰ.ዓ.ወ) ነብይ ሆኖ ከመላክ በፊትም የነቢያችን ደጋግሞ የራሳቸው እንደነበረ ይመሰክርልናል። የመጀመሪያ ታሪክ በለቢታቸው ከነበረችው ሸዲጃ (ረ.ዓ) ጋር ተመሳሳይ የንግድ ውል ገብተው እንደነበር ይታወሳል።

የሚነግዱ ብዙኃን ተለወጡ ፤ የስኬት ማማን ተቆናጠጡ። በየጊዜው ከምንም ተነስተው ትልቅ የሃብት ደረጃ የሚደርሱ ወጣቶች መበራከት ጀመሩ። በ960 እኤአ በመንግስት መዝገብ ውስጥ የነበሩት የቬኑስ የኢኮኖሚ ልሂቃን (ሃብታሞች) ቁጥር በ69% አዳዲስ ስሞችን ሲጨምር ፤ በሚቀጥሉት ሀያ አመታት ውስጥ ወደዚኛው የህብረተሰብ ክፍል የተቀላቀሉ የአዲስ ሃብታሞች ብዛት ከሁለት እጥፍ በላይ ማደግ ቻለ። ሀብትና የፖለቲካ ስልጣን ካላቸው ጥብቅ ግኑኝነት በመነሳትም በጥቂቶች እጅ ወደነበረው ፖለቲካና ስልጣን አዳዲስ ስሞችና ቡድኖች መጠጋትና ጫና መፍጠር መቻልም ጀመሩ። እንደዚህ አይነት የንግድ ውል ከቬኑስም በፊት በአረቢያ ተግባር ላይ ሲውል የነበረ ነው። ከነብያችን (ሰ.ዓ.ወ) ነብይ ሆኖ ከመላክ በፊትም ይተገበር እንደነበረ የነብያችን የራሳቸው ታሪክ ይመሰክርልናል። የመጀመሪያ ባለቤታቸው ከነበረችው ኸዲጃ (ረ.ዓ) ጋር ተመሳሳይ የንግድ ውል ገብተው እንደነበር ይታወሳል። በአንድ ወቅትም ለኸድጃ ከፍተኛ ትርፍን ያስገኘ ቅፍለት መርተው እንደነበርና ባሳዩት ታማኝነትና የተሳካ የንግድ ጉዞ የኸዲጃን ቀልብ መማረካቸውን ታሪካቸው ያወጋናል።

የቬኑስ መክሰም

በሰሜናዊቷ የኢጣሊያ ከተማ የነበረው ምቹ የንግድ ስርዓት አዳዲስ ባለሃብቶችን መፍጠሩን ቀጥሏል። ከዚህ ቀደም አንድን እቃ አንድ ግለሰብ ያመጣው ከነበረ የኋላ ኋላ የተለያዩ ሰዎች በብዛት ወደቬኑስ ማጋዝ ጀመሩ። አንድን የንግድ መስመር ለብቻ ተቆጣጥረው በነበሩ ጥቂት ነጋዴዎች ላይ ብዙ አዳዲስ ነጋዴዎች ኮሜንዳ የፈጠረላቸውን እድል በመጠቀም ተመሳሳይ የንግድ መስመርን መገልገል ጀመሩ። ይህም በወቅቱ ለብቻቸው ሀብት ያካብቱ ለነበሩ የቬኑስ ሀብታም ነጋዴዎች የራስ ምታት ሆነ። የሚያገኙት ትርፍ ከግዜ ወደግዜ ማሽቆልቆሉን ማስቆም አቃታቸው። ከዚህም ሲከፋ ከነሱ የተሻለ ዕቃዎችን ማምጣት በቻሉ አዳዲስ ነጋዴዎች ከስራ ውጭም መሆን ተበራከተ። ይህ የቬኑስን ሀብት ለረጅም ግዜ ተቆጣጥረው ለነበሩና ፖለቲካውንም በፊት አውራሪነት ሲሾፍሩ ለነበሩ ባለሀብቶችና ልሂቃን የሚዋጥላቸው ነገር አልሆነም። ይባስ ብሎ እየፈረጠመ የመጣው የአዳዲስ ባለሃብቶች ክፍል ፖለቲካውንም መገዳደር ጀመረ። ይህ ቀድሞም ያላማራቸው የነበሩት የቬኑስ ልሂቃን በቅድሚያ ፖለቲካዊ ስልጣናቸውን ፤ በመቀጠል ደግሞ ኢኮኖሚውን ለአዲስ መጪዎች የማይቀመስ የማድረግ እንቅስቃሴ ጀመሩ። በፖለቲካዊ እርከን ውስጥ ለመካተት የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን በማብዛት ፣ ከብዙ ጥረቶች በኋላ ከራሳቸው ከልሂቃኑና ከነሱ ቅርብ ካሉ ሰዎች ውጪ እንዳይሆን ለማድረግ ቻሉ። ልሂቃኑ በቬኑስ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1310 እኤአ የፖሊስ ኃይል በማደራጀት የሚነሱ ተቃውሞችን በጉልበት መደፍጠጥ ጀመሩ። የፖለቲካ መቀመጫቸውን አደላድለው እንዳበቁ ለዚህ ከፍተኛ ስጋት የዳረጋቸውን ኮሜንዳን የመሰሰሉ የውል አይነቶችን እንዲያስተናግድ የፈቀደውን የኢኮኖሚ ህግጋት ወደ መናዱ ተንቀሳቀሱ። የመጀመሪያው የግፍ ዱላ ያረፈውም ኮሜንዳ ላይ ሆነ። ኮሜንዳን በቬኑስ ምድር ሙሉ ለሙሉ እርም አደረጉት። በመቀጠልም የሚደረጉ ማንኛውም ዓለም አቀፍ ንግዶች መንግስት በብቸኝነት እንዲቆጣጠረው አደረጉ። አጋጣሚው ለስርአቱ ቅርብ የነበሩ ባላባቶች ንግዱን መልሰው ለብቻቸው ለማካሄድ ሰፊ እድል ከፈተላቸው። በዓለም አቀፍ የውጭ ንግድ ላይ በግል ለመሰማራት በሚፈልጉም ላይ ከፍተኛ ግብር በመጫን ከገበያ እንዲወጡ አደረጉ። የቬኑስ ኃብትና ስልጣን መልሶ በጥቂቶች እጅ ወደቀ። ይህም የዛች ድንቅና የበለፀገች ከተማ የመጨረሻዋ መጀመሪያ ሆነ። ሌላ የአውሮፓ ሀገሮችና ከተማዎች እያደጉና የህዝብ ቁጥራቸው እየጨመረ ሲሄድ ቬኒስ ግን በፍጥነት ወደ ውድቀቷ ማሽቆልቆሏን ቀጠለች። የንግድ እንቅስቃሴውም ፣ የከተማዋ መስፋፋትም በከፍተኛ ሁኔታ በመቀነሱ እኤአ በ1500 የነበራት የህዝብ ቁጥር ከሁለት ምዕተ ዓመት በፊት ከነበራት በታች ሆነ። የጥቂቶችን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የተወሰደው ፖለቲካዊ እርምጃ ቬኒስን ዳግም ላታንሰራራ አከሰማት። በአሁኑ ወቅት ቬኑስ ከዓሳ ማጥመጃና ከቱሪስት መስህብነት ያለፈ ቦታ የላትም። ከኢኮኖሚ መሪነትም ወደ ሙዚየምነት ላትመለስ ተቀየረች።

ቬኑስና ዘምዘማችን

ሁለቱ ብዙ የሆነ መመሳሰል አላቸው። ዘምዘም ባንክ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ወለድ ዓልባ ባንክ ለመሆን ጫፍ ላይ ደርሶ ነበር።"በህብረተሰቡ ዘንድ ያላው ከፍተኛ የወለድ ዓልባ ባንክ ፍላጎት እንዳለ ሆኖ ለባንክ ሴክተሩም ተደራሽነት ጥሩ አስተዋፅዖ ይኖረዋል" በማለት ያሞካሸው መንግስት የወለድ አልባ ባንክ ምስረታውን ያለምንም ምክንያት ከለከለው። ባንኮች በአብዛኛው የትርፍ ምንጫቸው ከወለድ የሚገኝ ሲሆን ፤ ተበዳሪ ከብድሩ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ማስያዣ እንዳለው ካረጋገጡ በኋላ ብራቸውን ያበድሩታል። ተበዳሪ ትርፋማ ከሆነ ብራቸውን ሲመልሳቸው ከከሰረና የተበደረውን መመለስ ካቃተው ደግሞ ያስያዘውን ንብረት ይወርሱታል። ስለዚህም እነዚህ ባንኮች በኢንቨስትመንቱ ላይ ምንም ዓይነት ሪስክ አይወስዱም ማለት ይቻላል። በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ግለሰብ ምንም ያህል ያማረ የቢዝነስ ሃሳብ ቢኖረው ፤ ለስራ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለማግኘት ማስያዣ ንብረት እስከሌለው ድረስ ብዙ ለውጥ ሊያመጣ የሚችለው የቢዝነስ ሀሳቡ መሬት ሊወርድ የሚችልበት እድል ዝቅተኛ ነው። እነዚህ ባንኮች ማስያዣ ማስያዝ ለሚችለው ብቻ እያበደሩ ባለኃብቶችን ይበልጥ ኃብታም ማድረግን እንጂ ከታች ያለውን የህብረተሰብ ክፍል በቀጥታ የሚደርሱበት አግባብ ጠባብ ነው። በተቃራኒው ወለድ አልባ ባንኮች ትርፋማ ሆኖ ለመቀጠል የግድ የቢዝነሱ አለም ላይ በመሳተፍ ትርፍ ማግኘት ግድ ይላቸዋል። ለዚህም ሲባል በስራቸው የሰበሰቡትን ገንዘብ ትርፋማ የቢዝነስ አማራጭ ያቀረበን ግለሰብ በገንዘባቸው